# ኢትዮጵያ እና ኢትዮጵያዊነት፤
## "ፈጣሪዬ" የምለው እግዚአብሔር: ማነው?

---

*ጥያቄ:-* *ቅድስት ሐና: ልጇን: ቅድስት ድንግል ማርያምን: በታኅሣሥ ወር: በ፲፯ኛው ቀን እንደፀነሰቻትና በመስከረም ፲ ቀን እንደወለደቻት የሚያመለክተውን: የግብፃውያኑን የመጽሐፍ ቃል: ፅንሰቷን: በታኅሣሥ ፳፥ ልደቷንም: በመስከረም ፩ ቀን ላይ እንዲውል ከሚያደርገው: ከእኛ ሥርዓት ጋር እንዴት ነው: የምታስታርቀው?*

መልስ:- የዲያብሎስ ሓሰት: በንስሓ: ወደእግዚአብሔር እውነት ተመልሶ እንዲታረቅ ከማድረግ በቀር: በእግዚአብሔር እውነትና በዲያብሎስ ሓሰት መካከል እንዴት ዕርቅ ሊኖር ይችላል? አይችልም:: በተነሣንበት ጉዳይ ላይ: ዕርቅ ሊኖር የሚችለውም: የሰው የኾነው: የእነርሱ: የሓሰትና የጥፋት ሥራ: የእግዚአብሔር ወደኾነው: ወደእኛው የእውነትና የልማት ሥራ ሲመለስ ብቻ ነው:: ይህን መሠረት በማድረግ: የጥያቄያችሁን መልስ: እንደሚከተለው: በሦስት ቁም ነገሮች አጠቃልዬ አቀርበዋለሁ:-

አንደኛ:- በኹለቱም ወሮች ቀኖች ላይ ፲ (ዓሥር) ያህል ቀኖችን የጨመሩት: እነርሱው: መኾናቸውን: የራሳቸው ሥራ: ዛሬም ይመሰክርባቸዋል፡ ይኸውም: እግዚአብሔር የሠራውንና ኢትዮጵያውያን: እስካኹን ጠብቀውት: እየተጠቀሙበት የሚገኙትን የቀን አቈጣጠር: እነርሱ: ምዕራባውያኑ: በእውቀታቸውና በጥበባቸው ለዋውጠው: በዚሁ አቈጣጠራቸው መሠረት: በዓመቱ ውስጥ ባሉት ወራት ላይ: ከ፮-፲፩ (ከስድስት እስከአሥራ አንድ) ቀኖችን እያከሉ ሲጠቀሙበት በመቀጠላቸው መኾኑ: በግልጽ ይታያል:: ይህ: የተምታታ ግብራቸው: በዚሁ: የ"ስንክሳር" መጽሐፋቸው ውስጥ: እንደገና: በሌላ ማስረጃ ተጋልጦና ተረጋግጦ ስለምናገኘው: የኢትዮጵያ የቃል ኪዳን አምላክ: የፈጸመልንን የቸርነትና የጥበብ ሥራ እናደንቃለን:: ይኸውም: በታኅሣሥ ፲፫ ቀን ስለሚውሉት በዓላት ሲዘረዝሩ: "ወበዛቲ ዕለት: ቦ: እለ ይቤሉ: 'ጸንሰታ ቅድስት ሐና: ለእግዝእትነ ቅድስት ድንግል ማርያም፡'" ማለትም: "በዚች ቀን: 'ቅድስት ሐና: ቅድስት ድንግል ማርያምን ጸነሰቻት፤' የሚሉ አሉ፤" ብለው: በአጭር [illegible] ዐረፍተ ነገር ወስነው የገለጹት ቃል ነው::

የሰዎች የኾነውን ሥርዓት: የመለኮት ከኾነው ጋር ለማስተካከል፥ ወይም: ለመለወጥ በመሞከር: እንደሌላው ድርጊታቸው ኹሉ: አኹንም: በዚህ ረገድ: ያለኀፍረትና ያለይሉኝታ የፈጸሙት የባሰ ጥፋትና በደል: በዚያው: የስንክሳር መጽሐፋቸው ውስጥ ባለው: በራሳቸው ቃል: እንዴት አድርጎ እንደሚመሰክርባቸው: በማስተዋል ተመልከቱት! ይኸውም: "ወተዝካረ በዓለ ልደታሰ: ናሁ ጸሓፍነ: ምሉኣ ወስፉሓ: አመ አሚሩ፡ ለወርኀ ግንቦት:: ይደልወነ ንግበር: በክልኤሆን ዕለታት: ተዝካረ ልደታ: ለእግዝእትነ፤ እስመ ይእቲ ትተነብል በእንቲኣነ፤" ማለትም: "እኛ ግን: 'የልደቷ መታሰቢያ በዓል: በግንቦት ወር፥ በመጀመሪያው ቀን ነው!' ብለን: እነሆ: አልምተንና አስፍተን ጽፈናል:: እመቤታችን: ስለእኛ ትማልዳለችና: የልደቷን መታሰቢያ በዓል: በኹለቱም ቀኖች ልናከብር ይገባናል::" የሚለው ቃላቸው ነው::

# ምዕራፍ ፮፡ በዓል።
## ስለቅድስት ድንግል ማርያም የልደት ቀን።

ኹለተኛ፦ ልጇ፡ ኢየሱስ ክርስቶስ፡ የተስፋ ቃሉን፡ በጽኑ ታማኝነቱ ጠብቆ፡ የቀጠሮውንም ጊዜ፡ ለአንዲት ካልዕት እንኳ ሳያሳልፍ፡ በዚችው፡ ቀዳማዊው አዳም በተገኘባት፡ በመስከረም ፩ ቀን፡ ዳግማዊው አዳም ኾኖ እንደተወለደባት አምነን፡ እነሆ፡ እኛም፡ በዚሁ እምነታችን፡ እየሠራንበት እንገኛለን። እንደዚሁ ኹሉ፡ የዚያች የተስፋ ቃል፡ አማናዊት መፈጸሚያ የኾነችው ድንግል ማርያምም፡ አርአያዋ የኾነችው፡ ቀዳማዊዋ ሔዋን በተገኘችባት፡ በመስከረም ፩ ቀን፡ ዳግማዊት ሔዋን ኾና እንደተወለደችበት መጠራጠርና ማስተባበል አይቻልም። የእኒህ፡ የዳግማውያኑ አዳምና ሔዋን፡ ማለትም፡ የድንግል ማርያምና የኢየሱስ ክርስቶስ፡ በዚሁ፡ በመስከረም ፩ ቀን የመወለዳቸው ምሥጢራዊ እውነታ፡ ቀዳማውያኑ አዳምና ሔዋንም፡ በዚሁ፡ በመስከረም ፩ ቀን ለመገኘታቸው፡ ማረጋገጫ ነው።

ሦስተኛ፦ መነሻው፡ መስከረም ፩ ቀን የኾነውን፡ "ዓመተ ምሕረት" ላስገኘው፡ ለባሕረ ሓሳቡ አቀማመር፡ መሠረቱ፡ የልጇ፡ የኢየሱስ ክርስቶስ መወለድ እንደመኾኑ መጠን፡ ይኸው ዘለዓለማዊ ምሕረት ለተረጋገጠበት፡ ለአዲሱ ኪዳን፡ ሕያው ምልክት የኾነችው፡ እናቱ፡ ድንግል ማርያምም፡ በዚሁ የምሕረት ጸጋ ውስጥ፡ በፍጹም ተዋሕዶ፡ አብራ የመገኘቷን ነገር፡ ፍጹም አስፈላጊ ያደርገዋል። ያለእርሷ መወለድ፡ ይህ የምሕረት ዓመት ሊኖር፡ ዘመኑም፡ "ተጀመረ!" ሊባል አይቻልምና። ስለዚህ፡ "እግዚአብሔር፡ ይህን የምሕረት ጸጋውን፡ ለፍጥረቱ በመስጠቱ ረገድ፡ ለፈጸመው ምሥጢራዊ ሥራውና መለኮታዊ ቸርነቱ፡ ምክንያትና መሣሪያው ያደረጋትን፡ የቅድስት ድንግል ማርያምን የልደት ቀን፡ በዚህ፡ የዓመተ ምሕረቱ መግቢያ የኾነውን፡ የብርሃን ደጃፍ፡ በከፈተበት፡ በመስከረም ፩ ቀን እንዲኾን አደረገ!" ብሎ መደምደሙ ተገቢ ይኾናል። የሔዋን መገኘት፡ በአዳም ቀድሞ መፈጠር ላይ የተመሠረተ እንደነበረ ኹሉ፡ የእግዚአብሔር ወልድ፡ በኢየሱስ ክርስቶስ ሰውነት መገለጥ፡ በድንግል ማርያም ቀድሞ መወለድ ላይ ተመሥርቷል ማለት ነው።

በመሠረቱስ፡ "ኪዳነ ምሕረት" ከማን ተገኘ? በእርሷ፡ በድንግል ማርያምና በልጇ፡ በኢየሱስ ክርስቶስ አንድነት አይደለምን? "ኪዳነ ምሕረት" የሚለው ስያሜስ፡ ለማን ተሰጠ? አምላክን፡ በድንግልና ጸንሳና ወልዳ፡ አጥብታና አሳድጋ፡ በዘለዓለማዊ እናትነት ለምትኖረው፡ ለእርሷ፡ ለድንግል ማርያም አይደለምን? ለመኾኑ፡ የቀደመችው የብሉይ ኪዳኗም ኾነች፡ የአዲስ ኪዳኑ ጽላት፡ ያለታቦት፡ ታቦቷም፡ ያለጽላት፡ አንዳቸው፡ ያለአንዳቸው ሊኖሩ፡ ከቶ ይቻላቸዋልን? አይቻላቸውም። ስለዚህ፡ "ከማሕፀን ጀምሮ እስከዛሬ በሰማያት፡ በሥጋና በነፍስ፥ በመንፈስም ያልተለያዩት፡ ኢየሱስ ክርስቶስና እናቱ ድንግል ማርያም፡ ለፍጥረተ ዓለሙ፡ ዓመተ ምሕረቱን፡ ማለትም፡ የምሕረቱን ዘመን ለማስገኘት፡ ሳይለያዩ፡ በሥጋ ቅደም ተከተል፡ በዚያችው፡ በአንዲቱ፡ በመስከረም ፩ ቀን፡ በሥጋ ተወልደው እንዲገለጡ፡ የእግዚአብሔር ጥበብና ፈቃድ ኾነ!" ብሎ መደምደም፡ የፍጹም ሃይማኖት ጣፋጭ ፍሬ ለመኾኑ ሊጠረጠር ከቶ አይቻልም።

# ኢትዮጵያ እና ኢትዮጵያዊነት፤
## "ፈጣሪዬ" የምለው እግዚአብሔር፡ ማነው?

---

እንግዲህ፡ እንዲህ አድርገን ከምናከብራቸው በዓላት መካከል፡ "ዓቢያን" እና "ንዑሳን"፡ ተብለውና በኹለት መደቦች ተለይተው የሚታወቁ መኖራቸውን ልትገነዘቡ ይገባችኋል።

## "ዓበይት" እና "ንዑሳን" በዓላት።

ጥያቄ:- *"ዓቢያን" እና "ንዑሳን" ተብለው የተለዩት በዓላት የትኞቹ ናቸው?*

መልስ:- "ዓቢያን" እና "ንዑሳን"፡ ማለት፡ "ታላላቅ" እና "ታናናሽ" ማለት ነው። በቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያውያን ዘንድ፡ "ዓቢያን በዓላት" የሚባሉት:-

፩ኛ፡ በ፲፮ ዓመታት የተራራቁትን፤ ነገር ግን፡ የዘመን፤ የወርና የዕለት ዑደት ያገናኛቸውን፡ የጌታችንና የእመቤታችን የልደት ዕለታትን የያዘው፡ መስከረም ፩ ቀን የሚውለው፡ "ርእሰ ዐውደ ዓመት"፡

፪ኛ፡ መሢሑ ሕፃን፡ "ኢየሱስ" ተብሎ፡ የኪዳኑ አብርሃምኑ ሥርዓት የፈጸመበት፡ መስከረም ፯ ቀን የሚውለው፡ "ግዝረተ ኢየሱስ"፥

፫ኛ፡ ሕፃኑ ኢየሱስ፡ በኦሪቱ ሥርዓት፡ በእግዚአብሔር ፊት ሊቆም፡ በአርባ ቀኑ፡ በእናቱ ቅድስት ድንግል ማርያም ዕቅፍ፡ ከመሥዋዕቱ ቁርባን ጋር፡ ወደቤተ መቅደስ የገባበትና ለስምዖን ተገልጾ የታየበት፡ ጥቅምት ፲ ቀን የሚውለው፡ "በዓለ ስምዖን"፡

፬ኛ፡ ታኅሣሥ ፩ ቀን የሚውለው፡ ብሥራተ ገብርኤልና ታኅሣሥ ፮ ቀን የሚውለው፡ ዕንሰታ ለማርያም አብረው የሚከብሩበት፡ "ዕለተ ትስብእት"፥

፭ኛ፡ በኢየሱስ ክርስቶስ ትስብእት (መፀነስ)፡ የእግዚአብሔር፡ የአንድነቱና የሦስትነቱ ምሥጢር በተገለጸበት ወራት፡ ጥር ፮ ቀን የሚውለው፡ "የአስተርእዮ ሥላሴ"፥

፮ኛ፡ በተዋሕዶ የከበረው፡ የኢየሱስ ክርስቶስ ፍጹም ጸምላክነትና ፍጹም ሰውነት ለዓለሙ ተገልጦ የተመሰከረበት፡ ጥር ፲፩ ቀን የሚውለው፡ "ጥምቀት"፥

፯ኛ፡ ኢየሱስ ክርስቶስ፡ የእናቱን የቅድስት ድንግል ማርያምን ፈቃድ በመፈጸም፡ እመ አምላክነቷንና አማላጅነቷን ያሳወቀበት፡ ጥር ፲፪ ቀን የሚውለው፡ "ቃና ዘገሊላ"፥

፰ኛ፡ ጥር ፳፩ ቀን የሚውለው፡ "አስተርእዮ ማርያም" የሚባለው፡ የቅድስት ድንግል ማርያም፡ የዕረፍተ ሥጋዋ እና መስከረም ፳፩ ቀን የሚውለው፡ የዕርገቷ መታሰቢያ፥

፱ኛ፡ እግዚአብሔር ወልድ፡ "ኢየሱስ ክርስቶስ" ከቅድስት ድንግል ማርያም በመወለዱ፡ የተገኘው ዘለዓለማዊ የምሕረት ቃል ኪዳን የሚታሰብበት፡ የካቲት ፲፮ ቀን የሚውለው፡ "ኪዳነ ምሕረት"፥

# ምዕራፍ ፯፣ በዓል።
## "ዓበይት" እና "ንዑሳን" በዓላት።

---

፲ኛ: "የጽዮን ንጉሥ" የኾነው: ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ: እንደነቢያቱ ቃል: በአህያዋና በውርንጫላዩቱ ላይ ተቀምጦ: "ሆሣዕና በአርያም! በእግዚአብሔር ስም የሚመጣ ቡሩክ ነው!" እየተባለ: ለድል አድራጊ እንደሚደረገው: የዘንባባ ዝንጣፊ በያዙ: ሕፃናትና አዛውንት: ወንዶችና ሴቶች: ሕዝብና ደቀ መዛሙርቱ ታጅቦ: በዕለተ እሑድ ወደኢየሩሳሌም ከተማ የገባበት: "ሆሣዕና":

፲፩ኛ: ከ"ሆሣዕና" በኋላ: ከትንሣኤ በፊት ባለው: የሰሙነ ሕማማት ዕለተ ዓርብ የሚውለው: "ስቅለት":

፲፪ኛ: ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ: እንደ,ቃሉ: ለሦስት መዓልትና ለሦስት ሌሊት: በከርሠ መቃብር አድሮ: ከሙታን ተለይቶ: በዕለተ እሑድ የተነሣበት: "ትንሣኤ":

፲፫ኛ: ከትንሣኤ እሑድ በኋላ: በአርባኛው ቀን: በዕለተ ሐሙስ የሚውለው: "የጌታ ዕርገት":

፲፬ኛ: ከትንሣኤ እሑድ በኋላ: ባለው: በሃምሳኛው ቀን የሚውለውና መንፈስ ቅዱስ በሐዋርያት ላይ የወረደበት: "በዓለ ፶ምሳ":

፲፭ኛ: ጌታ: ግርማ መለኮቱን: በብርሃን ክብሩ: ለነቢያቱና ለሐዋርያቱ ተጠሪዎች የገለጠበት: ነሐሴ ፲፫ ቀን የሚውለው: "ደብረ ታቦር":

፲፮ኛ: ነሐሴ ፲፮ ቀን የሚውለው: የቅድስት ድንግል ማርያም የትንሣኤዋና የዕርገትዋ መታሰቢያ የኾነችው: "ፍልሰታ ለማርያም" ናቸው።

"ንዑሳን በዓላት" የሚባሉት ደግሞ:-

፩ኛ: ጌታችን ተሰቅሎበት: ሥጋው የተቆረሰበትና ደሙ የፈሰሰበት መስቀል የሚታሰብበት: መስከረም ፲፯ ቀን የሚውለው: "መስቀል":

፪ኛ: እመቤታችን: ሕፃን ልጇን ይዛ: ከጻድቁ ቅዱስ ዮሴፍና ከሰሎሜ ጋር: በኢትዮጵያና በግብፅ: "ቍስቋም" በተባለችው: የኢትዮጵያውያን ገዳም የፈጸሙት ስደታቸው የሚታሰብበት: ኅዳር ፮ ቀን የሚውለው: "ቍስቋም":

፫ኛ: ጌታችንና እመቤታችን: ዓሥሩ የእግዚአብሔር ቃላት በተጻፉባቸው ጽላትና እነርሱን በያዘችው ታቦት አድረው የኖሩባት ኪዳነ ሙሴ የምትከብርበት: ኅዳር ፳፩ ቀን የሚውለው: "ኅዳር ጽዮን"፥

፬ኛ: ሕፃን ማርያም: እንደቅዱሳን ወላጆቿ ስእለት: እግዚአብሔርን ልታገለግል: በሦስት ዓመቷ: ወደቤተ መቅደስ ገብታ መኖር የጀመረችበት: ታኅሣሥ ፫ ቀን የሚውለው: "በአታ ለማርያም"፥ እንዲሁም: ታኅሣሥ ፩ ቀን ከሚውለው: ከ"ትስብእት" በኋላና ከ"አስተርእዮ ሥላሴ" በፊት ባሉት አራት ተከታታይ የእሑድ ሰንበታት የሚዘከሩት:-

# ኢትዮጵያ እና ኢትዮጵያዊነት፤
## “ፈጣሪዬ” የምለው እግዚአብሔር፡ ማነው?

፭ኛ፡ “ስብከት”፥
፮ኛ፡ “ብርሃን”፥
፯ኛ፡ “ኖላዊ”፥
፰ኛ፡ “በዓለ ወልድ”፥

፱ኛ፡ በዓቢይ ጾም እኩሌታ እሑድ የሚውለው፡ አምላካችን ኢየሱስ ክርስቶስ፡ ስለዳግም ምጽአቱና ስለዓለሙ ፍጻሜ፡ ለደቀ መዛሙርቱ፡ ምሥጢሩን፡ በተራራው የአትክልት ቦታ የገለጠበት፡ “ደብረ ዘይት”፥

፲ኛ፡ ከጌታ ትንሣኤ እሑድ በኋላ ባለው በቀጣዩ ዕለተ ሰኑይ (ሰኞ) የሚውለው “ማዕዶት” ናቸው።

የመላእክት፥ የጻድቃንና የሰማዕታት የዓመት በዓላት፡ በእነዚህ ውስጥ ይጠቃለላሉ።

### ርእሰ ዐውደ ዓመት።

ጥያቄ፦ *መልካም! እንግዴህ፡ በቅድሚያ፡ ልትነግረን የሚያስፈልገን፡ እያንዳንዱ አዲስ ዓመት ስለሚጀመርበት፡ ስለመስከረም ፩ ቀን በዓላችን መኾኑ አይደለም?*

መልስ፦ አዎን! “የዓመቱ በዓላት ዘውድ” የኾነው ታላቁ በዓላችን፡ በመስከረም ፩ ቀን የሚውለው ነው፤ ስለዚህ፡ “ርእሰ ዓውደ ዓመት” ይባላል፤ “ቅዱስ ዮሓንስ”፥ “የዘመን መለወጫ”፥ “ዕንቍጣጣሽ” በምንላቸው የስም አጠራሮች ይታወቃል። እነዚህ ስያሜዎች፡ ለዚች ዕለት፡ ለምን እንደተሰጡ፡ ከዚህ የሚከተሉት አጫጭር መግለጫዎች ያስረዱችኋል፦

ሀ. በአገራችን ኢትዮጵያ፡ “ክረምት” የምንለው፡ የዝናቡ ወራት አልፎ፡ የአበባው ወራት ሲተካና በደመና ተሸፍኖ የከረመው ሰማይ ጠርቶ፡ በፀሓይ ብርሃን ሲደምቅ፡ “መስከረም ጠባ!” እንላለን። በዚህ ጊዜ የሚሰማን ደስታ፡ አፍአዊ ብቻ ሳይኾን፡ ውሳጣዊም፥ መንፈሳዊም ስለኾነ፡ በቃላት ሊገለጽ ያዳግታል። ወራቱ፡ ተለውጦ፡ በብርሃን ፀዳል ሲሞላ፥ ዘመኑ፡ በአዲስ፥ ያውም በምሕረት ዓመት ሲተካ፥ የእኛም መንፈስ፡ አብሮ፡ በደስታ ብርሃን ይፈካል፤ አእምሮአችንም ይታደሳል።

አዎን! አሮጌው ዘመን አልፎ፡ አዲሱ ሲተካ፡ “መስከረም ጠባ!,ፀሓይ ወጣ!” ብለን፡ የአዲሱን ዓመት፡ የሥጋዊ ዕድሜ ጉዞ፡ በሥነ ፍጥረት እንጀምራለን፤ እንደዚሁ ኹሉ፡ በአዳምና ሔዋን፡ የጋብቻ ቃል ኪዳን ተወጥኖ፡ በዳግማዊው አዳም ኢየሱስ ክርስቶስና በዳግማዊቷ ሔዋን ድንግል ማርያም የምሕረት ቃል ኪዳን የተፈጸመውን፡ የዓመቱን መንፈሳዊ የሕይወት ጉዟችንን “ዑደት” (ዙረት)፡ መስከረም ፩ ቀን በሚውለው ዕለት እንጀምራለን፤ ስለዚህ፡ ዕለቲቱን፡ በዚህ ገጽታዋ፡ በዓል አድርገን ስለምናከብራት፡ “የዓመቱ ዙረት መነሻ ናት” ለማለት፡ “ርእሰ ዓውደ ዓመት” ትባላለች።

# ምዕራፍ ፮፤ በዓል:: ዓበይትና ንዑሳን በዓላት::

## ርእሰ ዐውደ ዓመት::

"ዖደ" በግእዝ: "ዞረ" ማለት ሲኾን: "ዓውድ": "መዞርያ" ማለት ነው:: ያለፈው የዓመቱ ዙረት: በ፫፻፷፭ ቀኖች ተሩብ ውስጥ አልቆ: አዲሱ ዙረት የተጀመረ መኾኑን ለማስታወቅ: ይህችን ቀን: "ርእሰ ዓውደ ዓመት" ብለን እናከብራታለን:: "መዞር": መሽከርከርን: ወይም: ክብ የኾነ መስመርን ተከትሎ መጓዝን ስለሚያሳይ: ይህ ቀን: በዘመናዊው የሥነ እውቀት (science) አነጋገር: "መሬት: ፀሓይን: አንድ ጊዜ ዞራ አብቅታ: አዲሱን ዙረቷን: እንደገና የምትጀምርበት ዕለት ይባላል!" ማለት ነው::

ይህች: መስከረም ፩ ቀን: የፈጣሪ ዕፁብ ድንቅ ሥራ የኾነው ሥነ ፍጥረት የተጀመረባትን ዕለት ለማዘከር የተመደበች ናት፤ በዚች ዕለት: የቤተ ክህነት ሊቆቻችን: የሥነ ፍጥረት ውጤቶች ኾነው: ከቸሩ እግዚአብሔር: ለሰው ልጆች ሥጋዊ ኑሮና መንፈሳዊ ሕይወት፥ ለቊርባንና ለመሥዋዕትም እንደሚያስፈልጋቸው አውቆ: በየዓመቱ: ከምድር አብቅሎ ከሰጣቸው ሲሳያት መካከል: ለዓይነት: ከአዝርዕቱ፥ ከአትክልቱና ከዕፀዋቱ: የስንዴን፥ የወይንን፥ የጽጌያትን ፍሬዎች፥ የዕጣንና የጧፉ ሳይቀር: በመሶበ ወርቅ ኾኖ: የዕንቊጣጣሽ አበባ ጉንጉን ጭምር: ለበረከት ያህል: በቤተ ክርስቲያን ያስቀርባሉ፤ እነዚህ ኹሉ ተ[illegible]ርድረው በሚታዩበት፥ ካህናቱና ሕዝቡም: ጸጥ ብለው በተቀመጡበት: ስለሊ[illegible]ጋሡ ፈጣሪና ስለተለጋሾቹ ፍጡራን፥ በጠቅላላ: ስለሥነ ፍጥረት፥ ስለጊዜ አሰላልና ስለዘመን አቈጣጠር: ማለትም: ስለካልዕት፥ ደቂቃ፥ ሰዓት፥ መዓልትና ሌሊት፥ ዕለታትና ሳምንታት፥ ወራትና ዓመታት፥ በጠቅላላ ስለዘመናት ጭምር: በቃላቸው: አስፋፍተውና አብራርተው፥ ተንትነውም ያስረዳሉ::

ዓውደ ዕለት፥ ዓውደ ወርኅ፥ ዓውደ ዓመት፥ ዓውደ አበቅቴ፥ ዓውደ ማኅተም፥ ዓውደ ቀመርና ዓውደ ፀሓይ በተባሉት መሥፈሪያዎች: የዓመቱን የቀን መቊጠሪያ ያወጣሉ:: እንዲሁም: "አበቅቴ" እና "መጥቅዕ" በተባሉ የቊጥር መደቦች: የዓመቱ አጽዋማት (የጾም ጊዜዎች) የሚጀምሩበትንና የሚያበቁበትን፥ የዓመቱም በዓላት የሚውሉበትን ዕለትና ወር ያስታውቃሉ:: ሊቃውንቱ: ይህን: "ባሕረ ሓሳብ" የሚባለውን: ጥልቅ የሒሳብ ሥራ፥ ስሌቱንና አቀማመሩን አከናውነው: ለቤተ ሕዝቡ: በይፋ የሚያሰሙት: እዚያው: እቤተ ክርስቲያኑ ጉባዔ መካከል ቆመው: በቃላቸው ስለኾነ: የአእምሮ ችሎታቸው ያስደንቃል::

ስለእኛ ኢትዮጵያውያን የዘመን አቈጣጠር ጥንታዊነት፥ ብቸኝነትና ትክክለኛነት፥ ከሌሎቹም የዓለም ሕዝቦች የአቈጣጠር ስልት ስለሚለይበት ኹኔታ የሚያብራራውን ዝርዝር ሓተታ: "ኢትዮጵያ: የዓለሙ መፋረጃ!"[፲፰፻] በሚለው መጽሓፌ ውስጥ ታገኙታላችሁና: ያን ተመልከቱት!

ለ. *"እነሆ: መንገድህን የሚጠርግ መልእክተኛዬን: በፊትህ እልካለሁ፤ 'የጌታን መንገድ አዘጋጁ! ጥርጊያውንም አቅኑ!' እያለ: በምድረ በዳ የሚጮህ ሰው ድምፅ!"* ተብሎ: በነቢዩ በኢሳይያስ የተጻፈውንና ስለኤልያስ የተነገረውን ትንቢት ለመፈጸም የመጣውን: መጥምቁ ዮሓንስን ለማስታወስ: የዚች ዕለት በዓል: "ቅዱስ ዮሓንስ"ም ይባላል::

# ኢትዮጵያ እና ኢትዮጵያዊነት፤
## “ፈጣሪዬ” የምለው እግዚአብሔር፡ ማነው?

---

እግዚአብሔር ወልድ፡ በኢየሱስ ክርስቶስ፡ ሰው ኾኖ በመወለዱ፡ “ዓመተ ምሕረት” ለተባለው፡ ለዘመነ ሓዲስ፡ ማለትም፡ ለአዲሱ ዘመን መግቢያና ለተስፋው መፈጸሚያ ማረጋገጫ እንደኾነ ኹሉ፡ የነቢያት መደምደሚያ የኾነው፡ የመጥምቁ ዮሓንስ፡ የሰማዕትነት ዕረፍት ደግሞ፡ ለዘመነ ብሉይ፡ ማለትም፡ ለአሮጌው ዘመን ማብቂያ ምልክት ኾነ::

ሐ. የመጀመሪያዎቹ ወንድና ሴት፡ አዳምና ሔዋን የተፈጠሩባት፡ የጋብቻ ቃል ኪዳናቸውንም፡ ከፈጣሪያቸው የተቀበሉባት፥ ኢትዮጵያም፡ በእግዚአብሔር መንግሥትነት ተመሥርታ፡ የነጻነት ህልውናዋን የጀመረችባት ዕለት የምትዘከርባት፥ ኖኅና ልጆቹ፡ ከጥፋት ውኃ ድነው፡ አራራት ላይ ከመርከባቸው የወጡባት፥ በተለይ፡ የኋለኞቹ አዳምና ሔዋን፡ ማለትም፡ በፍጥረት መጀመሪያ፡ በፈጣሪ ጥበባት የተገኙትን ምሥጢራት ኹሉ፡ በጥራት አጠቃልሎና አዋሕዶ፡ ለፍጹሙ መልካም ሕይወት ያበቃው ኢየሱስ ክርስቶስና እናቱ፡ ቅድስት ድንግል ማርያም ስለተወለዱባት፡ “ዓመተ ምሕረት”ን ያስገኘች በመኾኗ፡ በዓሏ፡ “የዘመን መለወጫ” ይባላል::

*መ. “እናንተ፡ ‘እኔ፡ ክርስቶስ አይደለሁም፤ ነገር ግን፡ ከእርሱ በፊት ተልኬአለሁ!’ እንዳልሁ፡ ራሳችሁ ትመሰክሩልኛላችሁ:: ሙሽራዪቱ ያለችው እርሱ፡ ሙሽራ ነው፤ ቆሞ የሚሰማው ሚዜው ግን፡ በሙሽራው ድምፅ እጅግ ደስ ይለዋል:: እንግዴህ፡ ይህ ደስታዬ ተፈጸመ::”* ብሎ መጥምቁ ዮሓንስ የተናገረውን ቃል እናስታውሳለን፤ በዚህ ቃል፡ *“ሙሽራው”* የተባለው፡ ሕፃኑ ኢየሱስ ክርስቶስ፡ በበረት ተወልዶ ሣለ፡ ሰብአ ሰገል እየሰገዱ፡ እጅ መንሻቸውን እንዳቀረቡለትም እናዘክራለን፤ በዚያን ጊዜ፡ እኒሁ ሰብአ ሰገል፡ ለሙሽራው እናትና ለአራሲቱ ሙሽሪት፡ ለኢትዮጵያዊቷ ቅድስት ድንግል ማርያም፡ “ለአንቺም፡ ዕንቍ ለጣትሽ እነሆ!” ብለው ስጦታቸውን አበርክተውላት ነበረ:: የሰማይ መላእክትና የምድር ሠራዊት፡ የምሥራች ደስታቸውን በአንድነት በገለጹባት፡ በዚች፡ የልደት ቀን፡ ዛሬም፡ እኛ ኢትዮጵያውያን፡ የአበባ ጉንጉናችንን ይዘን፡ ስለእናት አገራችንና[፻፹] መቅደስ ንግሥታችን፡ እርስ በርሳችን፡ “እንቍጣጣሽ!” እንባባላለን::

### በበዓሉ የሚፈጸሙ ሃይማኖታውያን ባህሎች::

*ጥያቄ:- በዚህ በዓል ጊዜ፡ እንደፈረንጆቹ የገና ዛፍ፡ እኛም፡ በግል፥ በቤተሰብና በኅብረተሰብ ደረጃ ልንፈጽማቸው የሚገቡን፡ ሥርዓቶችና ባህሉች አሉን ወይ? ካሉን፡ ምን ምን እንደኾኑ ዘርዝረህ ብትገልጽልን!?*

**መልስ:-** አዎን! አሉን:: ከእነዚህም መካከል፡ እስኪ፡ ዋና ዋናዎቹን ልጠቃቅስላችሁ:-

፩ኛ ለመስከረም ፩ ቀን አጥቢያ፡ ገና ሌሊቱ ሳይነጋ፡ ሰው ኹሉ፡ በቤቱ፡ ወይም ወደወንዝ ወርዶ፡ ገላውን የመታጠብ ልማድ አለ::

# ምዕራፍ ፮፤ በዓል:: ዓበይትና ንዑሳን በዓላት::

## ርእሰ ዐውደ ዓመት::

### በበዓሉ የሚፈጸሙ ሃይማኖታውያን ባህሎች::

---

ይኸውም: ያለፈውን ዓመት ዕድፍ: ከሰውነት ገላ ለማስወገድ ብቻ ሳይኾን: የማይጠቅመውንና የሚጎዳውን አሳብና ነገር ኹሉ: ከነጓዙ ጥሎ: ሰውነትንም: ከሥጋ ዕድፍ አጽድቶና ከነፍስ ኃጢአት አንጽቶ: እያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ: በየአጥቢያ ቤተ ክርስቲያኑ በመገኘት አስቀድሶ: ራሱን: በኢየሱስ ክርስቶስ ቅዱስ ሥጋና ክቡር ደምም አጽድቶ: አዲሱን: የምሕረት ዓመት: በአዲስ መንፈስ መቀበል ይገባል ማለት ነው::

፪ኛ. ገና በዋዜማው ማታ: የቤቱ ወንድ ኹሉ: ችቦውን ይዞ: ወደማድቤት እየገባ: ከለኰሰ በኋላ: ተመልሶ ሲወጣ: የደጃፉን መድረክ በችቦው እሳት ይተረኩሳል፤ በዚህ ጊዜ: እርሱም: ሴቶቹም: ድምፃቸውን እያሰሙ: "የጎመን ምንቸት ውጣ! የገንፎ ምንቸት ግባ!" ይላሉ:: ይህም: "በክረምቱ ወራት: በብዛት: ለምግብ እየተቀቀለ የሚቀርበው: በቀላሉ: በዝናብ የበቀለው: የጓሮው አትክልት ነበር፤ እንግዲህ ወዲህ ግን: የተዘራው የእህል ዘር በቅሎ: አፍርቶና ተመርቶ፥ ታጭዶና ተወቅቶ: ወደጎተራ የሚገባበትና ለምግብ የሚቀርብበት ጊዜ ደረሰ!" የሚለውን የምሥራች መልእክት ማሰማታቸውና ይህን ላደረገላቸው ፈጣሪ: ምስጋናቸውን ማቅረባቸው ነው::

፫ኛ የችቦው መብራት: "የክረምቱ ጨለማ አልፎ: የፀሓዩ ብርሃን ወጣልን!" የሚለውን ደስታቸውን ለመግለጽ ነው::

፬ኛ ጧት በማለዳው: ወንዶችና ሴቶች ልጆች: የአዲሱን የምሕረት ዓመት መግባት በማብሠር: ለየወላጆቻቸውና ለየቤተሰቦቻቸው፥ ለቅርብ ጎረቤቶቻቸውና ለሩቅ ዘመዶቻቸውም: ወደየመኖሪያ ቤቶቻቸው እየኼዱና "ዕንቍጣጣሽ! እግዚአብሔር: እንኳን ከዘመን ወደዘመን አሸጋግሮ: ለአዲሱ ዓመት፥ ለዓውደ ዓመቱና ለብርሃን ልደቱ አደረሳችሁ!" እያሉ: በመስቀልኛና በነዶ መልክ: ራሳቸው የሠሩትን: የአበባ ጉንጉን ያቀርባሉ::

፭ኛ. በተለይ ቈነጃጅቱ (ልጃገረዶቹ): በኅብረት ኾነው: "አበባዬ ሆይ!"፥ "ለምለም!" የሚለውን የዕንቍጣጣሽ ዘፈን በመቀባበል: "ባልንጀሮቼ፥ ቁሙ በተራ! እንጨት ሰብሬ፥ ቤት እስክሠራ! እንኳን ቤትና፥ የለኝም ዐጥር! እንደው አድራለሁ: ኮከብ ስቆጥር! ... ባልንጀሮቼ፥ አትበተኑ! እስክንለማ፥ አብራችሁ ኹኑ! ...ባልንጀሮቼ፥ የለም አትበሉ! የተገኘውን፥ አብራችሁ ብሉ! ባልንጀሮቼ፥ አብረን አብረን! ሞትም ቢመጣ፥ ተነባብረን!" እያሉ: በሠፈራቸው ውስጥ: በየቤቱ እየተዘዋወሩ: መልካም ምኞታቸውን ይገልጻሉ:: ባለቤቶቹም: ያላቸውን ስጦታ በማበርከት ይመርቋቸዋል::

፮ኛ. ቀደም ብሎ እንደተገለጸው: ሰዉ ኹሉ: የውስጥ መንፈሱ: በደስታ የበዓል ስሜት ተመልቶ፥ የላይ አካሉም: በንጹሕ ክት ልብሱ ተሽልሞ: ከሌሊቱ ጀምሮ: ወደየሰበካ ቤተ ክርስቲያኑ ይኼዳል፤ እዚያም: እግዚአብሔር: ለአዲሱ የምሕረት ዓመት ስላበቃው: ምስጋናውን ካቀረበና የምሕረቱ ኪዳን ማረጋገጫ የኾነውን ቅዱስ ቍርባን ከተቀበለ በኋላ: ወደየቤቱ ይመለሳል::

## ኢትዮጵያ እና ኢትዮጵያዊነት፤
### "ፈጣሪዬ" የምለው እግዚአብሔር፡ ማነው?

---

፯ኛ. እዚያም፡ በለምለም ሣርና በቀጤማ ጐዝጓዝ፥ በጽጌረዳና በአደይ አበባ መዓዛ ታውዶና ተጊጦ፤ በመልከ ጼዴቅ ኅብስተ አኰቴትና ጽዋዓ በረከት ምሳሌ፡ "ጠበል ጠዲቅ" ተብሎ የተሠየመው፡ ዳቦና ጠላው ተዘጋጅቶ በሚጠብቀው ቤቱ እንደተገኘና ቤተሰቡ እንደተሰባሰበ፡ ካህን ካለ፡ በካህኑ እጅ፡ ካህን ከሌለ፡ እያንዳንዱ እውነተኛ ኢትዮጵያዊ፡ ሴቱም፡ ወንዱም፡ በመልከ ጼዴቅ ልጅነቱ፡ የመልከ ጼዴቅ ጸጋና በረከት ያደረበት ስለኾነ፡ ኹሉም ካህን ነውና፡ "በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ" በሚለው መክፈቻ፡ "አቡነ ዘበሰማያትን" እና "በሰላመ ቅዱስ ገብርኤል መልአክ" የሚባሉትን፡ የጌታችንን የምስጋና ጸሎትና የእመቤታችንን የሰላምታ ጸሎት በኅብረት ይደግማሉ። በመጨረሻ፡ የቤተሰቡ አባወራ (እርሱ ከሌለ፡ የቤቱ እመቤት)፡ በእጁ የመስቀል ምልክት እያማተበ፡ ጠበል ጠዲቁን ባርኮ፡ መጀመሪያ ዳቦውን ይቆርሰዋል፤ ያም ተሸንሽኖና በዝርግ ማቅረቢያ ተደርጎ፡ አዳዩ፡ "በረከተ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ!" እያለ፡ በዚያ ላለው፡ ለእያንዳንዱ ታዳሚ እያዞረ ያድለዋል፡ ተቀባዩም፡ "አሜን!" እያለ፡ ድርሻውን እያነሣ፡ በአክብሮት ከሳመ በኋላ፡ እንደጠዲቅነቱ፡ በእጁ እየቆረሰ ይመገበዋል፤ ጠላውም፡ እንደዚሁ፡ በየጽዋ ተቀድቶ፡ ይታደልና፡ ኹሉም፡ በጠበል መልክ እየቀመሱ ይጠጡታል። ከዚህ በኋላ ነው፡ የበዓሉ መሰናዶ የኾነው ገበታ ተዘርግቶ፡ ግብዣው የሚቀልጠው።

፰ኛ. እስከመስቀል በዓል ድረስ ባሉት ኹለት ሳምንታት፡ ዘመድ፡ ከዘመዱ፡ ጎረቤት፡ ከጎረቤቱ፡ ወዳጅ፡ ከወዳጁ፤ ትልቁም፡ ትንሹም፤ ሴቱም፡ ወንዱም፡ ኹሉም ሲገናኝ፡ እየተፈላለገም፡ "እንኳን አደረሰህ! አደረሰሽ! አደረሰን! አደረሳችሁ!" እየተባባለ፡ ቀደም ብለው የተጠቀሱትን የደስታ ሰላምታዎችና የመልካም ምኞት መግለጫ ቃላቶች ሲለዋወጥና በየቤቱ የበዓል ድግሱን እያዘጋጀ፡ ተጠራርቶ ሲገባበዝ፥ ደሆችንም ሲያበላ ይሰነብታል።

፱ኛ. በዚህ ዕለት፡ "ገና (ና ይጠብቃል)" የምንለውን፡ የጌታችንና የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስን፡ የልደቱን በዓል ስናከብር፡ ሌሎች፡ ብዙ ትዝታዎች ይመጡብናል። በልጅነት ዕድሜያችን፡ ትዝ ከሚሉን ነገሮች መካከል፡ በየቤታችን፡ የገና ዳቦው ተጋግሮና ጠላው ተጠምቆ፥ እንጀራውና ወጡ ተዘጋጅቶ፥ ቄጠማው ተጐዝጉዞና ምንጣፉ ተነጥፎ፥ በዓሉ፡ የጌታ ልደት በመኾኑም፡ ረቡዕና ዓርብ ሳይቀሩ፡ ፍስክ ኾነው የሚውሉበት ስለኾነ፡ ዶሮውና በጉ ታርዶ፥ በየጎረቤቱም የተጣለው የፍሪዳው ቅርጫ ሥጋ መጥቶ የሚደረገው መሰናዶና ያለው ሽርጉድ አንዱ ነው።

አዎን! በዚህ ዕለት፡ ወንዱም፥ ሴቱም፥ ትልቁም፥ ትንሹም፡ እርስ በርሱ፡ በቤት ውስጥ፥ በመንገድም ሲገናኝ፡ ሰላምታው ኹሉ፡ ቀደም ብሎ እንደተገለጸው፡ "እንኳን አደረሰህ! አደረሰሽ! አደረሰዎ! አደረሳችሁ!" እየተባባለ የሚሳሳመውና ሰላምታ የሚሰጣጣው፥ በውጭም፡ ጎልማሶች፡ ቡድን ለይተው፡ "በገና ጨዋታ! አይቆጡም ጌታ!" እያሉ፡ በገና ዱላና "ጥንግ" በተባለች፡ የከብት አጥንት፡ ወይም፡ ከእንጨት ወይም ከጨርቅ የተሠራች ጠጣር ኳስ፡ የሚጫወቱት፡ የሰፌ ሜዳ ጨዋታ ትዝ ይላል።

፲ኛ. ሌላው ደግሞ: በየቤተ ክርስቲያኑ: ከዋዜማው ማታ አንሥቶ: ካህናቱ: መዘምራኑና ሕዝቡ: *"ክርስቶስ: ከቅድስት ድንግል ስለተወለደ: ዛሬ: ታላቅ የደስታ ቀን ነው! ...እግዚአብሔር: ራሱን: መሥዋዕት አድርጎ በማቅረብ: ፍጥረቱን ኹሉ ሊያድን: ዛሬ ተወለደ! በበረት ውስጥ ተኛ! በጨርቅም ተጠቀለለ!"* የሚል ትርጉም ያለውን በግእዙ: *"ዮም: ፍሥሐ ኮነ! በእንተ ልደቱ ለክርስቶስ፥ እምቅድስት ድንግል! ...በጎል ሰከበ፥ በአጽርቅት ተጠብለለ፥ እግዚእ መድኅን፣ ቤዛ ኵሉ ዓለም: ዮም ተወልደ!"* እያሉ: ለቸሩ ፈጣሪያቸው: ሌሊቱን ሙሉ: በዜማና በማኅሌት ሲያቀርቡት የሚያድሩት: የምስጋና መዝሙር ነው:: ከዚያም: እኩለ ሌሊት ሲኾን: ቅዳሴ ገብተው: ሥርዓተ ቅዳሴው: በካህናቱና በምእመናኑ የቅዱስ ቍርባን ማቀበልና መቀበል ከተፈጸመ በኋላ: ሰዉ ኹሉ: ቅዳሴ ጠበል እየጠጣና እየተባረከ: ወደየቤቱ በሚመለስበት ጊዜ: ያለው መንፈሳዊ ደስታ: ትዝታው: ከቶ አይረሳም::

ኢትዮጵያውያን: በዚህ በዓላችን ጊዜ: *"ዮም ፍሥሐ ኮነ! በእንተ ልደቱ ለክርስቶስ!"* ማለትም: "ዛሬ የደስታ ቀን ኾነ! የክርስቶስ ልደቱ ነውና!" የሚለውን የምሥራች ቃል: እንለዋወጣለን:: ይህ የደስታ መንፈስና ሥርዓት: እንደዘመነ ትንሣኤ: እስከመስከረም ፳ ቀን ድረስ ይቀጥላል::

በቤተ ክርስቲያንና በቤት፥ በአደባባይና በሜዳ የሚካኼደው: ይህ: የአለባበስና የሰላምታ፥ የጸሎትና የቍርባን፥ የጠበል ጠዲቅና የመስተንግዶ፥ የጨዋታና የዘፈን ሥርዓት: በየአንዳንዱ በዓል ጊዜ የሚደረግ: ቋሚ ወግ ስለኾነ: እናንተና እኔ፥ እኛንም የመሰሉት ኢትዮጵያውያን: ኹላችን: ይኸው ባህላችን እንዳይዘነጋ: በያለንበት ጠብቀን ልንፈጽመው፥ ለልጆቻችንም እያሳወቅን ልናስተላልፈው ይገባናል::

## የኢየሱስ ክርስቶስ በዓለ ልደት::

**ጥያቄ:-** *በመስከረም ፩ ቀን ከምናከብረው: ከታላቁ በዓላችን የምናገኘው፥ ዋና ቍም ነገርም አድርገን: ከልባችን ልናስበው የሚገባን መልእክት ምን ይመስልሃል? ልታመለክተን ይቻልሃል?*

**መልስ:-** በዚህ: በመስከረም ፩ ቀን በሚውለው የበዓል ዕለት ከሚታሰቡት: ከሌሎቹ ታላላቅ ብሔራውያን ምክንያቶች፥ በተለይም: ከቅድስት ድንግል ማርያም ልደትና ከኢትዮጵያ ነጻነት ጋር ተዋሕዶ: ጥልቅ የኾነ መንፈሳዊ አንክሮንና ተዘክሮን የሚያሳድርብን: ቀዳሚው ቍም ነገር: የአምላካችን የኢየሱስ ክርስቶስ ልደት ኾኖ ይገኛል:: ይኸውም: አምላክ: ሰውን ከመውደዱ የተነሣ: ራሱን: እስከመጨረሻው ደረጃ አዋርዶ: በሰውነት መወለዱ ብቻ ሳይኾን: እንደነገሥታት ልጆች: በቤተ መንግሥት መቀማጠሉ ቀርቶበት፥ ከደኃ ሴት እንደተወለደ ሕፃንም እንኳ: በደሳሳ ጎጆ ውስጥ: መጠጊያ ማግኘት በዝቶበት: በሰውነት ኑሮ: እጅግ ዝቅ ካለው ዝቅጠት ደርሶ: በእንስሳት በረት መወለዱ ነው::

# ኢትዮጵያ እና ኢትዮጵያዊነት፤
## "ፈጣሪዬ" የምለው እግዚአብሔር፡ ማነው?

---

ለዓለማቱ ፈጣሪና ባለቤት፡ አልጋው፥ ፍራሹና ብርድ ልብሱ፥ መደቡም ቀርቶበት፥ የሚጠቀለልበትም በቂ ጨርቅ እንኳ ታጥቶ፡ የተኛው፡ በባዶው መሬት ላይ ሲኾን፥ ከበረቱ የሌሊት ብርድ ያማሟቁት፡ በበረቱ ውስጥ የነበሩት እንስሳት ናቸው። በዲያብሎስ የባርነት አገዛዝ፥ የኃጢአት ቀንበርና የሞት ፍዳ ተቀፍድዶ ይማቅቅ የነበረው ፍጥረት፡ በቃተተ ተስፋ ይጠባበቀው የነበረውን፡ የጌታን የመወለዱን ምሥራች፡ ከሰማይ መላእክት የሰሙት፡ በእልፍኝ የሚኖሩት፡ ቅምጥሎቹ የከተማ ታላላቆች ሳይኾኑ፡ ከመንጎቻቸው ጋር በሜዳ ያደሩ፡ ምስኪኖቹ የገጠር እረኞች ናቸው።

አዎን! አምላካችን፡ ስለእኛ ሲል፡ ከነእናቱ የተቀበላቸውን መከራዎች፡ መቋቋም የጀመረው፡ ገና በማሕፀን ሣለ እንሥቶ መኾኑ፡ ከዮሴፍ ጥርጣሬና ከአይሁድ ጥላቻ ጀምሮ፡ በደረሰበት እንግልት ይታወቃል፤ ከዕንሰቱ በኋላ የቀጠለው ይኸው መከራው፡ እነሆ፡ በበረትም ተከሠተ! እንግዲህ፡ ፈጣሪያችን እግዚአብሔር፡ እኛን፡ የጠፋነውን በጎቹን፡ እንደቃል ኪዳኑ ሊፈልገንና ሊያድነን የመጣው፥ ያዳነንም፡ እንዲህ አድርጎ ነው።

ታዲያ! ለዚህ ፍቅሩና መሥዋዕትነቱ የምንመልስለት ውለታ፡ ከቶ ምንድር ነው? እርሱ እንደወደደን፥ እኛም፡ እርሱን መውደድ መኾኑን፤ እርሱን መውደዳችንንም፡ የምናውቀው፡ ጠላቶቻችንን ሳይቀር፡ ሰውን ኹሉ ስንወድድ መኾኑን ነግሮናል። ይህን ትሩፋት ማድረግ የምንችለው፡ እግዚአብሔርንና ሰውን ያስታረቀ፥ ሥጋንና ነፍስንም ያስማማ፡ እውነተኛ ሰላማችን፡ እርሱ፡ ኢየሱስ ክርስቶስ፡ ቅዱስ መንፈሱን፡ በሰውነታችን ውስጥ ያሳድር ዘንድ፡ የየልቦናችንን በር እያንኳኳ ነውና፡ ስንከፍትለት ብቻ ነው። ስለዚህ፡ እንክፈትለት እንጂ፡ "እንቢ!" አንበለው! እያንዳንዳችንንም፡ በየስማችን እየጠራን ነውና፡ "አቤት!" ብለን፡ ፈቃዱን እንፈጽም!

### የድንግል ማርያም በዓለ ልደት።

ጥያቄ:- *በዚሁ በዓል ላይ አብረን ስለምናስበውና ስለምናከብረው፡ ስለቅድስት ድንግል ማርያም ልደት፡ በዚህ መልኩ የምትገልጽልን፡ ተጨማሪ፥ ወይም፡ ልዩ ቍም ነገር ሊኖርህ ይችል ይኾን? ካለህ፡ እባክህ ብታካፍለን?*

መልስ:- አዎን! ከዚህ በዓል ጋር አብሮ ስለሚታሰበው፡ ቀደም ብሎ ስለተጠቀሰው፡ ስለቅድስት ድንግል ማርያም፡ የልደቷ በዓል፡ እዚህ ላይ ሊታወስ የሚገባው ተጨማሪ ቍም ነገር አለኝ፤ እንኳንም ጠየቃችሁኝ እንጂ፡ ደስ ብሎኝ፡ እንደሚከተለው እገልጽላችኋለሁ።

እርግጥ፡ የእርሷ ልደት፡ እንደልጇ ልደት ኹሉ፡ በውጪ፡ በሊባኖስ ተራራ ላይ፡ በዛፍ ሥር መኾኑ፡ በልጇ ልደት፡ ኋላ፡ በበረት የተከሠተውን፡ ታላቁን የመለኮት ምሥጢር፡ ቀደም ብሎ፡ በእርሷ ልደት፡ ፍንጩን አሳይቷል። ይህም የኾነው፡ በጠቅላላ፡ ስለክርስቶስ፥ በተለይም፡ ቅድሚያ ስላለው፡ ስለትስብእቱና ስለልደቱ የተነገረው ትንቢት ኹሉ፡ ለመጨረሻው ፍጻሜ እንዲበቃ ለማድረግ የሚያስችለውን መሠረት ለመጣል ነበረ።

# ምዕራፍ ፲፤ በዓል:: ዓበይትና ንዑሳን በዓላት::

## ርእሰ ዐውደ ዓመት፤ የኢየሱስ ክርስቶስ በዓለ ልደት::

### የድንግል ማርያም በዓለ ልደት::

---

ይኸውም: የድንግል ማርያም ወላጆች፥ አያቶች እና/ወይም ቅድመ አያቶች: የልጃቸው ቀዳሚት አርአያ የኾነችውን: የንግሥተ ሳባን ፈለግ በመከተልና ከኖኅ ጀምሮ: በኢትዮጵያውያን ዘንድ: ሲወርድ ሲዋረድ የተለመደውን ሃይማኖታዊ ጉዞ: የትውልድ ግንዳቸው መልከ ጼዴቅ ወደቈረቈራት: ቅድስት ሀገር: ወደኢየሩሳሌም በማድረግ ያረጋገጡት ነው::

ቅድስት ድንግል ማርያም: ገና: በእናቷ በሐና ማሕፀን ውስጥ ተፀንሳ ሣለች: ሕሙማንን በመፈወስ ብዙ ተአምር ታደርግ ስለነበረ: ያን ኹሉ ተአምራት የተመለከቱ አይሁድ: ለምቀኝነት አያርፉምና: በኢትዮጵያውያኑ: ኢያቄምና ሐና ላይ: ታላቅ ቅንዓት አደረባቸው፤ "ቀድሞ: ከእነዚህ ወገን የሚኾኑ: 'ዳዊት: ሰሎሞን':- አርባ አርባ ዘመን: እንደሰም አቅልጠው፥ እንደገል ቀጥቅጠው ገዙን፤ ደግሞ: ከዚህች የተወለደ: እንደምን ያደርገን ይኾን?" ብለው: በጠላትነት ተነሡባቸው::

በዚህ ጊዜ: የእግዚአብሔር መልአክ: ኢያቄምን: "ወደሊባኖስ ተራራዎች: ይዘሃት ሂድ!" ብሎት: ወደዚያ ኼደው: ሐና: እመቤታችን: ድንግል ማርያምን: በዚያ የተራራ ዛፎች ሥር ወልዳታለች! በዚህም: *"እምሊባኖስ: ትወፅእ መርዓት!": ማለትም: "ሙሽሪት: ከሊባኖስ ትወጣለች!"* የሚለው ትንቢት ተፈጸመ::

የእርሷ ልደት: በሊባኖስ ተራራ: በዛፍ ሥር፤ የልጇ የኢየሱስ ክርስቶስም ልደት: በቤተ ልሔም: በከብቶች በረት፥ እንዲሁም: በጻድቁ ዮሴፍ የተጠበቀው ምድራዊ መጠለያቸው: በናዝሬት ዋሻ መኾኑ: ለዚያ ሃይማኖታዊ ጉዟቸውና ለመጻተኛ ኑሮአቸው እውነተኛነት: በቂ ማስረጃ ኾኖ ይመሰክራል:: "ዮሴፍ" የሚለው ስም: በግብፅ ስደተኛ ኾኖ ከኖረው: ከመጀመሪያው ዮሴፍ ወዲህ: ለስደተኛ ግለሰብ የሚሰጥ መኾኑ: እዚህ ላይ ሊጤን ይገባዋል::

በዚህ መልክ: በመስከረም ፩ ቀን የጀመርነውን የምሕረቱን ዓመት ሥጋዊና ነፍሳዊ ጉዞ: ወደፊት: በየመልካቸው እንደምናስተናግዳቸው እንደሌሎቹ ምግባሮቻችን ኹሉ: በእውነተኛው መንፈሳዊ አምልኮታችን አካኺደን ለፍጻሜ የምናበቃው ሊኾን ይገባል:: ይህም ማለት: በዚህ ጉዞ: እግዚአብሔር: ይህን ዓለም ሲፈጥር: ለሰው ልጆች ሥጋዊ ሕይወት: አስፈላጊ የኾኑትን: ከፀሓይ አንሥቶ: እስከነፋስ፥ ውኃና መሬት ድረስ ያሉትን መሠረታውያን ነገሮች፥ ከእነዚህ የሚገኙትንም: የሚንቀሳቀሱትንና የማይንቀሳቀሱትን ረቂቃንና ግዙፋን ፍጥረታት: አትረፍርፎ መስጠቱ ይታሰብበታል ማለት ነው፤ ይህ ብቻ አይደለም፤ ከዚህ ጋር ደግሞ: እኒሁ የሰው ልጆች: በመንፈሳዊ ሕይወታቸው ረገድ: የሚያስፈልጋቸውን ኹሉ: እንዲሁ: ምንም ሳይቀረው: ያሟላላቸው መኾኑ ብቻ ሳይኾን: በጠቅላላ: ለሥጋዊውና ለመንፈሳዊው መልካም ህልውናቸው: ጠንቅ የኾኑት: የክፋት ኃይላት፥ ኃጢኣትና ሞት: በመጨረሻ: በኢየሱስ ክርስቶስ ሰው መኾን አስወግዶላቸው: የዘለዓለም ድል አድራጊነት ጸጋን ያስገኘላቸው መኾኑን በመገንዘብና በማስታወስ ጭምር ሊኾን ይገባል ማለት ነው::

# ኢትዮጵያ እና ኢትዮጵያዊነት፤
## "ፈጣሪዬ" የምለው እግዚአብሔር፡ ማነው?

---

እንግዲህ፡ እያንዳንዱ በዓል፡ እውነተኛ ኹኖ፡ ለእየራሳችን እርካታን የምናተርፍበት፥ በፈጣሪያችንም ፊት ሞገስን የምናገኝበት፡ በዚህ መልክ ስናከብረው መኾኑን፡ በብርቱ ልትገነዘቡት ይገባችኋል።

*ጥያቄ፡-* *"ድንግል ማርያም፡ ከኢትዮጵያ፡ ወደእሥራኤል ምድር የኼደችው፡ በትንቢቱ መሠረት፡ ኢየሱስ ክርስቶስን፡ የይሁዳ ክፍል በኾነችው፡ በቤተ ልሔም ልትወልደው ነው!" ስለሚለው እምነት፥ በመሠረቱም፡ ስለእርሷ ኢትዮጵያዊነትና እግዚአብሔር ወልድ፡ ከእርሷ፡ በኢትዮጵያዊነት ስለመወለዱ፡ ከዚህ አስቀድሞ ከተረዳነው ጋር፡ እዚህ ላይ፡ በተጨማሪ የምትሰጠን ማብራሪያ ይኖራል ን?*

*መልስ፡-* ለዚህ ጥያቄያችሁ፡ መልስ የኾነውን ማብራሪያ፡ ቀደም ብለው ታትመው፡ ለንባብ በበቁት፡ "ኢትዮጵያዊው፡ በማንነቱ ፍለጋ!"፥ "ኢትዮጵያ፡ የዓለሙ መፋረጃ!" እና Ethiopia: The Classic Case በተባሉት መጻሕፍቴ ውስጥ አግኝታችሁታል ብዬ አምናለሁ፡ ያን መሠረት በማድረግ፥ ከዚያ የቀሩ ቁም ነገሮች ቢኖሩም፡ እነዚያን ጨማምሬ፡ ከዚህ የሚከተለውን ሐተታ፡ አሳጥሬና አጠቃልዬ አቀርብላችኋለሁ፤ እነርሱም፡ እግዚአብሔር፡ ሰው ኾኖ፡ ፍጥረቱን ሊያድንበት ያዘጋጀውን መለኮታዊ ሥራ፡ እውን የሚያደርገው፡ እንዴትና በምን እንደኾነ፡ ለሰው ልጆች፡ በተለይም ላመኑበት ወገኖቹ፡ ይልቁንም፡ የቃል ኪዳን ልጆቹ ለኾኑት፡ ለኢትዮጵያውያን፡ እያከታተለ የገለጣቸው፡ የቅድሚያ ሰዑብ ድንቅ ሥራዎቹ ሲኾኑ፡ እነሆም፡ በተራቸው፡ የተሰፋው ፋናና ማጽኛ፡ መፈጸሚያና ማኅተም ለኾነችው፡ ለቅድስት ድንግል ማርያም፡ ጥላና ምሳሌ፡ አርአያና ምልክት ኾነው አገልግለውታል፦

፩ኛ፡ ገና በፍጥረት መጀመሪያ፡ *"እግዚአብሔር አምላክም፡ እባቡን (ዲያብሎስን) አለው ይህን ስላደረግህ፡ ...በአንተና በሴቲቱ* (በሔዋን) *መካከል፡ በዘርህና በዘርዋ* (ከድንግል ማርያም በሚወለደው ልጅ) *መካከል፡ ጠላትነትን አደርጋለሁ፤ እርሱ* (ኢየሱስ ክርስቶስ)፡ *ራስህን ይቀጠቅጣል፡ አንተም፡ ሰኰናውን ትቀጠቅጣለህ።"* ይህ የኾነው፡ አዳምና ሔዋን በተፈጠሩባት፡ እግዚአብሔር፡ ከሰው ልጆች ጋር ላደረጋቸው፡ ለሰባቱ ቅዱሳት ኪዳናት መሠረት የኾነው፡ የአዳምና ሔዋን የጋብቻ ቃል ኪዳን በተፈጸመባት፥ የዔዶም ገነት በምትገኝባትና ለአራት ከሚከፈለው ወንዟ፡ አንዱ የኾነው፡ "ግዮን" በከበባት፡ በዚችው፡ በኢትዮጵያ ምድር ስለኾነ፡ የሰው፡ ማንነቱ የሚታወቀው ደግሞ፡ በተወለደባት ምድር በመኾኑ፤ የድንግል ማርያም ኢትዮጵያዊነት፡ የተረጋገጠበት የመጀመሪያው ማስረጃ ይህ ነው።[፪፻፬]

፪ኛ፡፥ የእግዚአብሔር ወገኖች የኾኑት፡ ደጋጎቹ አባቶችና እናቶች፡ እስከጥፋት ውኃ ድረስ፡ በኢትዮጵያ ኖረው፡ በኖኅና በቤተሰቡ አማካይነት፡ ከጥፋት ውኃ የዳኑባት፡ የውኃ ኾነ የነፋስ መቅዘፊያና ሰብአዊ ቀዛፊ ሳይኖራት፡ በመለኮት ኃይል ብቻ ተጠብቃ የተመራችው መርከብ፡ እኛ ኢትዮጵያውያን፡ "ድንግል ማርያም ናት!" እንላለን።

## ምዕራፍ ፺፤ በዓል። ዓበይትና ንዑሳን በዓላት።
## ርእሰ ዐውደ ዓመት፤ የኢየሱስ ክርስቶስ በዓለ ልደት።
### የድንግል ማርያም በዓለ ልደት።

---

በመጨረሻም፡ ኖኅና ቤተሰቡ፡ በኋላ ዘመን፡ በመልከ ጼዴቅ ተቈርቍሮ፡ ሰው የሚኾነው አምላክ፡ ዓለሙን ለማዳን እንዲሰቀልባት ወደተመረጠችው፡ ወደኢየሩሳሌም ከተማ፡ የመጀመሪያዋን የደኅንነት ጉዞ ፈጽመውና ከሞት ተርፈው፡ ከእግዚአብሔር ጋር፡ ላደረጉት ቃል ኪዳን፡ ምልክት የኾነችው ቀስተ ደመና፡ "ድንግል ማርያም ናት!" ብለን እንናገራለን። ከዚህ የተነሣ፡ የጋብቻውን ቃል ኪዳን፡ ፍሬያማው አንድነታችን፡ መርከቧን፡ ቤተ መቅደሳችን/ቤተ ክርስቲያናችን፡ "የማርያም መቀነት" የምንለውንም የቀስተ ደመና ምልክት፡ ሰንደቅ ዓላማችን አድርገንና በፊትል ጥልፍ ቀሚሳችን በተዋበ የሴት ወገቧ ላይ አስታቀን፡ "እናት አገራችን ኢትዮጵያ" በሚል ስሟ፡ የምናውቃት፡ የምንጠራትና የምንሥላት መኾናችን፡ ይህ፡ ኹለተኛው ማስረጃ ነው።

፫ኛ፡ እግዚአብሔር፡ ሙሴን፡ ወደግብፅ ልኮት፡ የእሥራኤልን ልጆች፡ ከፈርዖን ባርነት፡ ነጻ ከማውጣቱ በፊት፡ በቅድሚያ፡ ወደኢትዮጵያ እንዲመጣና ኢትዮጵያዊት ሚስት አግብቶ፡ በዚያ፡ እንደእሥራኤላውያን ልማድ፡ ብዙ ሚስቶችን በማግባት ሳይኾን፡ በእግዚአብሔር ሕግ መሠረት፡ በአንዲት ሚስት ተወስነው እንደሚኖሩት፡ እንደኢትዮጵያውያን ሥርዓት፡ ለብዙ ዓመታት÷ እስከመጨረሻውም፡ በእርሷ ብቻ ተወስኖ እንዲኖር ለምን አደረገ? መለኮታዊ ምክንያት አለው። ሙሴ፡ የኢየሱስ ክርስቶስ ቀዳሚ ምሳሌና አርአያ ሲኾን፡ የኢትዮጵያዊው ካህን፡ የዮቶር ልጅ የኾነችው ሚስቱ ሲፓራ ደግሞ፡ የድንግል ማርያም ቀዳሚት ምሳሌና አርአያ መኾኗን ጭምር ሊያሳይ በመኾኑ፡ ይህ እውነታ፡ የድንግል ማርያምን ኢትዮጵያዊነት ለማሳየት፡ ሦስተኛው ማስረጃ ነው።

፬ኛ፡ ከአዳምና ሔዋን ጀምሮ፡ እስከ ሙሴ ዘመን ድረስ፡ በኪዳነ ልቦና ጸንቶ የቆየው የዐሥሩ አምላካውያት ትእዛዛት ሕግ፡ በኢትዮጵያውያን የልብ ጽላት ላይ ተጽፎ እየተሠራበት ሳለ፡ በሙሴ መሪነት፡ ከግብፅ ባርነት፡ ነጻ የወጡት እሥራኤላውያን ግን፡ በታላቅ ኃይሉ፡ ነጻ ያወጣቸውን፡ የአባቶቻቸውን፡ የአብርሃምን÷ የይስሐቅንና የያዕቆብን አምላክ፡ እንደኢትዮጵያውያኑ፡ በዚያው፡ በኪዳነ ልቦና፡ በእውነትና በመንፈስ ሊያመልኩት ባለመፈለጋቸው÷ ከዚህ ይልቅ፡ በክህደትና በዓመፅ ተነሣሥተው፡ በጣዖት የማምለክ ዝንባሌን ስላሳዩ፡ እግዚአብሔር፡ ያን ሕጉን፡ በኹለት የድንጋይ ጽላት (ሰሌዳዎች) ላይ፡ በጣቶቹ ጽፎና በታቦት (በማኅደር) አድርጎ፡ እንደሰጣቸው ይታወቃል።

ይኹን እንጂ፡ እነርሱ፡ በቃል ኪዳኑ ሕግ ውስጥ ያሉትን ትእዛዛት መፈጸም አቅቷቸው ስላፈራረሷቸው÷ ከዚህም የተነሣ፡ የኃጢአታቸው ጽዋ ስለሞላ፡ እነርሱና አገራቸው፡ በአረማዊው ናቡከደነጾር እንዲደመሰሱ፡ ከአምላካቸው ተወስኖ ኖሮ፡ ያ፡ ታላቅ ጥፋት ከመድረሱ በፊት፡ ያች፡ እነዚያን ጽላት የያዘችው ታቦተ ሕጉ፡ ወደኢትዮጵያ መምጣቷና *"ቃል ሥጋ ኾነ!"* እንደሚለው እንደወንጌላዊው ዜና፡ የአምላክ ሰው መኾን፡ በእውንነት እስከተፈጸመበት ጊዜ ድረስ፡ በኢትዮጵያ መኖርዋ እርግጥ ነው።

# ኢትዮጵያ እና ኢትዮጵያዊነት፤
## “ፈጣሪዬ” የምለው እግዚአብሔር፡ ማነው?

ጽላቱ፡ ሰውነትን፡ ማለትም፡ ነፍስንና ሥጋን ከድንግል እናቱ በተዋሕዶ የለበሰው የአምላካችን፡ የኢየሱስ ክርስቶስ፥ ጽላቱን የያዘችው ታቦትም፡ የቅድስት እናቱ ምሳሌዎች በመኾናቸው፡ ኢየሱስ ክርስቶስን የወለደችው ድንግል ማርያም፡ ከኢትዮጵያ ምድር የተገኘች ኢትዮጵያዊት ለመኾኗ፡ ይህ፡ አራተኛው ማስረጃ ነው።

፭ኛ፦ እግዚአብሔር፡ ኢትዮጵያዊቷ ንግሥት ማክዳ፡ በዚያ ጥንታዊ ዘመን፡ ያን የመሰለ አታካችና አዳጋች ጉዞ ወደኢየሩሳሌም እንድታደርግ ለምን ፈቀደ? *“ከወገብህ የሚወጣውን ዘርህን፡ ከአንተ በኋላ አስነሣለሁ! ...የመንግሥቱንም ዙፋን፡ ለዘለዓለም አጸናለሁ፡ እኔም፡ አባት እኾነዋለሁ፡ እርሱም፡ ልጅ ይኾነኛል።”* ብሎ፡ “ልበ አምላክ” ለተባለው፡ ለቅዱስ ዳዊት፡ የገባለትን ቃል ኪዳን ሊፈጽም አይደለምን? እነሆ፡ ንግሥት ማክዳ፡ ይህ፡ መለኮታዊ የተስፋ ቃል፡ “የዳዊት ልጅ!” በተባለው፡ በኢየሱስ ክርስቶስ የተፈጸመበትን፡ የእግዚአብሔርን ልጅ የወለደች፡ ድንግል ማርያምን ያስገኘውን፡ የቃል ኪዳን ዘር፡ ከንጉሥ ሰሎሞን ተቀብላ (ፀንሳ)፡ ወደአገርዋ፡ ወደኢትዮጵያ ተመለሰች።

እንግዲህ፡ በኢየሩሳሌም የነገሠው፡ የነቢዩ ዳዊት ልጅ፡ እሥራኤላዊው ንጉሥ ሰሎሞን፡ የኢየሱስ ክርስቶስ ቀዳሚ ምሳሌና አርአያ ሲኾን፡ የመልከ ጼዴቅ ዘር የኾነችው፡ ኢትዮጵያዊቷ ንግሥት ማክዳ ደግሞ፡ የድንግል ማርያም ቀዳሚ ምሳሌና አርአያ ናት፡ ይህም፡ *“ንግሥተ ዓዜብ፡ [ኢትዮጵያ] በፍርድ ቀን፡ ከዚህ ትውልድ ጋር ተነሥታ ትፋረደዋለች፡ ታሳፍረዋለችም፡ የሰሎሞንን ጥበብ ለመስማት፡ ከምድር ዳርቻ መጥታለችና። እነሆም፡ ከሰሎሞን የሚበልጥ ከዚህ አለ!”* በሚለው፡ በራሱ በጌታ ቃል ተረጋግጧል።

ስለዚህ፡ ይህ፡ የንግሥተ ሳባ ኢትዮጵያዊነትና በእርሷ የተፈጸመው፡ መለኮታዊ ዕቅድ፡ ድንግል ማርያም፡ ኢትዮጵያዊት ለመኾኗ፡ አምስተኛው ማስረጃ ነው።

፮ኛ፦ *“ኢትዮጵያ ታበጽሕ እደዊሃ ኀበ እግዚአብሔር!”* ማለትም፡ *“ኢትዮጵያ፡ እጆቿን፡ ወደእግዚአብሔር ትዘረጋለች!”* ተብሎ፡ በአምላካዊ ቃል የተነገረላት ሰብአዊት ፍጡር፡ ድንግል ማርያም ካልኾነች በቀር፡ ሌላ፡ ከቶ፡ ለማን ሊኾን ይችላል? መቼም፡ ቃሉ፡ ምድርን፡ አገርን፡ ወይም ግዑዝ አካልን የመሰለ፡ ሌላ ነገርን የሚወክል አይደለም፤ እንደቃሉ አነጋገር፡ የምትዘረጋቸው እጆች ያሏት፡ ለዘለዓለምም፡ ሕያውት ኾና፡ በምድር ላይ፡ በሰብአዊት ሴት አንቀጽ፡ “ኢትዮጵያ” በሚል ስሟ ስትጠራ የምትኖር፡ እጆቿን ወደእግዚአብሔር ዘርግታ፡ መልካሙን ዘለዓለማዊ ምላሽ፡ ከፈጣሪዋ ያገኘች፡ ሰብአዊት ፍጡር፡ ከድንግል ማርያም በቀር፡ ሌላ ፍጡር ሊኖር አይችልም።

## ምዕራፍ ፮፤ በዓል፡፡ ዓበይትና ንዑሳን በዓላት፡፡
## ርእሰ ዐውደ ዓመት፤ የኢየሱስ ክርስቶስ በዓለ ልደት፡፡
### የድንግል ማርያም በዓለ ልደት፡፡

---

አዎን፡ በመላው የሰው ልጆችና በፍጥረቱ ኹሉ ስም፡ እጆቿን፡ ወደእግዚአብሔር ዘርግታ፡ በፍጹም ብቅዓት ያቀረበችው ልመና፡ ከሥሉስ ቅዱስ መንበረ ጸባዖት ደርሶ፡ የቅዱሱ ኪዳን የመጨረሻ ማኅተም የኾነውን የምሕረት ቃል ኪዳን ኢየሱስ ክርስቶስን ያስገኘችው፡ ያች "ኢትዮጵያ"፡ ድንግል ማርያም ለመኾኗ፡ ይህ፡ ስድስተኛው ማስረጃ ነው፡፡

፯ኛ፡ *"የእሥራኤል ልጆች ሆይ! እናንተ፡ ለእኔ፡ እንደኢትዮጵያ ልጆች አይደላችሁምን? ይላል እግዚአብሔር፡፡"* የሚለው፡ የነቢዩ ቃል፡ በመጀመሪያ፡ ስሙ፡ "እሥራኤል" የኾነ፥ ብዙዎች ልጆችም ያሉት ሰው መኖሩን ያመለክተናል፡፡ ታዲያ፥ እርሱ ማነው? ሰብአዊ ፍጡር የኾነው፡ በወንድ አንቀጽ የሚጠራው፡ የአብርሃም ልጅ የይስሓቅ ልጅ፡ የዔሳው መንትያ፡ ያዕቆብ አይደለምን? "እሥራኤል"፡ ቀድሞ፡ የእግዚአብሔር ወልድ፡ ኋላም፡ የኢየሱስ ክርስቶስ ስም መኾኑ፥ ይህንም ስም ለያዕቆብ የሰጠው፡ እርሱ ራሱ የስሙ ባለቤት መኾኑ ይታወቃል፡፡

ይኸውም፡ ቀድሞ፡ በብሉይ ኪዳን፡ *"ከእንግዴህ ወዲህ፡ ስምህ፡ 'እሥራኤል' ይባል እንጂ፡ ያዕቆብ አይባል! ከእግዚአብሔር፥ ከሰውም ጋር ታግለህ፡ አሸንፈሃልና!"* ተብሎ የተጻፈው ቃል፥ ኋላም፡ *"እሥራኤል፡ ሕፃን በነበረ ጊዜ ወደድሁት፤ ልጄንም፡ ከግብፅ ጠራሁት፡"* ተብሎ፡ በሙሴ መሪነት፡ ከግብፅ ባርነት ነጻ በወጡት የእሥራኤል ሕዝብ በማስመሰል፡ በነቢዩ የተነገረው ትንቢት፡ በኢየሱስ ክርስቶስ የተፈጸመ በመኾኑ ነው፡፡ አዎን! ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ፡ በሕፃንነቱ፡ ከእናቱ፡ ድንግል ማርያም ጋር፡ ወደግብፅ ተሰድዶ፥ እዚያም፡ የኢትዮጵያውያን ርስት በኾነው፡ በቍስቋም ገዳምና በኢትዮጵያ፡ ቆይቶ፡ ከሦስት ዓመት ተኩል በኋላ ወደናዝሬት ስለመመለሱ፡ የአዲስ ኪዳኑ ባለምሥራች ሲጽፍ፡ ይህንኑ፡ *"ልጄን፡ ከግብፅ ጠራሁት!"* የሚለውን ቃል እንደጠቀሰው ይታወሳል፡፡

እንግዴህ፡ ስለ"እሥራኤል" የተነገረው፡ ያ የእግዚአብሔር ቃል፡ ቀደም ብሎ፡ በ፯ኛው ተራ ቁጥር የተጠቀሰው፡ "ኢትዮጵያ" የሚለው ስያሜ፡ ለማን ሊሰጥ እንደሚገባ፥ ለማንስ እንደተሰጠ ያመለክተናል፡፡ ይኸውም፡ "እሥራኤል" የተባለውን አምላክ፡ ለወለደችው፡ ለድንግል ማርያም፡ የተሰጠ መኾኑን ነው፡፡ ይህን እውነታ ለመረዳት፡ *"የእሥራኤል ልጆች ሆይ! እናንተ፡ ለእኔ፡ እንደኢትዮጵያ ልጆች አይደላችሁምን? ይላል እግዚአብሔር፡፡"* የሚለውን፡ የራሱን የነቢዩን ቃል በማስተዋል መመልከቱ ይበቃል፡፡

አዎን! እግዚአብሔር፡ እርሱን በአምላክነቱ ፈልገው ላመኑበትና ለወደዱት፥ ቃሉንም ለጠበቁት ወላጆቻቸው፡ ለአብርሃምና ለይስሓቅ፥ ለራሱም ለያዕቆብ የሰጣቸውን ቃል ኪዳን በማጽናት፡ ስለስሙና ስለእነርሱ ፍቅር ሲል፡ በኋላ ዘመን፡ ልጆቻቸውን፡ የእግዚአብሔር ሕዝብ ሊያደርጋቸው ስለፈለገ፡ "እሥራኤል" የሚለውን ስም እንደሰጣቸው ኹሉ፡ እንዲሁ፡ በቀደመው ዘመን፡ ከእነርሱ፡ ከእሥራኤል ልጆች ይልቅ፡ አስቀድመው ላወቁት፥ ላመኑበትና ለወደዱት፥ ቃሉንም ጠብቀው ለኖሩት ኢትዮጵያውያን ደግሞ፡ እርሱን ለመውለድ በምትበቃው እናቱ ስም፡ የእርሷ ልጆች ተብለው እንዲጠሩ ፈቃዱ ኾነ ማለት ነው፡፡

# ኢትዮጵያ እና ኢትዮጵያዊነት፤
## "ፈጣሪዬ" የምለው እግዚአብሔር፡ ማነው?

---

ስለዚህ፡ ቀደም ብሎ ከተሰጠው ማብራሪያ ጋር፡ የራሱ የነቢዩ ቃል፡ "እሥራኤል" የሚለው ስም፡ ኢየሱስ ክርስቶስን የሚመለከት፥ "ኢትዮጵያ" የሚለው ስያሜ ደግሞ፡ ድንግል ማርያምን የሚያመለክት መኾኑን፥ እንዲሁም፡ እግዚአብሔር፡ ከእሥራኤላውያን ይልቅ፡ አስቀድሞ ያወቀውና የወደደው፡ ኢትዮጵያውያንን መኾኑን፡ በግልጽ ስለሚያረጋግጥ፡ ድንግል ማርያም፡ "ኢትዮጵያ" ለመኾኗ፡ ይህ፡ ሰባተኛው ማስረጃ ይኾናል።

ቀደም ብለው የተጠቀሱትን ማስረጃዎች የሚያጠናክሩ፡ ሌሎች፡ የገዘፉ እውነታዎችን፡ እዚህ ላይ ማከል ይቻላል። ከእነዚህ መካከል፡ አንዱን ብቻ ልጥቀስላችሁ! ድንግል ማርያምን፡ በሥጋ ጭምር የምንዛመዳት በመኾኗ፡ "እናታችንና ንግሥታችን፥ ሃይማኖታችንና አገራችንም ናት!" ብለን፡ በስሟ፡ አገራችን፡ "ኢትዮጵያ"፥ እኛም፡ ልጆቿ፡ "ኢትዮጵያውያን" ተብለን እንደምንጠራ ኹሉ፡ ልጇን ኢየሱስ ክርስቶስንም፡ "ፈጣሪያችንና አምላካችን፡ አባታችንና መድኃኒታችን፡ ብቻ ሳይኾን፡ "ካህን፡ ሊቀ ካህናታችን፥ ንጉሥ፡ ንጉሠ ነገሥታችንም ነው!" ብለን፡ የነፍሳችንና የመንፈሳችን ብቻ ሳይኾን፡ የሥጋችንም ጌታና ባለቤት መኾኑን፡ ለዓለሙ ኹሉ፡ በይፋ ያረጋገጥንበት ብሔራዊ አቋማችን ይገኛል። ያም፡ "ሞዐ አንበሳ፡ ዘእምነገደ ይሁዳ!" የሚለውን መለኮታዊ ዓርማ፡ ብሔራዊ ማንተማችንና በሰንደቅ ዓላማ ላይ አሥፍረን፡ ማዕከላዊ ምልክታችን በማድረጋችን ታውቋል።

መቼም፡ በሰብአዊው የሥጋ ዝምድና ሓረግ፡ በቀጥታ ያልተሣሠረውን ማንንም ሰው፡ በግዴታና በኃይል ካልኾነ በቀር፡ በፈቃዱ አምጥቶና ተቀብሎ፡ በራሱ ላይ የሚያነግሥ ወገን፡ ወይም ሕዝብ፡ በምድር ላይ ስለሌለ፡ ኢትዮጵያውያንም፡ በሥጋ ዝምድና የተሣሠሩ ባይኾኑ ኖሮ፡ ኢየሱስ ክርስቶስን፡ ንጉሣችን፥ እናቱን፡ ድንግል ማርያምንም፡ ንግሥታችን ብለው፡ በፍጹም ሃይማኖታዊ ፈቃደኛነትና ደስታ፡ በላያቸው ሊያነግሡዋቸው፥ መንግሥታቸውንም፡ የራሳችን ብለው ሊተዳደሩበት ባላደረጉም ነበር።

ይህን እውነታ፡ በንጽጽር አቅርቦ ለማሳወቅ፡ ርቆ ኼዶ፡ ሌላ ማረጋገጫን መፈለግና ማቅረብ አያሻም፤ አረማዊው ጲላጦስ፡ ኢየሱስ ክርስቶስን፡ በአደባባይ፡ በፊታቸው አቁሞ፡ *"ንጉሣችሁን ልስቀለውን?"* ብሎ፡ የአይሁድን ካህናትና ሕዝቡን በጠየቃቸው ጊዜ፡ *"ከቄሣር በቀር፡ ሌላ ንጉሥ የለንም!"* ብለው የሰጡት ቁርጥ ምላሽ ይበቃል፤ ደግሞም፡ እኒሁ አይሁድ፡ ወንጀሉ ተገልጾ እንዲጻፍበት በፈለጉበት፡ የመስቀሉ ዓናት ላይ፡ ጲላጦስ፡ *"የአይሁድ ንጉሥ፡ የናዝሬቱ ኢየሱስ!"* የሚል ቃልን በማስጻፉ፡ እንደገና፡ *"ራሱ፡ "እኔ የአይሁድ ነኝ! አለ፤" ብለህ ጻፍ እንጂ፡ "እርሱ፡ የአይሁድ ንጉሥ ነው!" ብለህ አትጻፍ!"* ያሉት ጥያቄያቸውና እርሱም፡ ለዚሁ ጥያቄያቸው፡ *"እኔ፡ የጻፍሁትን ጽፌአለሁ!"* ሲል የሰጣቸው ቁርጥ መልስ፡ የእውነታውን ንጽጽር፡ የበለጠ ያጎላዋል።

## ምዕራፍ ፮፡ በዓል:: ዓበይትና ንዑሳን በዓላት::
## ርእሰ ዐውደ ዓመት፤ የኢየሱስ ክርስቶስ በዓለ ልደት::
### የድንግል ማርያም በዓለ ልደት::

---

አይሁድ፡ በኢየሱስ ክርስቶስ ላይ ያላቸው የጥላቻ ተቃውሞ፡ ይህን በመሰለ ኹኔታ ተገልጾ የታየው፡ እርሱ፡ ጌታችን፡ የሞት ፍርዱን በተቀበለበት ጊዜ ብቻ አልነበረም፤ ገና፡ ቀደም ብሎ፡ በኢየሩሳሌም ቤተ መቅደሳቸው ውስጥ እያስተማረ ሳለ ጀምሮ፡ ተከሥቶ ነበር፤ ያም የጥላቻ ተቃውሞ፡ ቀዳሚ ምሳሌው የኾነው ሙሴ፡ ኢትዮጵያዊት ሚስቱን አግብቶ፡ ኢትዮጵያዊ በመኾኑ፡ ከሕዝበ አይሁድ ብቻ ሳይኾን፡ ከእህቱ፡ ከማርያምና ከወንድሙ፡ ከአሮን ሳይቀር የደረሰበትን የመሰለ ነበር:: ይኸውም፡ አይሁድ፡ በኢየሱስ ክርስቶስ ላይ የነበራቸው የጥላቻ ተቃውሞ፡ ኢትዮጵያዊ መልኩን በማየት፡ ማንነቱን ከመናቃቸው የተነሣ እንደነበረ፡ ራሱ፡ ኢየሱስ ክርስቶስ፡ *"የሙሴ ሕግ እንዳይሻር ብላችሁ፡ ሰውን፡ በሰንበት የምትገርዙ ከኾነ፡ ሰውን፡ ኹለንተናውን፡ በሰንበት፡ ጤናማ ስላደረግሁ፡ ለምን ትቃወሙኛላችሁ? በእውነት ፍረዱ እንጂ፡ በሰው ላይ፡ የፊቱን መልክ አይታችሁ፡ በአድልዎ አትፍረዱ!"* ሲል፡ በአምላካዊ አንደበቱ በተናገረው ቃሉ ስለመሰከረ፡ ይህን እውነታ ማስተባበል፡ ለማንም አይቻለውም::[፻፸፰]

ጥያቄ:- *በዚህ አከራካሪ ነጥብ ላይ፡ ይህን የመሰለ አጥጋቢና ጠቃሚ መልስ ካገኘን፡ ከዚሁ ጋር የተያያዘ ለሚመስለን፡ ለሌላው ጥያቄያችን፡ ማብራሪያ ትሰጠን ዘንድ፡ ጥያቄውን፡ እዚህ ላይ ልናነሣልህ እንሻለን፡ እርሱም፡ መልአኩ፡ ቅዱስ ገብርኤል፡ ለድንግል ማርያም፡ 'እነሆም፡ ዘመድሽ ኤልሣቤጥ፡ እርሷ ደግሞ፡ በእርጅናዋ፡ ወንድ ልጅን ፀንሳለች!' ሲል የተናገረው ቃል፡ ድንግል ማርያም፡ ኤልሣቤጥን የመሰሉ፡ ሌሎች ሴቶችና ወንዶች ዘመዶች፡ በዚያ አገር ያሏት መኾኑን የሚያመለክተው እውነታ ነው፡ ታዲያ! ይህ ነገር፡ ከእመቤታችንና ከልጇ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ኢትዮጵያዊነት ጋር እንዴት ሊጣጣም እንደሚችል የሚያስገነዝብ ማብራሪያ የሚያስፈልገው አይመስልህም?*

መልስ:- በመጀመሪያ ደረጃ፡ ነቢዩ ዳዊት፡ "የሳሌም ንጉሥ" የተባለው አባቷ መልከ ጼዴቅ የቈረቈራትን "ኢየሩሳሌም"ን መነሻ አድርጎ፡ "ኢትዮጵያ" ስለተባለችው ድንግል ማርያም፡ በመዝሙሩ ሲተነብይ፡ *"የእግዚአብሔር ከተማ* (ኢየሩሳሌም) *ሆይ! ስለአንቺ የተነገረው ኹሉ፡ ዕፁብ ድንቅ ነው፤ ...እነሆ፡ ፍልስጥኤማውያን፡ ጢሮስም፡ የኢትዮጵያም ሕዝብ፡ እነዚህ፡ በዚያ ተወለዱ::"* ብሎ የተናገረው ቃል፡ ለዚህ ጥያቄያችሁ መልስ መነሻ ነው፤ ኢትዮጵያውያን፡ ጥንት፡ ከመሥራቿ አባታቸው፡ ከመልከ ጼዴቅ ጀምሮ፡ የእርሷ፡ የኢየሩሳሌም ባላባትና ባለርስት ኾነው፡ በእርሱ ስም፡ ያለማቋረጥ ሲያስተዳድሩዋት የኖሩ፥ ዛሬም እየኖሩ ያሉ ለመኾናቸው መሠረታዊው ማስረጃ ይህ መኾኑ፡ ሊታወቅ ይገባል::

"ንግሥተ ሳባ" የምትባለው፡ ኢትዮጵያዊቷ ንግሥት ማክዳ፡ ያን ኹሉ ጓዝ ይዛ፡ ወደኢየሩሳሌም ለመኼድ የቻለችው፡ ከዚሁ ባለቤትነት የተነሣ መኾኑም እንዳይዘነጋ ያስፈልጋል::

# ኢትዮጵያ እና ኢትዮጵያዊነት፤
## “ፈጣሪዬ” የምለው እግዚአብሔር፡ ማነው?

---

የአዲስ ኪዳኑ “አቤሜሌክ”፥ ወይም፡ “ባኮስ”፥ የተባለው፡ ኢትዮጵያዊው ጃንደረባ፡ “ሕንደኬ” የተባለችው የኢትዮጵያ ንግሥት ባለሥልጣን፡ በዚያን ጊዜ ጸንቶ ይሠራበት በነበረው በኦሪታዊው የኢትዮጵያውያን ሥርዓት፡ ሊሳለም ወደኢየሩሳሌም ኼዶ የተመለሰው፡ የኢትዮጵያውያን ሀብት ወደነበረው፡ ወደጋዛ መኾኑ፡ በሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ ውስጥ ተጽፎ የሚነበበው፡ ይህን እውነታ አረጋግጦ ያስረዳል።

በኹለተኛ ደረጃ፡ እኛ ኢትዮጵያውያን፡ ከክርስቶስ ልደት አንድ ሺ ዓመት በፊት፡ ታቦተ ጽዮን ወደኢትዮጵያ እስከመጣችበት ጊዜ ድረስ፡ በዚህ መልክ፡ በኢየሩሳሌም ነዋሪዎችና ተመላላሾች የነበርን ስንኾን፡ ከዚያ በኋላ፡ በታቦተ ጽዮን ባለአደራነታችን ምክንያት፡ እውነተኞቹ እሥራኤላውያን ኾነን መገኘታችን ደግሞ፡ ሌላው እውነታ ነው።

ከዚህ የተነሣ፡ በኦሪቱ ሕግና ሥርዓት አፈጻጸም በኩል፡ በሥጋዊዉ ኾነ በመንፈሳዊው፡ በሃይማኖታዊዉም ይዞታ ረገድ፡ በኢትዮጵያም፥ በኢየሩሳሌምም በነበረን ባለመብትነት፡ በኹለቱም ምድሮች፡ ያለችግር እንኖር የነበርን መኾኑ አያጠያይቅም፤ እንዲህ ከኾነ ደግሞ፡ በዚያን ጊዜ፡ እንደዛሬው ኹሉ፡ የኢትዮጵያውያን፡ በኢየሩሳሌምና በአካባቢ አውራጃዎቿ በብዛት፡ መገኘትና ነዋሪ መኾን፥ እርስ በርሳቸው ተጋብተውና ተዋልደው መኖራቸውም፡ በምንም መልኩ ሊያስደንቅ ከቶ አይችልም።

የእኔ የራሴ፡ አንዲት እኅቴ፡ ባል አግብታና ትዳር ይዛ፥ ወንዶችና ሴቶች ልጆችንም ወላልዳ፡ በኢትዮጵያ ስትኖር፡ በኢየሩሳሌም ካለን የባለርስትነት መብት የተነሣ፡ ይህንኑ ብሔራዊ መብታችንን ለማስጠበቅ በሚል ምክንያት፡ በጊዜው ለነበረው፡ የኢትዮጵያ መንግሥት ተጠሪ በመኾን፡ ከነባለቤቷና ከነልጆቿ፡ ወደኢየሩሳሌም ኼዳ ሣለ፡ በዚያ፡ እንደገና ልጆችን ወልዳ፡ ልጆቿም፡ እዚያው፡ ተጋብተውና ተዋልደው መኖራቸው፡ ለዚህ እውነታ፡ ይህችው እኅቴ፡ ምሳሌና ማስረጃ ኾና ልትቀርብ ይቻላል።

ስለዚህ፡ እንኳንስ፡ ትንቢት እያለ፡ ባይኖርም፡ እመቤታችን፡ ቅድስት ድንግል ማርያም፡ ሳትወለድ፡ ወላጆቿ፥ ወይም፡ አያቶቿ፥ ወይም ቅድመ አያቶቿ፡ ወደኢየሩሳሌም ኼደው፡ በዚያ፡ ጊዜያዊ ቆይታ፤ ዘመድ ጥየቃ፥ ወይም ጉብኝት ቢያደርጉ፥ ወይም ኑሮን ቢመሠርቱ፥ ከዚህም የተነሣ፡ የካህኑ ዘካርያስ ሚስትና የመጥምቁ ዮሐንስ እናት የኾነችውን ኤልሣቤጥን የመሰሉ፡ ብዙ ኢትዮጵያውያን ወንድሞችንና እኅቶችን፥ ኢትዮጵያውያት እኅቶችንና አክስቶችን፥ ሌሎችንም፤ የቅርብና የሩቅ ዘመዶችን አፍርተው ቢገኙ፡ አግባብና የሚጠበቅ ውጤት ከመኾኑ በቀር፡ ሌላ ትርጉም ሊሰጠው ከቶ አይቻልም።

---

እንዲያውም: "ኤልሣቤጥ" የሚለው የስም አጠራር: በዕብራውያን አይሁድ ዘንድ ስለሌለ፥ ምንም እንኳ: ወንጌላዊው ሉቃስ: የእውነተኞች ኢትዮጵያውያት መለያ በኾነው እሥራኤላዊትነቷ: *"ከአሮን ልጆች ነበረች፡"* ቢላትም: ያ ስሟ: ኢትዮጵያዊ መኾኑ: በእርሷና በድንግል ማርያም ማንነት ሊረጋገጥ ስለሚችል: ለተነሣንበት የእውነት ፍለጋ: ተጨማሪ ማስረጃ ሊኾነን ይችላል፡ ይኸውም: "ኢየሱስ" እና "ዮሐንስ" ብሎ: ለጌታችንና ለመጥምቁ: አዳዲስ ስሞችን ባወጣላቸው: በመልአኩ: በቅዱስ ገብርኤል አንደበት: ኤልሣቤጥ: የድንግል ማርያም ዘመድ መኾኗ ስለተነገረ ነው::[፻፸፱]

## በዓለ ግዝረት::

"በዓለ ግዝረት": መሢሑ ሕፃን: ከቅድስት ድንግል ማርያም: በቤተ ልሔም: በበረት ከተወለደ በኋላ: *"ስምንት ቀንም በተፈጸመ ጊዜ: ሕፃኑን ሊገዝሩት: ወሰዱት: ስሙንም: ገና በማሕፀን ሳይፀነስ: አስቀድሞ: መልአኩ እንደሰየመው: 'ኢየሱስ' አሉት::"* በሚለው የወንጌላዊው ቃል መሠረት: በ፰ኛው ቀን: "ኢየሱስ" ተብሎ: የኪዳኑ አብርሃምን ሥርዓት የፈጸመበትን ዕለት በማስታወስ የምናከብረው በዓል ነው፡ እርሱም: "በዓለ ግዝረተ ኢየሱስ" ተብሎ: በመስከረም ፰ ቀን ይከበራል::[፻፹]

እኛ ኢትዮጵያውያን: ይህን በዓል የምናከብረው: የኢየሱስ ክርስቶስን ግዝረት ለማስታወስ ብቻ ሳይኾን: ሥርዓቱን: ቀድሞም: በኪዳኑ ልቦና: ማለትም: ከአብርሃም በፊት በኖርንበት አምልኮተ እግዚአብሔር: ስንፈጽመው የቆየን፥ ኋላም: በኪዳኑ አሪቱ: በአብርሃም፥ በመጨረሻም: በኪዳኑ መንፈስ ቅዱስ ምክንያት: ያንኑ ጥንታዊ ሥርዓታችንን አጽንተን የቀጠልን መኾናችንን ለማረጋገጥ ጭምር ነው፡ በዚህም: እየራሳችን: በቅዱሱ ኪዳን ጸጋ: በነፍስ: የሃይማኖትን ግዝረት: በሥጋም: የምግባርን ግዝረትን ተቀብለን: በመንፈስ ቅዱስ አማናዊውን የእግዚአብሔር ልጅነትን ክብር የተቀዳጀን መኾናችንን እናዘክርበታለን::

## በዓለ ስምዖን

"በዓለ ስምዖን" ተብሎ: ጥቅምት ፲ ቀን የሚከበረው በዓል: ሕፃኑ ኢየሱስ: እንደኦሪቱ ሥርዓት በእግዚአብሔር ፊት ሊቆም: በአርባ ቀኑ: በእናቱ ቅድስት ድንግል ማርያም ዕቅፍ: ከመሥዋዕቱ ጋር: ወደቤተ መቅደስ የገባበትና ለስምዖን ተገልጾ የታየበትን ዕለት የሚያስታውሰን ነው:: በዚያች ዕለት የኾነውን ዜና: ከዚህ የሚከተሉት: የብሉዩና የሐዲሱ ኪዳናት መጻሕፍት ጥቅሶች ይናገሩታል::

# ኢትዮጵያ እና ኢትዮጵያዊነት፤
## "ፈጣሪዬ" የምለው እግዚአብሔር፡ ማነው?

---

*"እግዚአብሔርም ሙሴን፡ እንዲህ ብሎ ተናገረው፡- "ለእሥራኤል ልጆች፡ እንዲህ ብለህ ንገራቸው፡- 'ሴት ብታረግዝ፡ ወንድ ልጅም ብትወልድ፡ ሰባት ቀን ያህል የረከሰች ናት፡ እንደሕመምዋ መርገም ወራት ትረከሳለች። በስምንተኛውም ቀን፡ ልጁ፡ ከሥጋው ሸለፈት፡ ይገረዝ! ከደምዋም እስክትነጻ፡ ሠላሳ ሦስት ቀን ትቀመጥ! የመንጻትዋ ቀንም እስኪፈጸም ድረስ፡ የተቀደሰን ነገር አትንካ! ወደመቅደስም አትግባ! ሴት ልጅም ብትወልድ፡ እንደመርገምዋ ወራት፡ ኹለት ሳምንት ያህል፡ የረከሰች ናት፡ ከደምዋ እስክትነጻ ድረስ፡ ስድሳ ስድስት ቀን ትቀመጥ!'" እንደሚለው "እንደሙሴ ሕግ፡ የመንጻታቸው ወራት በተፈጸመ ጊዜ፡ በጌታ ሕግ፡- "የእናቱን ማሕፀን የሚከፍት ወንድ ኹሉ፡ 'ለጌታ የተቀደሰ ይባላል!' ተብሎ እንደተጻፈ፡ በጌታ ፊት ሊያቆሙት፡ በጌታም ሕግ፡- 'ኹለት ዋልያ፡ ወይም፡ ኹለት የርግብ ጫጩቶች' እንደተባለ፡ መሥዋዕት ሊያቀርቡ፡ ወደኢየሩሳሌም ወሰዱት።*

*"እነሆም፡ በኢየሩሳሌም፡ 'ስምዖን' የሚባል ሰው ነበረ፡ ይህም ሰው፡ የእሥራኤልን መጽናናት፡ ይጠባበቅ ነበር፡ ጻድቅና ትጉህም ነበረ፡ መንፈስ ቅዱስም፡ በእርሱ ላይ ነበረ፡ በእግዚአብሔር የተቀባውንም ሳያይ፡ እንዳይሞት፡ መንፈስ ቅዱስ ገልጦለት ነበር። በመንፈስ፡ ወደመቅደስ መጥቶ ሣለ፡ እናቱና ዘመዶቹ፡ እንደሕጉ ልማድ ያደርጉለት ዘንድ፡ ሕፃኑን ኢየሱስን፡ ይዘውት፡ ወደመቅደስ ባገቡት ጊዜ፡ እርሱ ደግሞ፡ በክንዱ ተቀብሎ፡ አቀፈው፡ እግዚአብሔርንም እየመሰገነ እንዲህ አለ፡- 'ጌታ ሆይ! እንደቃልህ፡ ዛሬ፡ ባሪያህን፡ በሰላም ታሰናብተዋለህ፡ ብርሃንን፡ ለአሕዛብ፡ ክብርንም፡ ለሕዝብህ፡ ለእሥራኤል ትገልጽ ዘንድ፡ በሕዝብህ ኹሉ ፊት ያዘጋጀኸውን ማዳንህን፡ ዓይኖቼ አይተዋልና።'*

*"ዮሴፍና እናቱም፡ ስለእርሱ በተባለው ነገር፡ ይደነቁ ነበር። ስምዖንም ባረካቸው፡ እናቱን ማርያምንም፡- 'እነሆ፡ ይህ፡ በእሥራኤል ላሉት፡ ለብዙዎቹ፡ ለመውደቃቸውና ለመነሣታቸው፡ ለሚቃወሙትም፡ ምልክት ተሾሟል። በአንቺ ግን፡ የብዙዎችን ሰዎች፡ የልባቸውን አሳብ ይገለጥ ዘንድ፡ በነፍስሽ፡ ሠይፍ ይገባል!' አላት።*

*"ከአሴር ወገን የምትኾን፡ የፋኑኤል ልጅ፡ ሐና የምትባል፡ አንዲት ነቢይትም ነበረች፡ እርሷም፡ ከድንግልናዋ ጀምራ፡ ከባልዋ ጋር፡ ሰባት ዓመት ኖረች፡ ሰማንያ አራት ዓመት ያህል፡ መበለት ኾና፡ በጣም አርጅታም ነበር፡ በጾምና በጸሎትም፡ ሌሊትና ቀን እያገለገለች፡ ከመቅደስ አትለይም ነበር። በዚያችም ሰዓት ቀርባ፡ እግዚአብሔርን አመሰገነች፡ የኢየሩሳሌምንም ቤዛ ለሚጠባበቁ ኹሉ፡ ስለእርሱ ትናገር ነበር።"*

እኛ ኢትዮጵያውያን፡ ዛሬ፡ ሕፃናት ልጆቻችንን፡ ወንዶቹን፡ በ፵፡ ሴቶቹንም፡ በ፹ ቀን፡ በቤተ ክርስቲያን፡ የክርስትና ጥምቀትን የምናስጠምቃቸው፡ በዚህ[፻፹፩] መሠረትና ምክንያት መኾኑን እንደተረዳችሁት ተስፋ አደርጋለሁ።

## በዓለ መስቀል::

አምላካችን ኢየሱስ ክርስቶስ: ተሰቅሎበት: ሥጋው የተቆረሰበትና ደሙ የፈሰሰበት ዕፀ መስቀል: በየዓመቱ: በመስከረም ፲፯ ቀን ታስቦ: በጥልቅ መንፈሳዊ ስሜትና በታላቅ የበዓል ሥርዓት ይከበራል::

ይኸውም: *"በክበረ ደሙ ለተቀደሰው: ለአምላካችን ለኢየሱስ ክርስቶስ መስቀል እንሰግዳለን! መስቀል: ኃይላችን ነው! መስቀል: መከላከያችን ነው! መስቀል: ቤዛችን ነው! መስቀል: የነፍሳችን መድኃኒት ነው! አይሁድ ካዱት! እኛ ግን አመንንበት! ያመንንበት እኛም: በመስቀሉ ኃይል ዳንን!"* የሚል ትርጉም ያለውን ጸሎታችንን: በግእዝ: በየዕለቱ ማለዳ ጀምረን: በቀኝ እጃችን በማማተብ: መላልሰን የምንጸልይበትንና የክርስትና ምልክታችን አድርገን ያነገብነውን መስቀል፡ እንዲሁም: የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስን መሰቀል የሚያስታውሰን በዓል ነው::

### ደመራ::

በበዓሉም ዋዜማ: "ደመራ" የሚባለው የበዓሉ መክፈቻ: በደመቀ ዝግጅትና ሥርዓት ተካኺዶ ይከናወናል:: ይኸውም: በየሰበካው ቤተ ክርስቲያን የቅጥር ውጭ አደባባይ (ማርገጃ) ላይ: የደመራው ቋሚና ተሸካሚ ይኾን ዘንድ: በጫፉ ቅርንጫፍ: የዓደይ አበባ ጉንጉን የታሠረበትን: ትልቅ እርጥብ አጣና: በመጀመሪያ አምጥተው: እንደምሰሶ ይተክሉታል፤ ከዚያ: ከየሠፈሩ የተመረጠ ኹነኛ ወይም ቀንደኛ የኾነ ሰው፥ ደግሞም: ዓቅሙ የሚፈቅድለትና ለማበርከት የሚፈልግ ማንኛውም ግለሰብ ጭምር: እርጥብና ለጋ የኾነውን የባሕር ዛፍ: በምሰሶው ዓይነት እያዘጋጀና እያመጣ: በቋሚው ላይ ይደምርበታል፤ "ደመራ" የተባለውም: ለዚህ ነው::

ሠርክ ሲደርስ: ይኸውም: ከቀትር በኋላ: ዓሥራ አንድ ሰዓት ሲኾን: ሕዝቡ ተሰብስቦና ደመራውን ከብቦ እንደቆመ: ልብሰ ተክህኖ በለበሱ ልኡካን መሪነት: ካህናቱና መዘምራኑ: መስቀልን በሚመለከት: ለበዓሉ የተመደበውን ሥርዓተ ጸሎት ያደርሳሉ:: በዚህ መሠረት: ካህኑ: *" ...መስቀለ ክርስቶስ: ቤዛነ፥ ወኃይልነ፤ አግዐዘ ጻድቃነ፥ ወኃጥአነ: እምግብርናተ ሰይጣን ጸላዒነ፡ ነሢአ ሥልጣነ እምእግዚአብሔር አምላክነ::"* ማለትም: "የክርስቶስ መስቀልማ: ከእግዚአብሔር አምላካችን: ሥልጣንን አግኝቶ: ጻድቃንንና ኃጥአንን: ከጠላታችን: ከሰይጣን የባርነት አገዛዝ: ነጻ ያወጣ: ቤዛችንና ኃይላችን ነው!" ዲያቆኑም: *"ጸልዩ: ቅድመ መስቀል! ኵልክሙ መሃይምናን: እንዘ ትእኀዝዎ በየማን፤ ወትከህድዎ ለሰይጣን፤ እስመ ተቀደሰ: በደመ መለኮት መድኀን::"* ማለትም: "ምእመናን ኹላችሁ! በቀኝ እጃችሁ እያማተባችሁና ሰይጣንን እየካዳችሁ: ባዳነን የመለኮት ደም በተቀደሰው: በክርስቶስ መስቀል ፊት ጸልዩ!" ሕዝቡም: *"ክቡር አንተ ንጉሠ ዕፀዎት መስቀል!"* ማለትም: "አንተ፥ የዛፎች ኹሉ ንጉሥ ሆይ! አዎን! ክቡር ነህ!" የሚለውን: የመስቀል ውዳሴ: በዜማ እየተቀባበሉ ያመሰግናሉ::

# ኢትዮጵያ እና ኢትዮጵያዊነት፤
## "ፈጣሪዬ" የምለው እግዚአብሔር፡ ማነው?

---

ጸሎቱ ሲያበቃ፡ *"መስቀል አብርሃ! በከዋክብት፡ አሠርገወ ሰማየ! እምኵሉሰ፡ ፀሐየ አርአየ!" ማለትም፡ "ከኹሉም ይልቅ፡ ደምቆ በሚታየው፡ በፀሐይ፥ ድምቀ፡ በከዋክብት፡ ሰማዩን እንዳስጌጠ፡ እነሆ፡ መስቀሉ፡ በዓለሙ ኹሉ አበራ!"* የሚለውን ዜማ እየዘመሩ፥ ቀጥሎም፡ ሕዝቡ፡ "እዮሃ አበባዬ! መስከረም ጠባዬ?!" የሚለውን፡ የሆታ መዝሙር፡ በመቀባበል እያሰማ፡ ደመራውን፡ ምስቶ ጊዜ ይዞራሉ:: በዚህ፡ የሥርዓተ ጸሎቱ ፍጻሜ ይኾንና፡ ወንዱ፡ የችቦ መብራቱን ሊያበራ፡ ወደየቤቱ ይኼዳል::

ወደእየቤቱ የተመለሰው ሰው፡ ችቦውን፡ ከምድጃው እሳት ለኩሶ ሲወጣ፡ በሰንቍጣጣሽ በዓል ዕለት እንዳደረገው፡ "የኅመን ምንቸት ውጣ! የገንፎ ምንቸት ግባ!" እያለ፡ በየደጃፉ መድረክ ላይ ከተረኰሰ በኋላ፡ የችቦ ፋናውን እያንቦገቦገ አምጥቶ፡ ከተቀጣጠለው የደመራው እሳት ላይ እያነጣጠረ፡ ከሩቅ በመወርወር ይጥለዋል:: የደመራው እሳት ተያይዞ፡ ነበልባሉ እየተንቀለቀለ፡ ብርሃኑ፡ የአካባቢውን ጨለማ፤ ሙቀቱም፡ የምሽቱን ብርድ ሲያስወግድለት፡ ሕዝቡ፡ በመንፈሳዊ ተመስጦ እየዘመረና በሃይማኖታዊ ስሜት እየጨፈረ፡ የደመራው፡ የመኻል ምሰሶ ኾኖ የቆመው እንጨት፡ ነድዶ እስኪወድቅ ድረስ ይቆያል::

ከዚህ በኋላ፡ ደመራው በገጠር የተደረገ ከኾነ፡ እያንዳንዱ፡ ከጓሮው፡ ወይም ከእርሻው መሬት፡ ፈጣሪው ባርኮ የሰጠው የድካሙ ፍሬ ቢኖር፡ ያንን፡ ከምስጋና ጋር ቆራርጦ ወይም ሸምጥጦ ያቀርብና፡ እሸቱን፡ በደመራው ፍሕም እየጠበሰ፡ እዚያ ካለው፡ ከቀረው ሰው ጋር ተሳትፎ ሲጨርስ፡ ወደየቤቱ ይመለሳል:: ደመራው ግን፡ እንዲሁ፡ ሲነድድ ያድራል::

በማግሥቱ ማለዳም፡ እያንዳንዱ ሰው፡ ወንዱም፥ ሴቱም፡ ወደነደደው የደመራ አመድ እየመጣ፥ ከአመዱም፡ በጣቱ እየጠቀሰ፡ የመስቀል ምልክትን፡ በየግንባሩ ላይ ካተመ በኋላ፡ ለጸሎት ወደቤተ ክርስቲያኑ ይገባል::

### የእውነተኛው መስቀል ፍለጋና ስለመገኘቱ::

ጥያቄ:- *የመስቀል በዓል፡ በእኛ፡ በኢትዮጵያውያን ዘንድ፡ በዚህ መልክ የሚከበረው፡ ለምን እንደኾነ፡ ብትገልጽልን?*

መልስ:- "ነገር ከሥሩ፥ ውኃ ከጥሩ!" እንደሚባለው፡ ስለመስቀል ታሪክ ሲወሳ፡ አዳምንና ሔዋንን በሚመለከት፡ ከዚህ የሚከተሉት ቍም ነገሮች ይጠቀሳሉ፤ ይኸውም፡ እኒህ፡ ኹለት የመጀመሪያ ሰዎች:-

፩ኛ:- የአምላክ ልጆች ኾነው፡ በቅንነት እንዲመሩበትና ለዘለዓለም ሕያዋን ኾነው፡ በገነት ተድላ እንዲኖሩበት፡ ከፈጣሪያቸው ከተሰጣቸው የእውነት ቃልና ከተጎናጸፉት መልካም ሕይወት ይልቅ፡ ዲያብሎስ ከተባለው የሐሰት አበጋዝ የቀረበላቸውን የጥፋት ምክር፡ በራሳቸው ምርጫ ተቀብለው፡ በክፋት ዓለም መኖርን መምረጣቸው፥

# ምዕራፍ ፮፤ በዓል:: ዓበይትና ንዑሳን በዓላት::

## በዓለ መስቀል::

### የእውነተኛው መስቀል ፍለጋና ስለመገኘቱ::

---

፪ኛ:- ቆይተው ግን: ከዚህ የኃጢአት ምግባራቸው ፍጹም ተጸጽተው: ንስሓ በመግባት: የፈጣሪያቸውን ምሕረት መጠየቃቸው፥ እግዚአብሔርም: ሊነገር በማይቻል ቸርነቱ: ኃጢአታቸውን ይቅር ማለቱ፥

፫ኛ:- እግዚአብሔር: የዚህ ይቅርታው መገለጫ በኾነው: በአንድ ልጁ: በኢየሱስ ክርስቶስ ቤዛነት: እነርሱንና የእነርሱን ፈለግ የተከተልን: እኛን ዘሮቻቸውን: በፈቃዳችን ካመጣነው: ከዚያ የፍዳ አገዛዝ: የኃጢአት ቀንበርና የሞት ዕዳ: ካዳነን በኋላ: ጥንቱኑ አዘጋጅቶልን ወደነበረው ወደዘለዓለም መንግሥቱ ሕይወት የመለሰን መኾኑ: ከኹሉ በፊት: መነሻና መሠረት ኾኖ መነገር አለበት::

ይህም ኹሉ ሊኾን የቻለው: አዎን! በቀላል አልነበረም፥ እግዚአብሔር ወልድ: ከቅድስት ድንግል ማርያም: በፍጹም ሰውነት ተወልዶ፥ ያለኃጢአት: እውነተኛውን ሰብአዊ ሥርዓት በመኖር: ለፍጥረቱ በጎ አርአያ ኾኖ: የእግዚአብሔርን መንግሥት ምንነት: በትምህርት ገልጦና አምላክነቱንም በተአምራት አሳይቶ፥ ልዩ ልዩ ፈተናዎችን አሸንፎና መከራዎችን ተቀብሎ: በመስቀል ላይ ራቁቱን ተሰቅሎና ደሙን አፍስሶ: ሙቶና ተቀብሮ: በመጨረሻ: በትንሣኤው: ያን ጠንቀኛ ጠላታቸውን ዲያብሎስን ድል በመንሣት ነው::

ከዚህ ጋር በማያያዝ: *"እኔን መከተል የሚወድ ቢኖር: ራሱን ይካድ! መስቀሉንም ተሸክሞ ይከተለኝ! ነፍሱን ሊያድን የሚወድ ኹሉ: ያጠፋታል! ስለእኔ ግን: ነፍሱን የሚያጠፋ ኹሉ ያገኛታል!"* የሚለው: የመስቀሉ ጌታ: የኢየሱስ ክርስቶስ ቃል እና የእርሱ ተከታይ ሐዋርያ: ቅዱስ ጳውሎስ: በመንፈስ ቅዱስ ተመልቶ: *"የመስቀሉ ቃል: ለሚጠፉት ሞኝነት፥ ለእኛ ለምንድን ግን: የእግዚአብሔር ኃይል ነው!"* በሚል የመክፈቻ አርእስት[፲፰] ስለመስቀል ምስጢር የሰጠው የትርጓሜ ሐተታ: አብሮ ሊነገር ይገባል::

የትርጓሜው ሐተታ እንዲህ ነው:- የአይሁድ ሊቃናት: ከካህናቱና ከሕዝቡ ጋር: በሰይጣናዊ ቅንዓት ተነሣሥተው: በስቅላት ያስገደሉት ኢየሱስ ክርስቶስ: ሥጋው ከተቀበረም በኋላ: ቅንዓታቸው ሊበርድ፥ ጭካኔያቸውም ሊረግብ አልቻለም፤ ያ: ያሠቃዩት ጌታ: ስለፍጥረቱ ቤዛነት: የመጨረሻው የፋሲካ በግ ኾኖ የተሠዋበትንና ይህን የመሰለው መለኮታዊ ፍቅር ተፈጽሞ: ምስጢሩ የተከሠተበትን እንጨት እንኳ: በርኅራኄያቸው ትተው ሊያልፉት አልፈለጉም:: "ደቀ መዛሙርቱ: ሥጋውን ሠርቀው እንዳይወስዱት" በሚል ምክንያት: መቃብሩን እንዲያስጠብቅላቸው: ወደጲላጦስ ኼደው በመማፀንና እርሱም ፈቃዳቸውን በመፈጸም: በድኑን ሳይቀር እንዳልተዉት ኹሉ: አኹንም: በመስቀሉ ላይ የፈጸሙት ግፍ: ከዚያ ያላነሰ፥ እንዲያውም የባሰና ወደር የማይገኝለት ኾኖ እንዲቀጥል ማድረጋቸውን እነሆ እንመለከታለን::

ይኸውም: መስቀሉ: ደብዛው ሳይቀር: ጨርሶ እንዲጠፋ ያደረጉበት መሠሪ ዕቅዳቸውና ክፉ ድርጊታቸው ነው:: በዚህ ዕቅዳቸው መሠረት: ማንም ሰው፥ የራሳቸው የኾኑት ወገኖቻቸው እንኳ ሳይቀሩ: ሊጠረጥሩ በማይችሉበት ኹኔታና ሥፍራ: መስቀሉን: በድብቅ አስወስደው ቀበሩት፤ ያም ሥፍራ: ለከተማው የቆሻሻ መጣያ የተመደበው ቦታ ነበር::

በዚህ ድርጊታቸው፡ ሦስት እኩይ ዓላማዎቻቸውን የፈጸሙ መሰሏቸው ነበር፡፡ ከእነዚህ ዓላማዎቻቸው መካከል:-

የመጀመሪያው፡ የሰማይና የምድር ፈጣሪና ጌታ የኾነው ኢየሱስ ክርስቶስ፡ ቅዱስ ሥጋው የተቆረሰበትንና ክቡር ደሙ የፈሰሰበትን ምሥዋዕ (መሠዊያ) መስቀሉን ማርከስ ሲኾን፥

ኹለተኛው ደግሞ:- ሕዝቡ ኹሉ፡ የቤቱንና የከተማውን ጥራጊና ቆሻሻ፡ በየቀኑ ያለማቋረጥ በማፍሰስና በመጣል፡ መቀበሩን ማንም ሊያውቅ እንዳይችል፡ ምናልባት ቢታወቅ እንኳ፡ ምን ጊዜም ተቆፍሮ እንዳይገኝና እንዳይወጣ ማድረግ ነው፡

ሦስተኛውም:- መስቀሉን እንዲህ አድርገው በሚቀብሩበት ጊዜ፡ የክፋታቸው መጠን ምን ያህል የጸና መኾኑን የሚያመለክተው፡ ሌላው ገጽታ ይታያል፡ ይኸውም፡ ዕፀ መስቀሉ፡ ምናልባት ተቆፍሮ የተገኘ እንደኾን፡ የዓለም መድኀን የተሰቀለበት፡ እውነተኛው እንጨት፡ የትኛው እንደኾነ ተለይቶ እንዳይታወቅ ለማደናገር ሲሉ፡ በቀኝና በግራ የተሰቀሉትን ወንበዴዎች ብቻ ሳይኾን፡ ሌሎች ወንጀለኞች ጭምር የተሰቀሉበትን እንጨት፡ ከጌታ መስቀል ጋር ደበላልቀው እንዲቀበር ማድረጋቸው ነው፡፡ ;

## ዕሌኒ ንግሥትና ልጇ ንጉሥ ቈስጠንጢኖስ፡፡

ነቢዩ ዳዊት፡ *"ጊዜ፡ ዝቢር ለእግዚአብሔር"* እንዳለው፡ እግዚአብሔር፡ ፈቃዱን የሚፈጽምበት፡ ሥራውንም የሚሠራበት ጊዜ ስላለው፡ የዚህ፡ የመስቀሉ ክብርና ኃይል የሚገለጽበት ቀኑ፡ እነሆ ደረሰ፡፡ ያም ቀን፡ ምድረ ከነዓንን በማጠቃለል፡ በማእከላዊው ባሕር አካባቢ ያለውንና በዘመኑ፡ "ሥጋዊው ሥልጣኔ ዳብሮበታል" የተባለውን ዓለም፡ በቄሣርነት የገዛው ቆስጠንጢኖስ፡ በ፫፻፳፭ ዓ. ም. በእናቱ በንግሥት ዕሌኒ አማካይነት፡ የክርስትናን እምነት ለመቀበል፡ ራሱን ያበቃበት ጊዜ ነበር፡፡ በዚያው ዓመት፡ ሃይማኖታዊት የኾነችው፡ ይህችው ንግሥት እናቱ፡ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ተወልዶ፥ አድጎና ኖሮ፡ ተሰቅሎና ሙቶ፡ ተነሥቶና ዐርጎ፡ ተልእኮውን በማከናወን፡ ዘለዓለማዊ የምሕረት ጸጋውን፡ ለሰው ልጆች፡ በቃል ኪዳን የሰጠባቸውን ቅዱሳት መካናት ትሳለም ዘንድ፡ ልቦናዋ ተነሣሥቶ፡ ወደኢየሩሳሌም እንድትጓዝ ኾነ፡፡

ዕሌኒ ንግሥት፡ ኢየሩሳሌም ገብታ፡ ቅዱሳት መካናትን እየተዘዋወረች ከጎበኘች በኋላ፡ ስለጌታ ቅዱስ መስቀል በጠየቀች ጊዜ፡ መስቀሉ የተቀበረበት ቦታ ባለመታወቁ፡ እስከዚያን ቀን ድረስ፡ የመስቀሉ ነገር የተሠወረ ምሥጢር ኾኖ እንደሚገኝ ተነገራት፡፡ በዚያን ጊዜ፡ መስቀሉን በሚመለከት፡ በመንፈሳዊ የፍቅርና የቅንዓት እሳት በነደደ ልቦናዋ፡ የጌታን፡ ሕማማቱንና የተናገራቸውን ቃላት በማዘከር፡ ወደፈጣሪዋ፡ የእንባ ጸሎትን አቀረበች፡ በእርሷ በኩል፡ ምን ማድረግ እንደሚገባት ያመለክቷትም ዘንድ፡ ወደቤተ ክርስቲያን መሪዎችና አገልጋዮች ካህናት፡ በየቦታው ወደዘጉ ባሕታውያን ሳይቀር እየላከች አስጠየቀች፡፡

## ምዕራፍ ፳፤ በዓል። ዓበይትና ንዑሳን በዓላት።
## የእውነተኛው መስቀል ፍለጋና ስለመገኘቱ።
### ዕሌኒ ንግሥትና ልጇ ንጉሥ ቈስጠንጢኖስ።

---

ከእነርሱም ያገኘችው መልስ፡ ካህናትና ምእመናን፡ በቤተ ክርስቲያን ተሰባስበውና በምሕላ ተጠምደው፥ የዘጉትና የበቁትም፡ በየበዓታቸው ተጠናክረው ኹሉም፡ በያለበት ጾምና ጸሎት በማድረስ፡ መንፈስ ቅዱስ፡ ምስጢሩን እንዲፈታው መጠየቅ መኾኑን የሚያመለክት ነበረ። እርሷም፡ ይህ የተባለው መንፈሳዊ ምግባር፡ ራሷ ጭምር በተካፈለችበት፡ እንዲካኼድ አድርጋ፡ የእግዚአብሔር ጽድቅ የተገለጸበትንና መልካም የምሥራች ፍሬ የኾነውን፡ ከዚህ የሚከተለውን መመሪያ ለማግኘት በቃች። ይህም፡ "ለመሥዋዕት እንደሚደረግ፡ እንጨት ተረብርቦ እንዲነድና በዚያ ላይ፡ በሱባዔና በምሕላ የተጸለየበት ዕጣን ተጨምሮ፡ ጢሰ ቅታሬው፡ ወደሰማይ ከወጣ በኋላ፡ ወደምድር ተወርውሮ የሚተከልበት ያ ቦታ፡ ጌታ የተሰቀለበት እውነተኛው ዕፀ መስቀል የተቀበረበት ሥፍራ መኾኑን አረጋግጦ የሚያሳይ ምልክት ይኾናችሁ!" የሚል ነበር።

በዚህ መሠረት፡ መንፈሳዊቷ ንግሥት፡ ይህንኑ መመሪያ በመከተል፡ የታዘዘው ሥርዓት እንዲፈጸም በማድረጓ፡ በሃይማኖታዊ ተስፋና ቅንዓት የተጠበቀው ውጤት ታየ! አዎን! ከሚነድደው እሳት ተነሥቶ፡ ወደሰማይ የወጣው የዕጣኑ ጢሰ ቅታሬ፡ ወደምድር ተመልሶ፡ ከተራራማነት መጠን ደርሶ በነበረ፡ በአንድ ጉብታ ላይ እንደጦር ተወርውሮ ተተከለ! ይህ ተአምር የታየበት ዕለት፡ መስከረም ፲፯ ቀን፥ ፫፻፳፯ ዓ.ም. ነበር። በዚያ ተራራ ላይ የሚደረገው ቁፋሮ፡ በዚሁ ቀን ተጀምሮ፡ ወደጥልቅ እየወረደ ሲቀጥል ከቆየ በኋላ፡ በመጋቢት ፲ ቀን፡ መስቀሎች ተከማችተው ከሚገኙበት ዐዘቅት ተደረሰ!

በዚያ ዐዘቅት ውስጥ ከነበሩት፥ ሳይበሰብሱና መሬት ሳይበላቸው ከተረፉት ጥቂት መስቀሎች መካከል፡ ለካ፡ ጌታችን፡ መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ፡ ለፍጥረቱ ቤዛ ኾኖ ደሙ የፈሰሰበት እውነተኛው ዕፀ መስቀል አብሮ ይገኝ ኖርዋል! ነገር ግን፡ የትኛው እንደኾነ ለይቶ ለማወቅ እጅግ አዳጋች ኾነ! ይኹን እንጂ፡ ይህን ችግር ለመፍታት፡ ረዥም ጊዜን አልወሰደም፡ ብዙ ድካምንም አልጠየቀም፤ አማናዊው ቅዱስ መስቀል፡ የተለያዩ ተአምራትን በመፈጸምና ራሱን ከሌሎቹ ለይቶ በማቅረብ፡ ማንነቱን፡ በታላቅ ኃይል ገልጦ ሊያሳይ ችሏልና።

ዛሬም፡ እኛ ኢትዮጵያውያን፡ "ደመራ" እና "መስቀል" እያልን፡ በየዓመቱ የምናከብረው በዓል፡ መነሻና ዓላማው፡ ይህ፥ መታሰቢያነቱም፡ ለዚህ መኾኑን፡ እናንተም፡ ልታውቁት ያስፈልጋችኋል።

*ጥያቄ:-* *ይህች ንግሥት ዕሌኒ፡ እንዴት ያለች፡ እውነተኛ ክርስቲያንና ጽኑ ሃይማኖታዊት ናት? ለክርስቲያኖችም ኹሉ፡ ባለውለታ ነች፤ አይደለችምን?*

መልስ:- አዎን! በእርግጥ ነች፤ በተለይም፡ ለእኛ፡ ለኢትዮጵያውያን።

# ኢትዮጵያ እና ኢትዮጵያዊነት፤
## "ፈጣሪዬ" የምለው እግዚአብሔር፡ ማነው?

---

ጥያቄ:- እንዴት?!

መልስ:- ይህችው ንግሥት ዕሌኒ፡ በኢየሩሳሌም ባሳለፈችው የጥቂት ዓመታት ቆይታዋ፡ የመጣችበትን፡ ቅዱሳት መካናትን የመሳለም ዓላማዋንና ታላቁ ትሩፋትዋ የኾነውን፡ የጌታን ቅዱስ መስቀል አስቆፍሮ የማውጣት ተልእኮዋን ማከናወን ብቻ ሳይኾን፡ በዚሁ፡ ጎልጎታ በተባለውና መስቀሉ በተገኘበት ቦታ ላይ፡ "የኢየሩሳሌምን ቤተ ክርስቲያን፡ በአምስት ዓመታት አሠርታ ጨረሰች:: አሠርታም እንደጨረሰች፡ ምዕራቡን፡ ለሮም (ለግሪኮች)፡ ምሥራቁን፡ ለሐበሾች (ለኢትዮጵያውያን) ሰጠች::"

ጥያቄ:- ኧረ! ነው እንዴ! ይህ፡ እንዴት ሊኾን ቻለ?! እስኪ፡ እባክህ፡ አስፋፍተህ ግለጥልን!?

መልስ:- ይህ የኾነው ያለምክንያት አልነበረም:: ያንም ምክንያት ልግለጥላችሁ! ኢትዮጵያውያን፡ ጥንት፡ ኢየሩሳሌምን ከቈረቈረው አባታቸው፡ ከመልከ ጼዴቅ ጀምሮ እስከኢትዮጵያዊት ንግሥታቸው፡ ማክዳ፡ ከዚያም፡ ታላቁ እስክንድር እስከተነሣበት ዘመን ድረስ፡ ከትውልድ ወደትውልድ እየተላለፉ፡ በውርስ የደረሷቸው፡ በኢየሩሳሌም ያሉት የዐፅመ ርስት ቦታዎችና ንብረቶች፡ በይዞታቸው ሥር ተጠብቀው ይኖሩ ነበረ፡ በእስክንድር ዘመን ግን፡ በእርሱ ሥልጣን፡ ከተተኩት ከአራቱ የጦር አዝማቾቹ አንዱ ወራሽ የነበረው፡ ፬ኛው አንጥያኮስ ኤጲፋንዮስ የተባለው አረማዊ፡ ከክርስቶስ ልደት በፊት፡ በ፩፻፷፰ ዓመት፡ ኢየሩሳሌም ገብቶ፡ ታላቅ ዕልቂትንና ብርቱ ጥፋትን አደረሰ፡ ከዚህ በኋላ፡ ከክርስቶስ ልደት በፊት፡ በ፩፻፷፯ ዓመት፡ መቃብያን፡ በእርሱ አገዛዝ ላይ በዓመፅ ተነሥተው፡ እስኪያስወግዱት ድረስ፡ እነዚህ፡ የኢትዮጵያ ይዞታዎች፡ በዚያ ከሚገኙት ቅዱሳት መካናት መካከል ጠፍ ኾነው ቆይተው ስለነበረ ነው::

- ይህን እውነታ፡ ከዚህ ቀጥሎ ያለው ማስረጃ ያረጋግጠዋል:: ስሙ፡ ቀደም ብሎ የተጠቀሰው ቆስጠንጢኖስ፡ ከክርስቶስ ልደት በኋላ፡ በ፫፻፳፮ ዓ.ም. ግድም፡ በሮም (በቍስጥንጥንያ) ነግሦ፡ እናቱን ወደኢየሩሳሌም ልኳት፡ እርሷም፡ ቀደም ብሎ እንደተገለጸው፡ የመጣችበትን የተቀደሰ ዓላማዋን፡ ታላቁን ተልእኮዋንና የሕንፃ ቤተ ክርስቲያን ሥራዋን አከናውና እንደፈጸመች ወዲያው፡ "በጊዜው ለነበሩት ክርስቲያኖች፡ ቦታ በምትሰጥበት ጊዜ፡ አብርሃ ወአጽብሐ የተባሉት፡ የዘመኑ የኢትዮጵያ ነገሥታት፡ ወደቆስጠንጢኖስና ወደእናቱ ንግሥት ዕሌኒ፡ እንዲህ ሲሉ ላኩ፡- "በኢየሩሳሌም፡ 'ገዳመ ንጉሥ' [ኋላ በእስላሞች ጊዜ 'ዴር ሡልጣን'] የተባለ አንድ ቦታ፥ የአሕዛብ ነገሥታት፡ ኢየሩሳሌምን እስኪያጠፏት ድረስ፡ ከጥንት ጀምሮ በኢትዮጵያ ነገሥታት እጅ እንደነበረ፡ ከታሪክ አይታችሁ፥ ከሽማግሌም ጠይቃችሁ፡ እንድትመልሱልን እንለምናችኋለን::

## ምዕራፍ ፮፣ በዓል:: ዝበይትና ንዑሳን በዓላት::
## የእውነተኛው መስቀል ፍለጋና ስለመገኘቱ::
## ዕሌኒ ንግሥትና ልጇ ንጉሥ ቈስጠንጢኖስ::

""ከእናንተ በፊት የነገሡ አሕዛብ: እግዚአብሔርን የማይፈሩ÷ ሰውን የማያፍሩ ነበሩና: እግዚአብሔር: ለሕዝቡ: አማኝ ንጉሥ እስኪያነግሥ ድረስ: ዝም አለን:: አሁን ግን: 'እግዚአብሔርን የሚፈራ÷ ለሕዝበ ክርስቲያን የሚራራ፣ ርስትን የሚተክል እንጂ የማይነቅል: ቆስጠንጢኖስ የሚባል ደግ ንጉሥ ነገሠ!' የሚል ዜናን ብንሰማ እጅግ በጣም ደስ አለን::

""ስለዚህ: አንቺም ክብርት ንግሥት ሆይ÷ ደግ ክርስቲያን መኾንሽንና ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስን ማፍቀርሽን ሰምተናልና: 'የናት ልመና: ፊት አያስመልስ: አንገት አያስቀልስ!' እንደሚባለው: ለንጉሡ ልጅሽ ነግረሽ: ርስታችንን አስመልሽልን!" ብለው ወደዕሌኒ ንግሥት ላኩ::

"እርሷም: ይህንኑ: ወደልጇ ወደንጉሥ ቆስጠንጢኖስ ልካ አሳወቀችው:: ንጉሥ ቆስጠንጢኖስም: የኢትዮጵያ ነገሥታት: አብርሃ ወአጽብሐ የላኩትን ቃል አይቶ: ከታሪክም ተመልክቶ፣ ከሽማግሌዎችም ጠይቆና ተረድቶ: የእናቱንም ምክር ሰምቶ: በደስታ: "እሺ!" አለ::

"ይኸው: በኢየሩሳሌም ቅዱሳት መካናት: የኢትዮጵያውያን ርስታቸው የኾነው ቦታ: በንጉሥ ቆስጠንጢኖስና በእናቱ በንግሥት ዕሌኒ ትእዛዝ: እንደቀድሞው: ለኢትዮጵያውያን እንዲመለስ ተደረገ:: ከዚያ በኋላ: ኢትዮጵያውያን መነኮሳት: መኖሪያ ቤት ሠርተው ባገኙት ቤተ ጸሎት እያገለገሉ ቆዩ:: ይህም የኾነው: ከ፫፻፳፰ ዓ.ም. ጀምሮ ነው:: እስከዘመነ ተንባላትም ድረስ: (ማለትም: እስላሞች ሥልጣን እስከያዙበት ጊዜ ድረስ:) ከሦስት መቶ ዓመታት ለሚበልጥ ጊዜ: በሰላምና በዕረፍት ኖሩ::"[፻፹፫]

### የመስቀሉ ነገርና ኢትዮጵያዊው አጼ ዳዊት::

**ጥያቄ:-** *ግሩም ነው! የመስቀሉ ነገር: ከዚህ በኋላ ምን ኾነ?*

**መልስ:-** የመስቀሉማ ነገር: በዚህ ኹኔታ: ለአንድ ሺ ዓመታት ያህል ተጠብቆ ሲኖር ሳለ: በመካከለኛው ዘመን ግድም: ከኢትዮጵያ ጋር በተያያዘ መልኩ: በመለኮታዊ ሥራ: እንደገና ሊነሣሣ የቻለበት ምክንያት ተፈጠረ፤ እርሱንም: እዚህ ላይ ወደማዘከሩ እንገባለን::

በ፲፫፻፹፩ ዓ. ም. በኢትዮጵያ ዙፋን ላይ ተቀምጦ: ለሠላሳ ዓመታት ያህል በዘውድ ሥልጣን የቆየው ዳግማዊ አጼ ዳዊት: በሃያ አምስተኛው የሥልጣን ዘመኑ: ናዝር የተባለ የእስላም ንጉሥ: በኢየሩሳሌምና በግብፅ የሚኖሩትን ክርስቲያኖች ኹሉ አስጨነቀ:: በዚያ መከራ ምክንያት: አባ ዮሐንስ የሚባለው: የኢየሩሳሌም ኤጲስ ቆጶስ: "ስለእግዚአብሔር ብለህ እርዳን! የክርስቲያን ስም ጠፋ! በእስላምም እጅ ተጨነቅን!" ሲል: ወደኢትዮጵያው መሪ: ወደአጼ ዳዊት: መልእክትን ላከ::

ይህን መልእክት የተቀበለው አጼ ዳዊት: በክርስቲያኖቹ ላይ የደረሰውን መከራ: ከመልእክተኞቹ በተረዳ ጊዜ: እጅግ አዘነ::

# ኢትዮጵያ እና ኢትዮጵያዊነት፤
## "ፈጣሪዬ" የምለው እግዚአብሔር፡ ማነው?

ወዲያውም፡ "ምታ ነጋሪት! ክተት ሠራዊት!" ብሎ ወደምድረ ግብፅ ለመዝመት፡ በግብፅና በኢየሩሳሌም፡ በመከራ የሚሠቃዩትንም ክርስቲያኖች፡ ከእስላሞች እጅ ለማዳን ተነሣ፡፡ ቊርጥ ውሳኔው በዚህ ብቻ ሳያበቃ፡ "የምሥርን [የግብፅን] አገር የሚያጠጣውን የዓባይን ውኃ ገድቤ፡ ወደውቅያኖስ እንዲፈስስ አደርገዋለሁ!" ብሎ ላከ፡፡

ምሥሮች (ግብፃውያን)፡ ያለዓባይ፡ ሌላ ውኃ የላቸውምና፡ እስላሞች፡ ይህን ቃል ሲሰሙ፡ ከንጉሣቸው ጋራ ተጨነቁ፡፡ ስለዚህም ነገር፡ በኢየሩሳሌምና በግብፅ ከሚኖሩት ክርስቲያኖች ጋር በግድ ታረቁ፡፡ አጼ ዳዊትም፡ ደስ ብሎት ወደአገሩ ተመለሰ፡፡

አጼ ዳዊት፡ ይህን የመሰለውን፡ ታላቅ የመታደግ ሥራ፡ በእግዚአብሔር ፈቃድና ኃይል ስላደረገላቸው፡ ለዚህ በጎ አድራጎቱ የሚመጥን፡ መልካም ውለታ ይኾንላቸው ዘንድ፡ "ምን ዓይነት ቋሚ የመታሰቢያ ስጦታ እናድርግለት?" ብለው፡ የኢየሩሳሌሙ ኤጲስ ቆጶስ፡ ካህናቱና ምእመናኑ አሰቡ፤ መከሩም፡፡

በዚያ ምክራቸውም፡ የጌታችን የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስን፡ የመስቀሉን ቀኝ ግማድ (ጒራጅ)፡ ከእርሱም ጋር፡ ዮሐንስ ወንጌላዊው፤ የሣለውን፡ የኢየሱስ ክርስቶስን ኵርዓተ ርእስና ወንጌላዊው ሉቃስ የሣላትን፡ የምስለ ፍቁር ወልዳን ሥዕል ሊልኩለት ተስማምተው ወሰኑ፡፡ ወስነውም አልቀረ፡ ይህንኑ ግማደ መስቀል፡ ከኹለቱ ሥዕሎች ጋር ላኩለት፡፡

ይህም የኾነው፡ ግማደ መስቀሉ፡ በሕያው ቅርስነቱ፡ እንደሌሎቹ ንዋያተ ቅድሳት ኹሉ፡ የልዑል አምላክ፡ የቃል ኪዳን ባላደራ በኾነችው፡ በኢትዮጵያ ምድር፡ ተጠብቆ፡ ለዘለዓለም ይኖር ዘንድ፡ የእግዚአብሔር ፈቃድ በመኾኑ ነው፡፡

የክርስቶስ ታማኝ አገልጋይ ኾኖ የተገኘው፡ ዕድለኛው አጼ ዳዊት፡ ይህን ዜና በሰማ ጊዜ፡ ዜናውም፡ ወደቤተ ክህነቱ፥ ወደቤተ ምልክናውና ወደቤተ ሕዝቡ ጆሮ ደርሶ በተሰማ ጊዜ፡ ኹሉም፡ ታላቅ ደስታ ተሰማቸው፤ ለፈጣሪያቸውም፡ ልባዊ ምስጋናን፡ በየቤታቸውና በየቤተ ክርስቲያናቸው አቀረቡ፡፡ ግማደ መስቀሉንም ለመቀበል፡ ወደአገራቸው ሰሜናዊ ጠረፍ፡ ጕዞ ለመጀመር፡ አልዘገዩም፡፡ ከአጭር ቀናት ዝግጅት በኋላ፡ ስናር ወደተባለችው ግዛት ተገዝው፡ በመስከረም ፲ ቀን፡ ፲፬፻፲፮ ዓ. ም. ግማደ መስቀሉን፡ ከእርሱም ጋር፡ ኹለቱን ሥዕሎች ተረከቡ፡፡ ከዚያን ጊዜ ጀምሮ፡ ይህ ዕለት፡ "ተቀጸል ጽጌ" እና "ያጼ መስቀል" ተብሎ፡ እነሆ እስከዛሬ፡ በየዓመቱ ይከበራል፡፡

አጼ ዳዊት፤ እርሱንም የተከተሉት፡ የቤተ ምልክናው፥ የቤተ ክህነቱና የቤተ ሕዝቡ ተጠሪዎች፡ እንዲህ አድርገው ከተረከቡት ግማደ መስቀል፡ ፍጹም የኾነውን መለኮታዊ በረከት ተቀብለውና በመስቀሉ ብርሃን ተመልተው፡ ይህንኑ፡ ቅዱሱንና ሰማያዊዉን ቅርስ ይዘው፡ ወደአገራቸው የሚያደርጉትን የመልስ ጕዞ፡ በታላቅ ሥርዓት ጀመሩ፡፡

## ምዕራፍ ፮፡ በዓል፡፡ ዓበይትና ንዑሳን በዓላት፡፡ የመስቀሉ ነገርና ኢትዮጵያዊው አጼ ዳዊት፡፡

አጼው፡ በግርማ መንግሥቱ፡ ቀሳውስቱና ደባትሩ (መዘምራኑ)፡ በቅዳሴ፡ በማኅሌትና በይባቤ፥ አለቆቹና ሠራዊቱ፡ በክብር ሰልፍ፥ እንዲሁም፡ ሕዝቡ፡ ወንዱ በሆታና ሴቱ በእልልታ፡ ግማደ መስቀሉን ዐጅበው፡ የዘመኑ መናገሻ ከተማ ከኾነችው ከተማ አድርሰው፡ በዚያ በተዘጋጀለት ማደሪያ፡ በታላቅ ማዕርግ አሳረፉት፡፡ ያችም ከተማ፡ በላይዋ ከታየው፡ የመስቀሉ ብርሃን የተነሣ፡ የዛሬ መጠሪያ ስሟን ያተረፈችውና በሸዋ፡ ተጉለት የምትገኘው፡ የዘርዓ ያዕቆብ መዲና፡ ደብረ ብርሃን ናት፡፡

ግማደ መስቀሉ፡ ለጥቂት ጊዜያት፡ በዚችው በደብረ ብርሃን ከቆየ በኋላ፡ በመጨረሻ፡ ከዚያ ተነሥቶና በወሎ ምድር ወደምትገኘው፡ ወደግሼን አምባ ተዛውሮ፡ ዛሬ፡ በዚያ ይኖራል፡፡ ይህ፡ በአጼ ዘርዓ ያዕቆብ ዘመን የተፈጸመው ድርጊት የደረሰው፡ ያለምክንያት አልነበረም፡፡ ቀደም ብሎ በተነገረው፡ የትንቢት ቃል መሠረት፡ ለግማደ መስቀሉ፡ የዘለዓለም ማረፊያ እንድትኾን የተመደበችውን ቅዱስ ተራራ ለመፈለግ፡ ከአጼው ጋር፡ የቤተ ክህነቱ፡ የቤተ ምልክናውና የቤተ ሕዝቡ ተጠሪዎች፡ ግማደ መስቀሉን ይዘው፡ ከተራራ ወደተራራ ተዘዋወሩ፡፡

ኢትዮጵያን፡ በቅዱስ መስቀሉ፡ ለሦስት ዓመታት ከሦስት ወራት ካስባረኩ በኋላ፡ በመጨረሻ፡ በተፈጥሮዋ የመስቀል መልክ ባላትና እግዚአብሔር፡ ለቅዱስ መስቀሉ ማረፊያ እንድትኾን፡ አስቀድሞ ባዘጋጃት፡ በግሼን ተራራ ላይ፡ ይኸው ግማደ መስቀል ዐረፈ፡፡ ግማደ መስቀሉ፡ በዚች ተራራ ላይ ከማረፉ በፊት፡ በመላ ኢትዮጵያ፡ በአራቱ ማዕዘናት፡ እንዲዘዋወር የኾነው፡ "የኢትዮጵያ አድባራት፡ በግማደ መስቀሉ ይቀደሱ ዘንድ፡ የእግዚአብሔር ፈቃድ በመኾኑ ነው፤" ተብሎ ይነገራል፡፡ ባሁኑ ጊዜ፡ ደብረ ከርቤ ተብላ የምትጠራው፡ ይህች የግሼን ተራራ፡ መጀመሪያ፡ ደብረ ነገሥት፡ ቀጥሎ፡ ደብረ ነጐድጓድ ትባል እንደነበረም ይታወቃል፡፡

ጥያቄ፡- *ስለመስቀል ነገር ከሰማነው፡ ከዚህ ሐተታ፡ ልናገኝ የምንችለውን ትምህርታዊ ጥቅም፡ አንተ፡ በምን ታጠቃልለዋለህ?*

መልስ፡- ኢትዮጵያውያን፡ በያመቱ፡ በመስቀል ዋዜማ፡ በመስከረም ፲፮ ቀን፡ ደመራን ደምረው* እና በደመራው ዙርያ ተሰባስበው፡ ተገቢውን ሥርዓተ ጸሎት ካደረሱ በኋላ፡ እሳቱን በማንደድ፡ ተከታዩን፡ መስከረም ፲፯ ቀንን እያደዘው የሚያከብሩት የመስቀል በዓል፡ በግዙፍ ሲፈጸም ከምናየው ሥርዓትና ድርጊት በላይ፡ ሌላ፡ ጥልቅ ምሥጢርና ዓቢይ መልእክት ያለው መታሰቢያ መኾኑ፥ ለታይታ ወይም ለልማድ ብቻ ተብሎ የሚከበር በዓል አለመኾኑም ሊታወቅ ይገባል፡፡

* እያንዳንዱ ምእመን፡ ቀርጦና መልምሎ፥ በጫፉም ቅጠል ላይ፡ የአደይ አበባ ነዶ አሥሮ፡ በመስቀል ዋዜማ ለሚነደው እሳት ያገለግል ዘንድ፡ ለዚህ ተግባር ወደተመደበው፡ ወደቤተ ክርስቲያን አደባባይ የሚያመጣውን፡ ለምለም አጠና (ለጋ ዛፍ)፡ በሌላው ላይ ስለሚደምረው፡ 'ደመራ' ተባለ፡፡

# ኢትዮጵያ እና ኢትዮጵያዊነት፤
## “ፈጣሪዬ” የምለው እግዚአብሔር፡ ማነው?

---

ቁም ነገሩ፡ ለጊዜው ነድዶ በጥቂት ሰዓታት ውስጥ አመድ የሚኾነው የእንጨቱ ክምርና፡ ብርሃኑ በድምቀት ተንቦግቡጎ ከታየ በኋላ፡ ወዲያው የሚጠፋው ግዙፉ የእሳት ነበልባል አይደለም። ቁም ነገሩ፡ ከመስቀሉ በዓል ርእስ መግቢያ ላይ የጠቀስሁላችሁ፡ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ፡ ስለመስቀሉ የተናገረው ቃልና በቅዱስ ጳውሎስ ብዕር የተጻፈው መልእክት፡ በልባችን ሰሌዳ ላይ ተቀርጾ፡ ሕይወታችንን እየመራንበት ነወይ? ደግሞስ፡ ከዚህ መለኮታዊ ቃልና ሓዋርያዊ መልእክት የተነሣ፡ ያ፡ በንግሥት ዕሌኒ ልቦና ውስጥ ይነድ የነበረው መንፈሳዊና ሃይማኖታዊ የቅንዓት እሳት፡ ዛሬ፡ በእኛ፡ በእያንዳንዳችን ልቦና ውስጥ እየነደደ ነወይ? ለሚለው ጥያቄ የምንሰጠው መልስ መኾኑ ተረጋግጦ ሊታወቅና ሊታመንበት፥ በምግባርም ሊገለጥ ይገባል።

አዎን! የአምላካችንና የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስ፡ እውነተኛ መስቀሉ ተቀብሮ ሊገኝበትና የፍቅሩ ዘለዓለማዊ እሳት፡ እንደደመራው እንጨት፡ ሊነድድበት የሚገባው ቦታ፡ ሃይማኖታዊውና መንፈሳዊው ልቦናችን መኾኑን፡ ይህ፡ የመስቀል በዓል ያስታውሰናል።

### ወርኀ ጽጌ።

ከመስከረም ፳፮ እስከ ኅዳር ፮ ቀን ድረስ፡ አርባ ዕለታት ያለው ወራት፡ “ወርኀ ጽጌ” ወይም፡ “ዘመነ ጽጌ” ይባላል። ቅድስት ድንግል ማርያምና ሕፃን ልጇ፡ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ፡ የተቀበሉትን፡ ቀዳሚ የስደት መከራ በማሰብ፡ ኢትዮጵያውያን፡ “ጾመ ስደት” ብለው፡ በየዓመቱ የሚፈጽሙት፡ የመጀመሪያው የዓመቱ ጾማቸው የሚካኼደው፡ በዚሁ፡ በ“ዘመነ ጽጌ” መኾኑ፡ በአንደኛው የዚህ መጽሐፍ ጥራዝ፡ ገጽ ፻፶፬-፻፶፭ ላይ ተገልጿል።

በግእዝ፡ “ጽጌ” ማለት፡ “አበባ” ነው። ዘር ኹሉ፡ ከፍሬ በፊት የሚያሳየው የምሥራች ምልክት፡ “አበባ” እንደመኾኑ መጠን፡ እግዚአብሔር፡ አዳምንና ሔዋንን፡ በኢትዮጵያ ምድር ፈጥሮ፡ ለመኖሪያቸው በከለለላቸው፡ የዔዶም ገነት መኻከል፡ የተከላት “የሕይወት ዛፍ” ምሳሌዋ የኾነችው፡ “እውነተኛዪቱ ሕያውት ዛፍ”፡ ድንግል ማርያምም፡ እውነተኛውን የዘለዓለም ፍሬ፡ ኢየሱስ ክርስቶስን፡ ከመውለዷ በፊት፡ በዘለዓለማዊት አበባነቷ፡ እንደርግበ ኖኅ፡ የዓለሙን የደኅንነት ምሥራች፡ ለፍጥረቱ ኹሉ ማወጇን ለማስረዳት፡ በአበባ ተመስላለች።

## ጸመ ስደትና ማኅሌተ ጽጌ።

የ"ጸመ ስደት"ን እና የ"ወርኀ ጽጌ"ን ምሥጢር፡ ኢትዮጵያዊው ሊቅ፡ አባ ጊዮርጊስ፡ ዘሀገረ ጋሥጫ፡ "ሰቆቃወ ድንግል" እና "ማኅሌተ ጽጌ" በተባሉት፡ በግእዙ፡ የመልእክታት ድርሰቶቹ፡ ገላልጦ፡ በሰፊው ተናግሮታል። "ዮሴፍ፡ የእግዚአብሔር መልእክ፡ ሌሊት፡ በሕልሙ እንደነገረው፡ ከእንቅልፋ ተነሥቶ፡ ሕፃኑን፡ ከእናቱ ከማርያም ጋር ይዞ፡ ወደግብፅ አገር ሸሸ፡ ማርያምም፡ 'የልጄን ደም ሲያፈስሱት ከማይ ይልቅ፡ የእኔን ሞት ያስቀድሙት!' ብላ አለቀሰች።" ተብሎ የሚተረጐመውን፡ *"ጐየ ዮሴፍ፡ ብሔረ ግብፅ፡ ተንሢኦ እምንዋሙ፡ መልአከ እግዚአብሔር ሌሊተ፡ በከመ ነገሮ በሕልሙ፡ ነሢኦ ሕፃነ፡ ዘምስለ ማርያም እሙ፡ ይእቲ ትበኪ፡ ወትቤ፡ 'ቀቲሎትየ ይቅድሙ! እምእርኢይ ለወልድየ፡ ዘይትከዓው ደሙ!'"* የሚለውን፡ የ"ሰቆቃወ ድንግል" ድርሰቱን ይጀምራል።

የ"ማኅሌተ ጽጌ" ድርሰቱንም፡ *"ጽጌ አስተርአየ፡ ሠሪፆ እምዓጽሙ!"* በሚል መክፈቻ ጀምሮ፡ *"እንዘ ተሐቅፊዮ ለሕፃንኪ፡ ጽጌ ፀዓዳ ወቀይሕ፡ አመ ቤተ መቅደስ ቦእኪ፡ በዕለተ ተአምር ወንጽሕ፡ ንዒ ርግብየ፡ ትናዝዝኒ እምላሀ፡ ወንዒ ሠናይትየ፡ ምስለ ገብርኤል ፍሡሕ፡ ወሚካኤል፡ ከማኪ ርኅሩኅ።"* በሚል ውዳሴ እየተንደረደረ ኼዶ፡ *"ተፈጸመ ናሁ፡ ማኅሌተ ጽጌ ሥሙር፡ አስምኪ ቦቱ፡ ንግሥተ ሰማይ ወምድር፡ ከመ በሕፅንኪ ያስምክ ፍቁር።"* በሚል ማሳረጊያ ይደመድመዋል። የዚህም ትርጉም፡ የመጀመሪያው፡ "ከግንዱ የሠረፀችው ሐረግ፡ አበባነቷን ገልጣ አሳየች!"፡ ከዚያ የቀጠለው፡ "አንቺ፡ የፈካሽ ጽጌረዳ ሆይ! ንጹሕና ተአምረኛ በኾነችው፡ በአርባኛዪቱ ዕለት፡ ሕፃን ልጅሽን አቅፈሽ፡ ወደቤተ መቅደስ እንደገባሽ፡ ዛሬም፡ የእኔ መልካሚቱ ርግብ ሆይ! ከኃዘናችን ታጽናኚን ዘንድ፡ ከርኅሩኁ መልአክ፡ ከሚካኤልና ከባለምሥራቹ መልአክ፡ ከገብርኤል ጋር አብረሽ ነዪልን!" ሲኾን፡ የመጨረሻውም፡ "በምሥጢር የተከናወነው፡ የአበባዪቱ ማኅሌት፡ እነሆ ተፈጸመ! የሰማይና የምድር ንግሥት ሆይ! ተወዳጁን ሕፃን ልጅሽን፡ በጭንሽ እንደታቀፍሺው ኹሉ፡ ይህን፡ ዝማሬያችንንም፡ እንደርሱ ታቀፊልን!" የሚል ነው።

በዚህ ወራት፡ በየሳምንቱ እሑድ ሌሊት፡ ካህናቱና መዘምራኑ፡ በየሰበካ ቤተ ክርስቲያናቸው እየተገኙ፡ ከዋዜማው ቅዳሜ ማታ ጀምረው፡ በመቋሚያ፡ በጸናጽልና በከበሮ በመዘመርና በማሸብሸብ፡ ቀደም ብሎ የተጠቀሰውን ማኅሌተ ጽጌ፡ በተመሰጠ መንፈሳዊ ስሜት ሲያደርሱ ያድራሉ። ምእመናንና ምእመናትም፡ በብዛት ተገኝተው፡ ሌሊቱን ኹሉ፡ በመንፈሳዊ ደስታ ተመልተው፡ ወንዶቹ፡ በጭብጨባ፡ ሴቶቹም፡ በእልልታ፡ ካህናቱን በማጀብ፡ የምስጋናው ዝማሬ ተካፋዮች ይኾናሉ።

ኢትዮጵያውያን፡ እንዲህ ባለ፡ የተለየ መልክ፡ መንፈሳዊ ደስታቸውን የሚገልጹት፡ ቀደም ብሎ ከተገለጸው፡ ከአበባው ምሥጢራዊ ምሳሌነት ጋር፡ ሌሎች ተጨማሪ ምክንያቶችም ስላሏቸው ነው።

# ኢትዮጵያ እና ኢትዮጵያዊነት፤
## "ፈጣሪዬ" የምለው እግዚአብሔር፡ ማነው?

እነዚህም:-

፩ኛ:- *"ልጄን ከግብፅ ጠራሁት፡"* የሚለው የነቢዩ ትንቢት ይፈጸም ዘንድ፡ እመቤታችን ድንግል ማርያም፡ ሕፃን ልጇን፡ ኢየሱስ ክርስቶስን ታቅፋ፡ ከዮሴፍና ከሰሎሜ ጋር፡ ወደምድረ ግብፅ የተሰደደችበትና በዚያም፡ "ቍስቋም" በተባለችው፡ የኢትዮጵያውያን ርስትና ገዳም ውስጥ የቆየችበት ጊዜ የሚታወስበት መኾኑ፡

፪ኛ:- በዚያኑ ወቅትና ከዚያ በኋላ፡ ልጇ፡ ፲፪ኛ ዓመቱን ከጨረሰበት ዕድሜው ጀምሮ ፴ ዓመት ሞልቶት እስኪጠመቅ ድረስ ባለው ዘመን መካከል፡ እናትና ልጇ፡ በሊቀ መላእክት ቅዱስ ዑራኤል ጠባቂነት፡ አገራቸውን ኢትዮጵያን፡ እየተመላለሱ የጐበኙባቸው ጊዜያት የሚዘከርበት ሰሞን መኾኑ ናቸው።

በእነዚህ ምክንያቶች፡ ይህ ወርኀ ጽጌ፡ በተለይ፡ ለእኛ ለኢትዮጵያውያን፡ መታሰቢያነቱ፡ እጥፍ ድርብ ኾኖ ይዘከራል። ይህም፡ በአንድ ወገን፡ በታላቅ ተመስጦ በሚካኼደው፡ በጽጌ ማኅሌት፡ በሌላ ወገን ደግሞ፡ በፍጹም ፈቃደኝነት በምትጸመው፡ በጽጌ ጾም ገዝፎ ይታያል።

የጽጌ ማኅሌቱና የስደቱ ጾም ፍጻሜ፡ እመቤታችንና ልጇ ባረፉባት፡ በኢትዮጵያውያኑ ገዳም፡ በደብረ ቍስቋም ተሰይሞ፡ በዓሉ፡ በኅዳር ፮ ቀን ይከበራል።

## ዘመነ አስተምህሮ።

ከኅዳር ፯ እስከ ፴ ቀን ድረስ፡ "ዘመነ አስተምህሮ" ይባላል። ሕዝቡ፡ ከመስከረም ፳፮ እስከ ኅዳር ፮ ቀን ድረስ ባለው "ወርኀ ጽጌ"፡ ስለሥነ ፍጥረት፡ ስለፈጣሪና ስለራሱ ፍጡርነት፡ በበለጠ ሲረዳ እንደቆየ ኹሉ፥ አኹን ደግሞ፡ ከኅዳር ፯ እስከ ፴ ቀን ድረስ ባሉት ሳምንታት፡ ከምሥጢረ ሥላሴ ተነሥቶ፡ በምሥጢረ ሥጋዌ፡ በምሥጢረ ጥምቀትና በምሥጢረ ቍርባን አልፎ፡ ወደምሥጢረ ትንሣኤ ሙታን የሚደርስበትን፡ የዓመቱን ሥጋዊና መንፈሳዊ ጉዞ፡ በትምህርት እየታነጸ ማደጉን ይቀጥላል፡ እያንዳንዱ ኢትዮጵያዊና እያንዳንዷ ኢትዮጵያዊት፡ በእነዚህ ሳምንታት፡ ሲቻላቸው፡ በቤተ ክርስቲያን፡ ሳይቻላቸው ደግሞ፡ በየቤታቸው እና/ወይም፡ በየሥራ ቦታቸው፥ አለዚያም፡ በየሚመቻቸው ሥፍራ እየተገኙ፡ ልመናቸውን፡ ወደፈጣሪያቸው እያቀረቡ፡ በነቢያት ትንቢት ሲጠበቅ የኖረውንና በሐዋርያት ተስፋ ተፈጽሞ የታየውን፡ የአዲስ ኪዳን ምሕረቱን ለመቀበል፡ እየራሳቸውን ያዘጋጁበታል።

ሕዝቡ፡ በዚህ፡ የትምህርትና የምሕላ አካኼዱ፡ እግዚአብሔር፡ በዘመነ ብሉይ፡ ለአባቶቹና ለእናቶቹ፡ በቃል ኪዳን ሲያደርግላቸው የቆየውን፡ የረድኤትና የበረከት ሥራዎቹን እያስታወሰ፡ እርሱም በፋንታው፡ እነርሱ ለበቁበት የገድል ጸጋና የድል አክሊል፡ ራሱን ለማብቃት፡ የሚደራጅባቸውን በዓላት እያከበረ፡ ጉዞውን ይቀጥላል። እነዚህም በዓላት፡ ከዚህ የሚከተሉት ናቸው:-

# ምዕራፍ ፮፤ በዓል።
## ዓበይትና ንዑሳን በዓላት።
## ዘመነ አስተምህሮ።

---

### የኅዳር ሚካኤል።

"የኅዳር ሚካኤል" ተብሎ፡ በኅዳር ፲፪ ቀን የሚከበረው፡ የሊቀ መላእክት ቅዱስ ሚካኤል በዓል ነው።

እግዚአብሔር፡ የእሥራኤልን ሕዝብ፡ በሙሴ አማካይነት፡ ከፈርዖን የባርነት አገዛዝና ከምድረ ግብፅ የሥቃይ ኑሮ፡ ነጻ አውጥቶ፡ መዓልቱን፡ በደመና፡ ሌሊቱንም፡ በእሳት ዓምድ ከልሎ እየመራቸው፡ የቀይ ባሕርንም፡ በደረቅ ምድር አሻግሮ እየጠበቃቸው፡ ውኃውን ከዓለት አፍልቆ፡ ኅብስተ መናውን ከሰማይ አውርዶ፡ "ሥጋ አማረን!" ቢሉም፡ ድርጭቱን በነፋስ አዝንሞ እየመገባቸው እንደተንከባከባቸው ይታወቃል፡ በአምላካቸው ቸርነት፡ ይደረግላቸው የነበረውን፡ ያን ኹሉ፡ የተራዳዒነት ተልእኮ ይፈጽምላቸው የነበረው፡ ሊቀ መላእክት ቅዱስ ሚካኤል ነበር። ይኹን እንጂ፡ እነርሱ፡ ለዚህ ኹሉ አምላካዊ ቸርነት፡ ውለታቢሶች በመኾን፡ ፈጣሪያቸውን አሳዘኑ፡ ይኸውም፡ ሙሴ፡ ከእግዚአብሔር ጋር ለመገናኘት፡ ወደተራራ ወጥቶ፡ ለጥቂት ቀናት፡ በሱባዔ መቆየቱን ምክንያት አድርገው፡ ካህን ወንድሙን አሮንን፡ "በፊታችን የምናስቀድመው፡ ጣዖት ካልሠራህልን!" ብለው አስጨንቀው፡ ጣዖቱን ማሠራታቸውና ማምለካቸው ነው።

እነርሱ፡ ሊጠፉበት የነበረውን የእግዚአብሔርን ቍጣ፡ ሙሴ በባለሟልነቱ አማልዶ቟ ቢያስመልስላቸውም፡ የእነርሱ፡ ማለትም፡ የእሥራኤል ልጆች ፍላጎት፡ እንደኢትዮጵያ ልጆች፡ እግዚአብሔርን፡ በእውነትና በመንፈስ ማምለክ ሳይኾን፡ እንደአሕዛብ፡ በሚታይና በሚዳሰስ ግዙፍ ነገር መኾኑን፡ እግዚአብሔር ተመለከተ፡ እንዲህ ከኾነ ብሎም፡ እርሱ፡ እግዚአብሔር፡ ቃሉን፡ በጽላት ላይ ቀርፆ፡ ያንም ጽላት፡ በግእዝ፡ "ታቦት" በሚባለው ማኅን ውስጥ እንዲያስቀምጡት አዘዞ፡ በዚያ፡ እንዲያመልኩት፡ "ታቦተ ጽዮን" የተባለችውን፡ የቃል ኪዳን ምስክር ሰጣቸው። ከዚህ የተነሣ፡ ጠላቶቻቸውን ድል ይነሡባት ዘንድ፡ እንዲህ አድርጎ በሰጣቸው፥ እርሱ፡ ለእነርሱ በሚገለጽባት፡ እነርሱም፡ እርሱን በሚያመልኩባት፡ በዚችው የጽላተ ሕግ ሃይማኖትና ምግባር ጸንተው፡ ይኼዱ ወይም አይኼዱ እንደኾነ ሊፈትናቸው፡ አርባ ዓመታት ሙሉ፡ በምድረ በዳ አንከራተታቸው። በዚያን ጊዜ፡ ለእሥራኤል ሕዝብ፡ *"አንተ፡ አንገተ ደንዳና ሕዝብ ስለኾንህ፡ በመንገድ ላይ እንዳላጠፋህ፡ እኔ፡ በአንተ መካከል አልወጣምና፡ በፊትህ፡ መልአኬን እሰድዳለሁ!"* ብሎ የመደበላቸው መልአክ፡ ቅዱስ ሚካኤል ነበረ። ይህ ኹሉ ዝክረ ነገር፡ በኦሪት ዘጸአት መጽሐፍ ውስጥ ተመዝግቦ፡ ዛሬ ድረስ እንደሚነበብ ታውቃላችሁ።

በዚያን ዘመን፡ እግዚአብሔር፡ ለወዳጆቹ፡ ለአብርሃም፥ ለይስሐቅና ለያዕቆብ፡ የገባውን ቃል ኪዳን በማሰብ፡ ለእሥራኤል ልጆች፡ ያን የመሰለ ታዳጊነቱን፡ በመልአኩ በቅዱስ ሚካኤል አገልጋይነት ያደርግ እንደነበረ፡ ዛሬ፡ "እውነተኞቹ እሥራኤል እኛ ስለኾንን፡ ይህንኑ ተራዳኢነቱን ይፈጽምልናል!" ብለው፡ የኢትዮጵያ ልጆች፡ የቅዱስ ሚካኤልን በዓል፡ በዚህ ዕለት ያከብራሉ።

# ኢትዮጵያ እና ኢትዮጵያዊነት፣
## "ፈጣሪዬ" የምለው እግዚአብሔር፡ ማነው?

---

በአገራችን፡ በኢትዮጵያ፡ በዚሁ፡ በኅዳር ሚካኤል ዕለት፡ ካህናቱ፡ በየቤተ ክርስቲያኑ፡ ጸሎተ ዕጣን እየደገሙ፡ የማዕጠንት ዕጣን የሚያሳርጉት፡ ሕዝቡ፡ በከተማ፡ ቍሻሻ የኾነውን ነገር ኹሉ እየሰበሰበ የሚያቃጥለው፡ በገጠርም፡ በየእርሻው፡ በተለይም በቆላ የሚኖረው ወገን፡ ስለወባና ወረርሽኝ፡ በየመሬቱ ላይ እሳት አንድዶ፡ ጪስ የሚያጬሰው፡ "ኅዳር ታጠነ!" የሚባለውን ይትበሃል ለማስታወስ ነው፡ የዚህም ምክንያት፡ በራእየ ዮሐንስ ተጽፎ እንደሚነበበው፡ "ሃያ አራቱ ካህናተ ሰማይ" የሚባሉት መላእክት፡ ስለዓለሙ ኹሉ ደኅንነት፡ በሰማይ፡ በጽርሐ አርያም፡ የምስጋናና የልመና ጸሎትን፡ ከዕጣን ማዕጠንት ጋር፡ በእግዚአብሔር መንበር ፊት፡ ያለማቋረጥ የሚያቀርቡትን ሥርዓት የተከተለ ነው፡ እንደዚሁ ኹሉ፡ እኛንም፡ እግዚአብሔር፡ በምድር ላይ፡ ካለፈው ዓመት፡ ከማናቸውም ዓይነት፡ ሕማምና ደዌ፡ ቸነፈርና በሽታ ጠብቆ ስላዳነን፡ ከሚመጣውም እንዲጠብቀን በማለት፡ በዚያ ሰማያዊ ሥርዓት፡ እኛም፡ ኢትዮጵያውያን፡ ለፈጣሪያችን፡ ምስጋናችንንና ልመናችንን፡ ይኸው እናቀርባለን፡ በቅርቡ፡ በአጼ ምኒልክ ዘመን ደርሶ የነበረውን፡ "የኅዳር በሽታ" የሚባለውን ከመሰለ፡ በዓመቱ ውስጥ፡ ተላላፊ የሰውና የከብት በሽታ ገብቶ፡ ሊያደርስ ከሚችለው ጥፋትና ዕልቂት "አድነን!" ለማለት፡፡

### የኅዳር ጽዮን፡፡

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስና እመቤታችን ድንግል ማርያም፡ ዓሥሩ የእግዚአብሔር ቃላት በተጻፉባቸው ጽላትና እነርሱን በያዘችው ታቦት አድረው የኖሩባትና ኪዳነ ሙሴ የምትባለው "ታቦተ ጽዮን" የምትዘከርበት በዓል፡ "ኅዳር ጽዮን" ወይም "ተዝካረ ማርያም" ተብሎ፡ በኅዳር ፳፩ ቀን ይከበራል፡፡

"ኅዳር ጽዮን" ተብላ፡ በኅዳር ፳፩ ቀን መከበርዋ፡ "እውነተኛዋ ታቦተ ጽዮን" እርሷ፡ ቅድስት ድንግል ማርያም መኾኗን ለማመልከት ብቻ ሳይኾን፡ "አማናዊቷ ቤተ መቅደስ"ም፡ እርሷው መኾኗን፡ አረጋግጦ ለማሳመን ነው፡፡ ይኸውም፡ የቃል ኪዳን ልጆቿ እንደኾኑት፡ እንደኢትዮጵያውያን የቀን አቈጣጠር፡ በመስከረም ፩ ቀን የተወለደችውን ድንግል ማርያምን፡ ወላጆቿ፡ እንደኦሪቱ ሥርዓት፡ በ፹ (ሰማንያ) ቀኗ፡ በእግዚአብሔር ፊት ሊያቀርቧት፡ በሕፃንነቷ፡ ወደቤተ መቅደስ የገባችበት ዕለት መታሰቢያ ጭምር መኾኑን ልታውቁት ያስፈልጋችኋል፡፡

ቀደም ብሎ እንደተገለጸው፡ በብሉዩ ኪዳን፡ ለእሥራኤል ሕዝብ መመኪያና ለድል አድራጊነታቸው ዋስትና ኾና፡ ስትጠብቃቸው የቆየችው፡ ይህችው "ጽላተ ኪዳን"፡ ከእነርሱ ተወስዳ፡ ለኢትዮጵያውያን ተሰጥታለች፡ ይህም የኾነው፡ በእርሷ ምስክርነት፡ እሥራኤላውያን፡ ከእግዚአብሔር ጋር ለተጋቡት ቃል ኪዳንና እርሷን በባለአደራነት ጠብቀው ለማኖር፡ የበቁና የታመኑ ኾነው ባለመገኘታቸው ነው፡፡

# ምዕራፍ ፮፤ በዓል።
## ዓበይትና ንዑሳን በዓላት።
### የኅዳር ጽዮን።

---

በዚያች፡ እንዲት በኾነችው መንታ ጽላት ላይ፡ በመለኮት ጣቶች የተጻፈው፡ የእግዚአብሔር ቃል፡ የአዲሱ ኪዳን ሕያውት ጽላት በኾነችው በድንግል ማርያም ማሕፀን ላይ ተቀርፆ፡ በሰውነት በተወለደ ጊዜ፡ የዚያች፡ የብሉዩ ኪዳን "ታቦተ ጽዮን"፡ ተልእኮዋን ለመፈጸም በቅታለች።

ስለዚህ፡ እኛ ኢትዮጵያውያን፡ ለምድራዊው ህልውናችን ብቻ ሳይኾን፡ ለሰማያዊው የዘለዓለም ሕይወታችን፡ አማናዊቷ (እውነተኛዋ) መመኪያችንና የድል አድራጊነት ዋስትናችን የኾነችው፡ ሕያዋ ታቦተ ጽዮን፡ እርሷ፡ "ቅድስት ድንግል ማርያም ናት!" ብለን አምነን፡ እነሆ፡ በዓሏን፡ በተለየ አንክሮና ተመስጦ እናከብረዋለን። ይህ በዓል፡ ምንም እንኳ፡ በመላዋ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን፡ አድባራትና ገዳማት፡ በገጠሩም ሳይቀር፡ በከፍተኛ መንፈሳዊ ስሜት የሚከበር ቢኾን፡ ወደኢትዮጵያ መጥታ፡ ከቆየችባቸው ቅዱሳት መካናት በኋላ፡ በመጨረሻ፡ ባረፈችበትና "የታቦተ ጽዮን መዲና" በተባለችው፡ በአኵስም፡ "እምነ ጽዮን"፡ ማለትም፡ "እናታችን ጽዮን" እየተባለች፡ በተለየ ደማቅ ሥርዓት ትከበራለች።

## ዘመነ ነቢያት።

"ዘመነ ነቢያት"፡ ከጾመ ነቢያት ጋር፡ ታኅሣሥ ፩ ቀን በሚውለው፡ በ"ዕለተ ትስብእት" ይጀምርና ልክ፡ ከአርባ ዕለታት በኋላ፡ ጥር ፲ ቀን ያበቃል፡ ይህም ቀን፡ "ከተራ" የሚባለው፡ የጥምቀት ዋዜማ ነው።

በዚች ወራት፡ ስለሚከበሩት በዓላት፡ የሚከተለውን ማብራሪያ አቅርቤላችኋለሁ፡-

## ዕለተ ትስብእት።

*ጥያቄ፡- "ዕለተ ትስብእት" ስለሚባለው፡ ስለቃሉ ትርጉም፡ ስለምሥጢሩም፡ በበለጠ ልታሳውቀን የሚያስፈልግ ይመስለናልና፡ እዚህ ላይ፡ አግባብነት ያለውን ሓተታ እንድትሰጥበት እናሳስብህ ዘንድ ፍቀድልን?*

**መልስ፡- "ትስብእት"፡ "ቃል ሥጋ ኾነ!" ማለት ነው፡ አምላክ፡ ሰው የመኾኑ ትንቢት የተፈጸመበት፡ ምሥጢሩም የተገለጸበት የመለኮት ሥራ ነው፡ ባጭሩ፡ የ"ምሥጢረ ሥጋዌ" ሌላው ስሙና ገጽታው ነው ሊባል ይቻላል።**

**በእውነተኛውና በትክክለኛው የቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያውያን ሥርዓት፡ ታኅሣሥ ፩ ቀን የሚውለው "ዕለተ ትስብእት"፡ ድንግል ማርያም፡ ኢየሱስ ክርስቶስን የጸነሰችባት ዕለት ናት። በዚች ዕለት፡ እግዚአብሔር፡ በመልኩ ለፈጠረው የሰው ዘር ያዘጋጀው፡ ይህ ታላቅ ቸርነቱ ይፈጸምባት ዘንድ ወድዶ በመረጣት ቅድስት ድንግል ዘንድ፡ የኾነውንና የተደረገውን ድንቅ ነገር፡ ዝክረ ነገሩ፡ ሲወርድ ሲዋረድ በደረሰን፡ እንዲህ በሚለው የትውፊት ቃል እጀምርላችኋለሁ፡-**

# ኢትዮጵያ እና ኢትዮጵያዊነት፤
## “ፈጣሪዬ” የምለው እግዚአብሔር፡ ማነው?

*“ናሁ፡ ድንግል ትፀንስ! ወትወልድ ወልደ!”* ማለትም፡ “እነሆ፡ ድንግል ትፀንሳለች! ወንድ ልጅም ትወልዳለች!” ተብሎ፡ በነቢያት የተነገረው ትንቢት የሚፈጸምበት ጊዜ ሲደርስ፡ እመቤታችን፡ ቅድስት ድንግል ማርያም፡ “ውኃ ስትቀዳ” ይላል፡ “በቤተ ዮሴፍ”ም ይላል፡ “በቤተ መቅደስ”ም ይላል፡ የእግዚአብሔር መልአክ፡ “ትፀንሲ!” “ትፀንሻለሽ!” አላት።

“ይህ፡ እንደምን ነው?” ቢሉ፡ ኹሉም ተደርጓል። ከእሥራኤል ደናግል ጋራ ውኃ ልትቀዳ ኼዳ፡ ስትመለስ፡ የተጠማ ውሻ ስላገኘች፡ ከቀዳችው ውኃ፡ ጨልፋ፡ በጫማዋ አጠጥታዋለች፡ “ርኅርኅተ ልብ” ያሰኛት፡ አንዱ ምግባርዋ፡ ይህ ነው። በዚህ ጊዜም፡ አብረዋት ከነበሩት ደናግል መካከል፡ አንዳንዶቹ “እንቴ! ይህን ያህል ርኅራኄ እንዴት ነው? ‘የዚህ ወራት፡ አምላክ፡ ከድንግል ይወለዳል!’ ይባላል፡ ከአንቺ ይኾን?” አሏት። ወዲያው፡ መልአኩ ተገልጦ፡ “ትፀንሲ!” “ትፀንሻለሽ!” አላት። ዝም ብላ ኼደች። ከቤት ደርሳ፡ ውኃውን ስታወርድ፡ መልአኩ፡ እንደገና፡ “ትፀንሲ!” “ትፀንሻለሽ!” አላት። “ይህ ነገር፡ ደጋገመኝ! እስቲ፡ ከቤተ መቅደስ ኼጄ፡ ልረዳው!” ብላ፡ ከእሥራኤል ደናግል ጋራ ተካፍላ፡ እያስማማች የምትፈትለው፡ ሐርና ወርቅ ነበር፡ ያን ይዛ፡ ወደቤተ መቅደስ ኼደች። በቤተ መቅደስ ተቀምጣ፡ ሐርና ወርቁን እያስማማች ስትፈትል፡ አሁንም እንደገና፡ “ትፀንሲ!” “ትፀንሻለሽ!” አላት።

ይህም መልአክ፡ ካህኑ ዘካርያስ፡ ሚስቱ ኤልሣቤጥ፡ መጥምቁ ዮሐንስን የምትፀንስ ስለመኾኗ፡ ከእግዚአብሔር ዘንድ የመጣለትን መልእክት በነገረው ጊዜ፡ ቃሉን በመጠራጠሩ፡ *“ይህችን ምሥራች እንድነግርህ የተላክሁ፡ እኔ፡ በእግዚአብሔር ፊት የምቆመው፡ ገብርኤል ነኝ!”* ያለው፡ ሊቀ መላእክት ነው። ይኸው መልአክ፡ ለኤልሣቤጥ ካበሠራት፡ ከስድስት ወራት በኋላ፡ በዚች ዕለት፡ ለድንግል ማርያም ተገልጦላት፡ በሦስተኛው ጊዜ፡ በቤተ መቅደስ፡ *“እነሆ ትፀንሻለሽ፡ ወንድ ልጅንም ትወልጃለሽ፡ ስሙንም፡ ‘ኢየሱስ’ ትዪዋለሽ፡ እርሱ፡ ታላቅ ይኾናል፡ ‘የልዑል ልጅ’ም ይባላል፡ እግዚአብሔር አምላክም፡ የአባቱን፡ የዳዊትን ዙፋን ይሰጠዋል፡ በያዕቆብ ቤትም ላይ፡ ለዘለዓለም ይነግሣል፡ ለመንግሥቱ፡ መጨረሻ የለውም።”* ብሎ፡ እግዚአብሔር አምላክ፡ ከእርሷ፡ ሰው ኾኖ የመወለዱን ምሥጢር ገልጦ አበሠራት።

በዚህ ጊዜ፡ እርሷም፡ *“ወንድ ስለማላውቅ፡ ይህ እንዴት ይኾንልኛል?”* ብላ መልሳ፡ በልቧ ያለውን የእውነት ጥያቄ አቀረበችለት። ድንግል ማርያም፡ ይህን ጥያቄ ለመልአኩ ማቅረቧ፡ ተጠራጥራው አይደለም፤ “እኔ፡ ይህን ነገር፡ እንኳን ሳደርገው፡ ስለማላስበውም፡ እንደምን ሊኾን ይችላል?” ስትለው ነው።

መልአኩም፡ *“መንፈስ ቅዱስ፡ በአንቺ ላይ ይመጣል፤ የልዑልም ኃይል ይጸልልሻል፡ ስለዚህ ደግሞ፡ ከአንቺ የሚወለደው ቅዱሱ፡ ‘የእግዚአብሔር ልጅ’ ይባላል፡ እነሆም፡ ዘመድሽ ኤልሣቤጥ፡ እርሷ ደግሞ፡ በእርጅናዋ፡ ወንድ ልጅን ፀንሳለች፡ ‘መካን’ ትባል ለነበረችው፡ ለእርሷ፡ ይህ፡ ስድስተኛ ወር ነው፤ “ለእግዚአብሔር የሚሳነው ነገር የለምና!”* የሚለውንና ሌላ ጥያቄ ሊያስከትል የማይችለውን አጥጋቢ ምላሽ ሰጣት።

# ምዕራፍ ፳፱፤ በዓል።
## ዓበይትና ንኡሳን በዓላት።
### ዕለተ ትስብእት።

---

እርሷም፡ ወዲያ ወዲህ የማያሰኘውን፡ ይህን፡ መልአካዊ መልስ ስላገኘች፡ አፍአዊውና ውሳጣዊው ኹለንተናዋ ረክቶ፡ ወዲያው፡ *"እነሆኝ የእግዚአብሔር ባሪያ! እንደ ቃልህ ይኹንልኝ!"* ብላ፡ መለኮታዊዉን መልእክት ለመቀበል፡ ፍጹም ዝግጁነቷንና ቁርጥ ፈቃደኛነቷን፡ ለሰማያዊው መልእክተኛ አሳወቀችው። ልክ፡ በዚች ዕለት፡ ከዕለቷም፡ ይህን ቃሏን፡ ከልቦናዋ አፍልቃ፡ በአንደበቷ ባሰማችባት፡ በዚች ቅጽበት፡ እግዚአብሔር ወልድ፡ በማሕፀኗ ተፀነሰ።

ስለዚህ፡ ፈጣሪ፡ ፈቃዱ ኾኖ፡ እንደተሰፋ ቃሉ፡ አምላካዊ አካሉንና ባሕርዩን፡ በንጽሕት ድንግል ማሕፀን ውስጥ፡ ከፍጡሩ፡ ሰብአዊ አካልና ባሕርይ ጋር አዋሕዶ፡ በፍጹም ሰውነት የተፀነሰባት፡ ይህች ዕለት፡ "ዕለተ ትስብእት" ተብላለች።

## ብሥራተ ገብርኤል።

"ዕለተ ትስብእት" የተባለችው፡ ይህችው፡ ታኅሣሥ ፳፪ ቀን፡ ሊቀ መላእክት ቅዱስ ገብርኤል፡ እግዚአብሔር ወልድ፡ በማሕፀኗ ተቀርጾና ሰው ኾኖ፡ ከእርሷ የሚወለድ የመኾኑን ምሥራች፡ ከእግዚአብሔር አብ ተልኮ፡ ለቅድስት ድንግል ማርያም ያሰማባት ዕለት ስለኾነች፡ "ብሥራተ ገብርኤል" ተብላ በታላቅ ክብርና ሐሴት ትዘከራለች፡ ትከበራለች።

## ፅንሰታ ለማርያም።

የቅድስት ድንግል ማርያም፡ አረጋውያን ወላጆች፡ ኢያቄምና ሐና፡ መካኖች በመኾናቸው፡ ፈጣሪያቸው እግዚአብሔር፡ ልጅ እንዲሰጣቸው፡ በሃይማኖት ተስፋ ጸንተው፡ በጾም፡ በጸሎትና በምጽዋት ምግባራትም ተወስነው ከኖሩ በኋላ፡ የለመኑትን የማይነሣው፡ የነገሩትንም የማይረሳው፡ ይኸው አምላካቸው፡ በሃይማኖታዊ ምግባራቸው፡ ለፍጹምነት የበቃውን ልመናቸውን ተቀብሎ፡ የሐና ማሕፀን፡ ለአምላክ እናትነት የተመረጠችውን፡ ድንግል ማርያምን ይፀንስ ዘንድ፡ በቅድስናው ከፍቶ፡ በታኅሣሥ ፫ ቀን፡ እመቤታችን ተፀነሰች፡ ያችም ዕለቷ፡ "ፅንሰታ ለማርያም" ተባለች።

## ስለቅድስት ድንግል ማርያም ፅንሰት።

**ጥያቄ:-** ስለቅድስት ድንግል ማርያም፡ ከፅንሰቷ ጀምረህ፡ ልናውቀው የሚገባንን፡ ዝክረ ነገርዋን፡ እዚህ ላይ ብታሰማን?

**መልስ:-** የእመቤታችን፡ የቅድስት ድንግል ማርያም፡ የምዝላቶቿ፡ ምዝላቶች ከኾኑት፡ ከኢትዮጵያውያኑ የተገኙት፡ ቅድመ ቅድም አያቶቿ፡ በጥሪቃና ቴክታ ይባላሉ። ይህ ቀራቸው የማይባሉ፡ ባለጸጎች ነበሩ።

ሀብታቸውም፡ በወርቅና በብር ሚዛን፡ በቀንድና በጋማ ከብት መጠን ብቻ የሚወሰን ሳይኾን፡ በወንድና በሴት አገልጋዮችና ሠራተኞች ብዛትም ጭምር የሚለካ ነበር፡ አንዱን ዓይነት፡ በምሳሌነት ለመጥቀስ፡ ከብዛቱ የተነሣ፡ ወርቁን፡ እንደአምባርና እንደቀለበት እየሠሩ፡ ከበሬውና ከላሙ ቀርን (ቀንድ) ላይ ያጠልቁት ስለነበር፡ የወርቁም፡ የከብቱም ብዛት፡ ይህን ያህል፡ "አቅርንተ ወርቅ" (የወርቅ ቀንዶች)፡ ይህን ያህል፡ "አቅርንተ ብሩር" (የብር ቀንዶች) ተብሎ ይቈጠር ነበር እንጂ፡ የቀረው አይቈጠርም ነበር።

ከዕለታት አንድ ቀን፡ በጥሪቃ፡ ገንዘባቸው ከሚገኝበት ግምጃ ቤቱ ገብቶ፡ የገንዘቡን ብዛት ከተመለከተ በኋላ፡ ሚስቱን፡ "ቴክታ! እኔ መኻን! አንቺ መኻን! ይህ ኹሉ ገንዘብ ለማን ይኾናል?" አላት። እርሷም፡ "እግዚአብሔር እንጂ፡ ከእኔ ባይሰጥህ፡ ወይ፡ ከሌላ ይሰጥህ ይኾናልና፡ ለምን አግብተህ፡ አትወልድም?" አለችው። እርሱም፡ "ይህንስ እንዳላደርገው፡ የአባቶቻችንና እናቶቻችን አምላክ ያውቃል!" አላት።

በዚህ ጊዜ፡ ኹለቱም አዘኑ። ወዲያው፡ ከሌሊቱ በአንዱ፡ ራእይ አይተዋል፡ ራእዩም፡ እንዲህ የሚል ነበረ፦ "ነጭ እንቦሳ፡ ከበረታቸው ስትወጣ፡ እንቦሳዪቱ፡ እንቦሳ እየወለደች፡ እስከስድስት ስትደርስ፡ ስድስተኛዪቱ፡ ጨረቃን፡ ጨረቃ፡ ፀሓይን ስትወልድ አይተው፡ ወደመፈክረ ሕልም (ሕልም ፈቺ) ኼደው ነገሩት። እርሱም፡ "ደግ ልጅ ትወልዳላችሁ! ከዚያም፡ እስከስድስት ትውልድ፡ እንደእርሷ፡ ደጋግ የኾኑ የልጅ ልጆችን ታገኛላችሁ! ስድስተኛዪቱ ጨረቃ፡ ከፍጡራን በላይ የምትኾን ልጅ ትወልዳላችሁ! የሰባተኛዋ፡ የፀሓይ ነገር፡ ግን፡ አልተገለጸልኝም፡ እንደነቢይ፡ እንደንጉሥ ያለ፡ ይኾናል!" አላቸው። እነርሱም፡ "ጊዜ ይተርጕመው!" ብለውት፡ ወደቤታቸው ተመለሱ።

ከዚህ በኋላ፡ እግዚአብሔር፡ የባልና ሚስቱን፡ የኀዘን ጸሎት ሰማ፡ እነሆ፡ ቴክታ ጸነሰች! ሴት ልጅንም ወለደች! "ምኞቴ ተፈጸመልኝ! ስእለቴም ደረሰልኝ!" ስትል፡ ለዚህች የስእለት ልጇ፡ "ሄኤሜን" የሚል ስም አወጣችላት። "ሄኤሜን"ም፡ ሴት ልጅን ወለደች፡ ይህች ልጇም፡ የልጅ ልጅ ጰይታ፡ ያች የወለደቻት ልጅ፡ "ሄርሜላ" ተብላ፡ እርሷ ደግሞ፡ የእመቤታችንን እናት፡ "ሓና"ን ወለደች።

ሓና፡ አካለ መጠን ስታደርስ፡ ከቤተ ይሁዳ ለተወለደ፡ "ኢያቄም" ለሚባል፡ ደግ ሰው አጋቢት። ምክንት፡ የምዝላቶቿ፡ ምዝላቶች ከኾኑት፡ ቅድመ አያቶቿ ወርዶ፡ እርሷ ላይ ሲደርስ፡ እንደእነርሱ መኻን ኾነች፡ ከዚያውም ጋር፡ በሀብቱ ቦታ፡ ድህነቱ ተተክቷል። ይህንም፡ ከዚህ የሚከተለው ዝክረ ነገር ያረጋግጣል።

የድኅነታቸው መጠን ወደምን ዓይነቱ ዝቅተኛ ደረጃ እንደወረደ የሚያሳየው፡ ሓና፡ ወደውጭ ለብሳ የምትኼደው ልብስ እስከማጣት መድረሷ ነበር፣ ለመሳለምና የተለመደ ጸሎቷን ለማድረስ እንኳ፡ ወደእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ ለመኼድ ካልቻለችበት ችግር ላይ ወድቃ ነበር።

# ምዕራፍ ፮፤ በዓል፡፡
## ዓበይትና ንዑሳን በዓላት፡፡
### ፅንሰታ ለማርያም፤ ስለቅድስት ድንግል ማርያም ፅንሰት፡፡

---

በእንደዚህ ያለ ኹኔታ ላይ ሳለች፡ ከዕለታት አንድ ቀን፡ የምትወድደው በዓሏ የኾነውን ቀን ለማክበር ይኹን፡ ወይም በልቡናዋ ያለውን ምኞቷን ይፈጽምላት ዘንድ፡ ስእለቷን ለአምላኳ ልታቀርብ፡ ወይም፡ በሌላ፡ ባልታወቀ፡ የሚገፋፋ ምክንያት፡ በግድ ወደእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ ለመኼድ ፈልጋ ተነሣች፤ ነገር ግን፡ ለዚያ ልዩ ቀን የሚኾን ማለፊያ ልብስ ስላልነበራት፡ ይህም ማጣቷ፡ ከዚያ ካሰበችው ዓላማዋ፡ ሊያስቀራት የሚችል ምክንያት ኾኖ ስላገኘችው፡ እጅግ አዘነች፡፡

ይህን ችግርዋን ለማስወገድ ስለምትችልበት መንገድ፡ በልቡናዋ፡ ስታወጣና ስታወርድ፡ የመጣላት መፍትሔ አንድ ብቻ ኾኖ አገኘችው፡ ይኸውም፡ ይህንኑ ችግሩዋን፡ በዝሙት ለምትኖር፡ ለአንዲት ጎረቤቷ ማዋየት ኾነባትና፡ በዚሁ አሳቧ ቆርጣ፡ እንዲህ ስትል፡ ችግሩዋን፡ ለዚያችው ጎረቤቷ አዋየቻት፦ "ዛሬ፡ ወደቤተ መቅደስ ኼጄ፡ እሳለማለሁ ብዬ አስቤ ነበር፡ ነገር ግን፡ ለብሼው የምኼደው ልብስ ስለሌለኝ፡ የምችል አይመስለኝም፡፡" ያች ጎረቤቷም፡ "ልብስማ፡ የእኔ፡ ከአንድ፡ ኹለት፡ ሦስት ያለልሽ አይደለምን? ለምን፡ ከእነዚያ፡ አንዱን መርጠሽ፡ ያንን ለብሰሽ፡ አትኼጂም?" አለቻት፡፡ ሐናም፡ በቅን ኅሊና፡ በየዋህ ልቡናና በትሑት ሰብእና፡ "አይ! ያማ አይኾንም! ያንቺ ልብስኮ የተሰበሰበው፡ በዐስበ ደነስ (በኃጢአት ዋጋ)፡ በዐስበ ዝሙት (በዝሙት ዋጋ) ነው፤ እግዚአብሔር ደግሞ፡ ንጹሓ ባሕርይ ነውና፡ ንጹሕ ነገር ይወድዳል፡ ይህን፡ ያንቺን ልብስ ለብሼ ብለምነው፡ 'እንዴት ይሰማኛል' ብዬ ነዋ!" አለቻት፡፡ ሴቲቱም፡ "ሐና! እኔ፡ 'በምን ምክንያት፡ ልጅ ነሣት?' እያልሁ፡ ሳዝንልሽ እኖር ነበር፡ ለካ፡ እንዲህ፡ እንደደንጊያ፡ አድርቆ ያስቀረሽ፡ ይህ ክፋትሽ ኖሯልና!" አለቻት፡፡ ሐናም፡ በዚህ፡ እጅግ አዘነች፡፡

ይህን ኀዘኗን የሚያባብስ፡ ሌላ ድርጊት ደግሞ፡ አጋጠማት፡ ይህም፡ ካላሰበችው አግጣጫ የተሠነዘረ ነበር፡፡ ኢያቄምና ሐና፡ ኹለቱም ኹሉ፡ "ለእግዚአብሔር፡ መሥዋዕት እናቀርባለን!" ብለው፡ ወደቤተ መቅደስ ኼዱ፡ ሊቀ ካህናቱ፡ "ሮቤል" ይባላል፡፡ እርሱም፡ "እናንተማ፡ 'ብዙ! ተባዙ!' ብሎ፡ እግዚአብሔር፡ ለአዳም የነገረውን፡ የበረከት ቃል ያስቀረባችሁ፡ ርጉማን አይደላችሁምን? ቢጠላችሁ ነው እንጂ፡ ቢወድዳችሁማ፡ ልጅ ይሰጣችሁ አልነበረምን? ስለዚህ፡ መሥዋዕታችሁን አልቀበልም!" ብሏቸዋል፡፡ ከዚህ በቀር፡ የእሥራኤል ሽማግሎች፡ ወላጆች የኾኑት ብቻ የሚመገቡት፡ ተረፈ መሥዋዕት (ከመሥዋዕቱ የሚተርፍ) ነበር፡ ያንንም እንዳይሳተፉ፡ ይኸው ሊቀ ካህናት ከልክሏቸዋል፡፡ በዚህ ኹሉ፡ ተደራራቢ ኀዘን ደርሶባቸው፡ በትካዜ ተመልሰዋል፡፡

ከቤተ መቅደስ ሲመለሱ፡ በመንገዳቸው ላይ፡ እንዲህ፡ በኀዘንና በትካዜ ተውጠው፡ ከዛፍ ጥላ ሥር፡ ዐረፍ ብለው ሳሉ፡ ሐና፡ ርግቦች፡ ከልጆቻቸው ጋር የሚያደርጉትን ጨዋታ፡ ዛፎችም፡ አብበውና አፍርተው፡ የሚያሳዩትን የሥነ ፍጥረት ውበት ተመልክታ፡ "አቤቱ! ርግቦችን፡ በባሕርያቸው እንዲዋለዱ፡ ዕፅዋትንም፡ በተፈጥሮአቸው እንዲያብቡ፡ እንዲያፈሩ የምታደርግ አምላክ፡ የእኔ ምንነቴ፡ ከደንጊያ የተሠራ ይመስል፡ ልጅ የነሣኸኝ፡ ለምን ይኾን?" ብላ አዘነች፡፡

# ኢትዮጵያ እና ኢትዮጵያዊነት፣
## "ፈጣሪዬ" የምለው እግዚአብሔር፡ ማነው?

---

ኹለቱም፡ ከቤታቸው ሲገቡ፡ ተነጋገሩና፡ "ወንድ ልጅ ብንወልድ፡ 'ወጥቶ ወርዶ፡ አርሶ ቆፍሮ፡ ይርዳን!' አንልም፡ ለቤተ እግዚአብሔር፡ አንጣፊ፡ ጋራጅ ኾኖ ይኖራል፡ ሴት ብንወልድ፡ 'ዕንጨት ሡብሬ፡ ውኃ ቀድታ ትርዳን!' አንልም፡ ለቤተ እግዚአብሔር፡ መሶበ ወርቅ ሰፍታ፥ መጋረጃ ፈትላ ትኑር!" ብለው፡ ብፅዓት ገብተዋል።

ኢያቄምና ሐና፡ ከቀደሙት አያት ቅድመ አያቶቻቸው ራእይ የረቀቀ፡ ሌላ ራእይ፡ በየበኩላቸው ያዩ፡ ይህም የኾነው፡ የሐምሌ አመ ፴ (የወሩ ማብቂያ) ዕለት ነበር። በዚች ዕለት ሌሊት፡ እርሷ፡ ለእርሱ፡ "ፀምር ሲያስታጥቁህ (ከበግ ፀጕር የተሠራ ማለፊያ ልብስ፡ ማለትም፡ በርኖስ ሲያለብሱህ)፡ መቋሚያህ አፍርታ፡ ፍጥረት ኹሉ ሲመገባት አየሁ!" ብላ፡ እርሱ ደግሞ ለእርሷ፡ "ነጭ ርግብ፡ ሰባቱን ሰማያት ሠንጥቃ መጥታ፡ በራስሽ ላይ ስታርፍ፡ በቀኝ ጆሮሽ ገብታ፡ በማሕፀንሽ ስታድር አየሁ!" ብሎ፡ ኹለቱም፡ ያዩትን ራእይ ተጨዋውተዋል። ወደሕልም ፈቺ ኼደው፡ እንዲተረጕምላቸው ቢነግሩት፡ "ደግ ልጅ ትወልዳላችሁ!" ከማለት በቀር፡ አስተካክሎና አሟልቶ ሊፈታላቸው አልቻለም። እነርሱም፡ "አንተስ አልፈታኸውም፡ ጊዜ ይፍታው!" ብለው፡ ወደቤታቸው ተመለሱ።

እነርሱም፡ የራእያቸውን ፍጻሜ፡ በሃይማኖት ተስፋና በትዕግሥት ምግባር፡ እየተጠባበቁ ሳሉ፡ የእግዚአብሔር መልአክ መጥቶ፡ "ደግ ልጅ ትወልዳላችሁ!" ብሏቸው፡ እመቤታችን ድንግል ማርያም፡ በብሥራተ መልአክ፡ በፈቃደ አምላክ፡ ታኅሣሥ ፯ ቀን ተፀነሰች። በተፀነሰችም ጊዜ፡ ብዙ ታምራት ተደርጓል። ከእነዚህም መካከል፡ ጥቂቶቹን፡ እዚህ ላይ እጠቅሳችኋለሁ፡

ለሐና፡ "ቤርሴባ" የምትባል አክስት ነበረቻት፡ አንድ ዓይና ነች፡ "ሐና! እግዚአብሔር፡ በረድኤት ጐበኘሽ መሰለኝ! ጡትሽ፡ ጠቍርዋል፡ ከንፈርሽም፡ አርሩዋል፡" ብላ ማሕፀኗን ዳስሳ፡ ዓይኗን ብታሸው፡ በርቶላታል። ይህን፡ አብነት አድርገው፡ሕሙማን ኹሉ፡ የሐናን ማሕፀን እየዳሰሱ፡ የሚፈወሱ ኾነዋል። ዳግመኛም፡ "ሳምናስ" የሚባል፡ ያጎቷ ልጅ ነበር፡ ሞተ፡ ትወድደው ነበርና፡ ያልጋውን ሸንኮር ይዛ፡ እየዞረች ስታለቅስ፡ ጥላዋ ቢያርፍበት፡ ተነሥቶ፡ "የሰማይና የምድር ፈጣሪ አያት ሆይ! ሰላም ለአንቺ ይኹን!" ብሎ፡ ከዚያ የሕልም ፈቺ የቀረውን ተርጕሞላታል።

## በአታ ለማርያም።

ሕፃን ማርያም፡ በቅዱሳን ወላጆቿ ስእለት፡ እግዚአብሔርን ልታገለግል የተሰጠች፡ የብፅዓት ልጅ ስለኾነች፡ በሦስት ዓመቷ፡ ወደቤተ መቅደስ ገብታ፡ በዚያ፡ የ፲፪ ዓመታት ኑሮዋን የጀመረችበት፡ ታኅሣሥ ፫ ቀን፡ "በአታ ለማርያም" ተብላ ትከበራለች።

## ድንግል ማርያም፡ በስእለት የተገኘች ልጅ ስላመኾኗ።

*ጥያቄ፡- ድንግል ማርያም፡ በስእለት የተገኘች ልጅ ስለመኾኗ፡ ዘርዝሮና አስፋፍቶ የሚያስረዳውን ዝክረ ነገር፡ ከዚሁ ጋር አያይዘህ ብትነግረን?*

መልስ፡- በዚህች በዓል ዕለት ሊታሰብና ሊነገር የሚገባው፡ የቅድስት ድንግል ማርያም፡ የዜና መዋዕሏ የመጀመሪያ ክፍል፡ እንዲህ ነው፡-

ሕፃን ማርያም፡ በተወለደች፡ በሦስት ዓመቷ፡ እናቷ ሐና፡ አባቷን ኢያቄምን፡ "ይህች ብላቴና፡ ሆዷ፡ ዘመድ ሳይወድድ፡ አፏ፡ እህል ሳይለምድ፡ ለእግዚአብሔር በገባነው ቃል መሠረት፡ ወስደን፡ ለቤተ መቅደስ አንሰጣትምን? 'የሰጠ ቢነሣ፡ የለበት ወቀሳ!' እንዲሉ፡ አንዳች ነገር ብትኾንብን፡ ከልጃችንም፥ ከእግዚአብሔርም ሳንኾን እንዳንቀር!" አለችው። እርሱም፡ "ፍቅርሽ ይለቅልሽ ብዬ ነው እንጂ፡ እኔማ፡ ፈቃዴ አይደለምን?" አላት። ከፍቅሩዋ ጽናት የተነሣ፡ ሐና፡ ሕፃን ማርያምን፡ ከጭኑዋ አውርዳት አታውቅም ነበር። ምክንያቱም፡ አንድ ቀን፡ ብቻዋን፡ ከቤት ውስጥ ትታት፡ ከደጅ ወጥታ ብትመለስ፡ የእግዚአብሔር መልአክ ሠውሮባት፡ ጥራ፡ ግራ አግኝታት ስለነበረ ነው፤ ከዚያ በኋላ፡ ያው እየመሰላት፡ ተለይታት አታውቅም።

ወላጆቿ፡ ይህን ተነጋግረው እንዳበቁ፡ ሕፃን ልጃቸውን፡ ማርያምን ወስደው፡ ለቤተ መቅደስ ሰጧት። በዚያን ጊዜ የነበረው ሊቀ ካህናት፡ ዘካርያስ ይባላል፤ እርሱም፡ ስለምግቧ ነገር ሊያስወስን፡ መጥቅዕ (ደወል) ደውሎ፡ ሕዝቡን ሰብስቦ፡ እየተወያዩ ሳለ፡ የእግዚአብሔር መልአክ፡ ሊቀ መላእክት ቅዱስ ፋኑኤል፡ የሰማይ ኅብስትና የሰማይ ጽዋ ይዞ፡ ከሰማይ ወርዶና ረብቦ ታየ፤ በዚህ ጊዜ፡ ሊቀ ካህናቱ ዘካርያስ፡ ለእርሱ የወረደለት ሀብት መስሎት፡ ሊቀበል ቢነሣ፡ ወደላይ ራቀበት፤ የሊቀ ካህናቱ ተወራጅ፡ ስምዖን ይባላል፡ እርሱም፡ ለመቀበል ቢነሣ፡ ወደላይ ራቀበት።

ከዚህ በኋላ፡ "ጥበበ እግዚአብሔር፡ ምሥጢሩ አይመረመርምና፡ ምናልባት፡ ለዚህች ብላቴና የመጣ ሀብት እንደኾነ፡ ማን ያውቃል? እስቲ እንየው!?" ብለው፡ ለብቻዋ አድርገዋት፡ ፈቀቅ ቢሉ፡ ድንኾል፥ ድንኾል እያለች፡ እናቷን ስትከተል፡ መልአኩ፡ ፈጥኖ ወርዶ፡ አንድ ክንፉን፡ አንጥፎ፡ አንድ ክንፉን ደግሞ፡ ጋርዶ፡ በሰው ቁመት ያህል፡ ከምድር አስለቅቆ፡ ከፍ አድርጓትና መግቧት ዐረገ። ከዚህ በኋላ፡ ካህናቱና ሕዝቡ፡ "የምግቧ ነገር፡ እንዲህ ከተያዘልንማ፡ ከሰው ጋራ ምን ያጋፋታል?" ብለው፡ ሕፃን ማርያምን፡ ከወላጆቿ ተቀብለው፡ ወደቤተ መቅደስ አግብተዋት፡ በዚያ፡ አሥራ ኹለት ዓመት ኖራለች።[፻፺፯]

## የታኅሣሥ ገብርኤል::

በዚሁ በታኅሣሥ ወር፡ በ፲፱ኛው ቀን የሚውለው፡ የ"ታኅሣሥ ገብርኤል" በዓል፡ የሚከበርበት ምክንያት እንዲህ ነው:-

እግዚአብሔር፡ በሙሴ መሪነት፡ የእሥራኤልን ሕዝብ፡ በግብፅ አገር፡ ይገኙበት ከነበረው የባርነት አገዛዝ፡ ነጻ አውጥቶ፡ ቤተ መቅደሳቸውንና ከተማቸውን፡ በኢየሩሳሌም አድርገው፡ በምድረ ከነዓን እንዲኖሩ አበቃቸው:: እነርሱ ግን፡ ባካባቢያቸው ያሉትን አሕዛብ እየተከተሉ፡ አምልኮ ባዕድን በመፈጸም፡ አምላካቸውን እግዚአብሔርን አሳዘኑት:: በነቢያቱ፡ ቢመክራቸውና ቢገሥፃቸውም፡ በዚያ ኃጢአታቸው እየጨመሩበት ከመኼድ በቀር፡ ከበደላቸው፡ ተጸጽተው ሊመለሱ፡ ጨርሶ የማይቻል ኾነ::

በዚህ መልክ፡ በፈጣሪያቸውና ከእርሱ ጋር በተጋቡት ቃል ኪዳናቸው ላይ፡ በሥውርና በገሃድ ያካኼዱት የነበረው ክህደት፡ ዓመፅና አመንዝራነት፡ በመጨረሻ፡ ጽዋው ስለሞላ፡ እግዚአብሔር፡ ለዚህ ድርጊታቸው፡ ምስክር የኾነችው ታቦተ ጽዮን፡ ከእሥራኤላዊው ንጉሥ፡ ከሰሎሞንና ከኢትዮጵያዊቷ ንግሥት፡ ከማክዳ በተወለደው፡ በቀዳማዊ ምኒልክ አማካይነት፡ በቅድሚያ፡ ወደኢትዮጵያ እንድትኼድ አደረገ:: ከዚያ በኋላም፡ ያወረሳቸውን አገርና ከተማ፡ ወርሮ ይበዘብዝ ዘንድ፡ አረማዊውን ንጉሥ፡ ናቡከደነፆርን፡ ታላቅ የሠይፍ ኃይልን አስታጥቆ፡ ወደኢየሩሳሌም ላከ፡ እርሱም፡ በዚያ፡ የቅጣት ተልእኮውን እንዲፈጽም፡ ኃጢአተኛውንም የእሥራኤል ትውልድ ፈጅቶ፡ የተረፉትን፡ በምርኮ፡ ወደምድሩ፡ ወደባቢሎን እንዲወስዳቸው፡ ለስደትም እንዲዳርጋቸው፡ አሠለጠነው::

ለዚያ ስደት ከተዳረጉት እሥራኤላውያን መካከል፡ በሃይማኖታቸው የጸኑና በምግባራቸው የተጠናከሩ፡ አካኼዳቸው፡ ከነቢዩ ዳንኤል ጋር የኾነ፡ አናንያ፡ አዛርያና ሚሳኤል የተባሉ መንፈሳውያን ወጣቶች ነበሩ:: እነዚህ፡ "ሠለስቱ ደቂቅ" የተባሉት፡ ሦስት ልጆች፡ በእውቀታቸውና በብልህነታቸው ተመርጠው፡ የንጉሡ ሹማምንት ኾነው ያገለግሉ ነበር::

የኋላ ኋላ ግን፡ የአገሩን አማልክት እንዲያመልኩ፡ ንጉሡ ላቆመውም ጣዖት እንዲሰግዱ፡ ያን ባያደርጉም፡ በአዋጅና ባደባባይ እየነደደ ባለ፡ አስፈሪ የእሳት ነበልባል ውስጥ የሚጣሉ መኾናቸውን የሚገልጽ፡ የፈተና ጥያቄ፡ ከንጉሡ ቀረበላቸው:: እነርሱም፡ ለገንዘብና ለሹመት ኳኍተው፡ የንጉሡን ቍጣም ፈርተው፡ አምላካቸውን የማይክዱ፣ ሃይማኖታቸውንም የማይለውጡ መኾናቸውን በመግለጽ፡ *"ንጉሥ ሆይ! የምናመልከው አምላካችን፡ ከእጅህም ኾነ፡ ከዚህ፡ ከሚነድደው የእሳት ነበልባል፡ ሊያድነን ይችላል፣ ባያድነንም እንኳ፡ አማልክትህን እንዳናመልክ፡ ላቆምኸውም፡ ለወርቁ ጣዖት እንዳንሰግድለት እወቅ!"* ሲሉ፡ በድፍረትና በቆራጥነት መልስ ሰጡት::

በዚህ ጊዜ፡ ፍርዱ እንዲፈጸምባቸው ከንጉሡ ታዞ፡ ሦስቱም ገድለኞች፡ በሚነድደው እሳት ውስጥ ተጣሉ:: ወደእሳቱ ሊጥሏቸው የወሰዷቸው ኃያላንም፡ በነበልባሉ ብርቱ ወላፈን እየተቃጠሉ ሞቱ::

## ምዕራፍ ፮፤ በዓል።
## ዓበይትና ንዑሳን በዓላት።
### የታኅሣሥ ገብርኤል።

---

ወደእሳቱ ውስጥ ታሥረው የተጣሉት፡ እኒህ መንፈሳውያን አርበኞች ግን፡ የእግዚአብሔር መልአክ፡ እሳቱን አቀዝቅዞላቸው፡ በነበልባሉ መካከል፡ ወዲያ ወዲህ ሲመላለሱ ከመታየት በቀር፡ በአካላቸው ቀርቶ፡ በልብሳቸው ላይ እንኳ፡ አንዳችም ጉዳት ሳይደርስባቸው፡ ከተፈረደባቸው የቃጠሎ ሞት ድነው፡ በደህና ሊወጡ ችለዋል። ይህንም፡ "የዚያን ጊዜም፡ ንጉሡ ናቡከደነፆር፡ ተደነቀ፡ ፈጥኖም ተነሣ፡ አማካሪዎቹንም፡ 'ሦስት ሰዎችን አሥረን፡ በእሳት ውስጥ ጥለን አልነበረምን? ...እነሆ፡ እኔ፡ የተፈቱ፡ በእሳቱም መካከል የሚመላለሱ፡ አራት ሰዎችን አያለሁ፡ ምንም አላቈሰላቸውም፡ የአራተኛውም መልክ፡ የአማልክትን ልጅ ይመስላል፡' ብሎ መለሰ።" የሚለው፡ የመጽሐፍ ቃል ያረጋግጣል።

"የአራተኛው መልክ፡ የአማልክትን ልጅ ይመስላል፡" የተባለው፡ ሊቀ መላእክት ቅዱስ ገብርኤል መኾኑን፡ ከትውፊታችን አግኝተነዋል።

በሃይማኖት ሳይወላውሉ፡ በምግባር ተጠናክረው፡ እስከመጨረሻው፡ ማለትም፡ የሞት ጽዋን ለመቀበል፡ ተዘጋጅቶና ቆርጦ እስከመቅረብ ድረስ፡ በጀመሩት ገድል፡ ጸንቶ መገኘት፡ የሚያስከትለው ውጤትና የሚያስገኘው ፍሬ፡ በነፍስ ብቻ ሳይኾን፡ የሥጋ ሞትን ጭምር በማስቀረት፡ የምሕረት ሕይወትን፡ በክፉት ኃይላትም ላይ፡ ድልን የሚያቀዳጅ፡ የመላእክት ተራዳኢነትን መኾኑን፡ በዚሁ፡ በታኅሣሥ ፲፱ ቀን የምናከብረው፡ የ"ታኅሣሥ ገብርኤል" በዓል ያስታውሰናል፡ ያስተምረናልም።

### ዘመነ ስብከት።

"ዘመነ ስብከት"፡ በታኅሣሥ ፳ እና በጥር ፲ ቀኖች መካከል ያሉት አራት፡ የእሑድ ሰንበታት፡ ከነሳምንታቶቻቸው፡ እያንዳንዳቸው፡ በቅደም ተከተል፡ "ስብከት"፡ "ብርሃን"፡ "ኖላዊ" እና "ጌና" ተብለው የሚጠሩት ናቸው።

በእነዚህ ሰንበታትና ሳምንታት፡-

- እግዚአብሔር ወልድ፡ በመንፈስ ቅዱስ ግብር፡ በድንግል ማርያም ማሕፀን ተፀንሶ፡ በፍጹም ሰውነት፡ ከእርሷ ስለመወለዱ፤
- የሰውነት አመጣጡም፡ ለዓለሙ በደል ቤዛ ኾኖ፡ የመሥዋዕትነት ዋጋን በመክፈል፡ ፍጥረቱን ለማዳን ስለመኾኑ፤
- "ኢየሱስ ክርስቶስ" በተባለበት ስሙም፡ በምድር ላይ እየተመላለሰ፡ ከኃጢኣት በቀር፡ እውነተኛውን ሰውኛ አኗኗር በመኖር፡ ለሰው ልጆች ኹሉ፡ ፍጹም አርአያነትን ስለማበርከቱ፡ በነቢያት የተነገሩትን የእግዚአብሔርን ትንቢታዊ ቃላት በመጥቀስ፡ ትምህርትና ምዕዳን (ምክር) ይሰጥባቸዋል፤ የተስፋ ዝማሬ ይሰማባቸዋል፡ ስለሥጋዌ ምሥጢርም፡ የቅኔያት ማዕበል ይወርድባቸዋል።

# ኢትዮጵያ እና ኢትዮጵያዊነት፣
## "ፈጣሪዬ" የምለው እግዚአብሔር፡ ማነው?

እነዚህን አርእስት በመከተል: "ፈኑ ኢዴከ እምአርያም!...ፈኑ ብርሃነከ ወጽድቀከ...": ማለትም: "እጅህን ከሰማይ ላክ!... ብርሃንህንና እውነትህን ላክ!" እያሉ: የቀደሙት ሰዎች: ወደፈጣሪያቸው ያቀርቡት የነበረው ያልተቋረጠ ልመና ተሰምቶላቸው: "አነ ውእቱ: ናባዊ ኄር!" ማለትም: ቸር ጠባቂ: እኔ ነኝ!" የሚላቸውና "የእግዚአብሔር ቀኝ እጅ": እውነተኛው የዓለም ብርሃን" የተባለው: ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ: እነሆ: "ሰው ኾኖ: በድንግል ማሕፀን ተፀነሰ! ተወለደ! እንደሰው: በምድር ላይ ተመላለሰ!" በማለት: በመንፈስ: ወደኋላ ተመልሰን: የነቢያትን የተስፋ ጉዞ ከፈጸምን በኋላ: ከጥምቀቱ በዓል እንደርሳለን።

የጥር ሥላሴ።

ከበዓለ ጥምቀት በፊት ግን: ጥቂት ቀደም ብሎ: በጥር ፯ ቀን: "የጥር ሥላሴ" በዓል ይከበራል። ይህም የኾነው: በታኅሣሥ ፩ ቀን በሚውለው: በኢየሱስ ክርስቶስ ትስብእት: ማለትም: አምላክ ሰው ኾኖ: በድንግል ማርያም ማሕፀን በመፀነሱ: የእግዚአብሔር: የአንድነቱና የሦስትነቱ ምሥጢር ስለተገለጸ: ስለታወቀና ስለተረዳ: የምሥጢረ ሥላሴና የምሥጢረ ሥጋዌ ነገር: በሰፊው እየተነገረ: ትምህርቱ እንዲሰጥበት: ምሥጢሩም እንዲፍታታበት ታስቦ ነው።

## ዘመነ አስተርእዮ።

ጥያቄ:- "አስተርእዮ" ምን ማለት ነው? ለምሳሌ: "አስተርእዮ ማርያም" እየተባለ: በዘልማድ እንደሚነገረው አባባል: በበዓላት ላይ እየተቀጸለ የሚደመጥ ዘይቤ አለ፣ ግን: እንዲህ የሚባለው: ለምንድር እንደኾነ: እናውቀውምና: ብታስረዳን?

መልስ:- "አስተርእዮ": "ታየ"፣ "ተገለጠ" የሚል ትርጉም ካለው: "ተርእየ" ከሚለው የግእዝ ቃል: የተገኘ ነው፣ "በገሃድ መታየት": "በይፋ መገለጥ" ማለት ነው። ከዚህ የተነሣ: ከበዓለ ጥምቀት አንሥቶ: እስከጾመ ኢትዮጵያ (ጾመ ነነዌ) ድረስ ያለው ጊዜ: "ዘመነ አስተርእዮ" ይባላል። እንዲህ የተባለበትንም ምክንያት ላሳውቃችሁ!

አስተርእዮ: "'የዲያብሎስን ገዢነት፡ የኃጢአትን ቀንበርና የሞትን ፍዳ: ለአንዴና ለመቼውም ጊዜ በመደምሰስ: ፍጥረቱን ኹሉ ለማዳን: ወደዓለም ይመጣል!' ተብሎ: ትንቢት ተነግሮለትና ሱባዔ ተቆጥሮለት: በተስፋ የሚጠበቀው: እግዚአብሔር ወልድ: ፍጹም ሰው በመኾን: በቅድስት ድንግል ማርያም ማሕፀን: በመንፈስ ቅዱስ ግብር: ያለወንድ ዘር ተፀነሰ፡ ከእርሷ: በድንግልና ተወልዶ: የሰው ልጅ ተባለ፣ ከኃጢአት በቀር: በኀውን የሰውን ሥራ እየሠራም: ለሠላሳ ዘመን በምድር ላይ ተመላለሰ።

# ምዕራፍ ፯፡ በዓል።
## ዓበይትና ንዑሳን በዓላት።
### ዘመነ አስተርእዮ።

"ከዚህ በኋላ፡ በዮርዳኖስ ወንዝ መካከል ቆሞ ሣለ፡ አባቱ፡ እግዚአብሔር አብ፡ ድምፁን በማሰማት፡ መንፈስ ቅዱስ፡ በርግብ አምሳል፡ ራሱ ላይ በመቀመጥ፡ እርሱ ራሱም፡ በአዋጅ ነጋሪው፡ በዮሐንስ እጅ በመጠመቅ፡ ማንነቱን፡ በይፋ ገለጠ!" ማለት ነው።

ይህ ወራት፡ የማይታየው፡ የአምላክ አካልና ባሕርይ፡ ከሚታየው፡ የሰው አካልና ባሕርይ ጋር ተዋሕዶ የተገለጠበትንና ማንነቱ በገሃድ የታወቀበትን ምሥጢር በማብራራት፡ ምሥራቹ የሚነገርበት፡ በዚህ መለኮታዊ የቸርነት ድርጊትም፡ ሰው ኹሉ፡ ደስታውን የሚገልጽበትና ምስጋናውን፡ ለፈጣሪው የሚያቀርብበት ጊዜ ስለኾነ፡ "ዘመነ አስተርእዮ" መባሉ፡ ትክክልና ተገቢ ኾኖ ይገኛል።

ከጥምቀት ጋር፡ ከእርሱም በኋላ፡ በዚሁ፡ በዘመነ አስተርእዮ የሚከበሩት በዓላት፡ ከዚህ የሚከተሉት ናቸው፦

## በዓለ ጥምቀት።

*ጥያቄ፦ ጥምቀት፡ በክርስቲያኑ ዓለም ካሉ ሕዝቦች ኹሉ ተለይቶ፡ በእኛ፡ በኢትዮጵያውያን ዘንድ ብቻ፡ እንዲህ፡ በታላቅ ድምቀት የሚከበርበት፡ ምክንያቱ፡ ምን እንደኾነ ብናውቀው፡ ለእየራሳችን ብቻ ሳይኾን፡ ለሌሎችም ለማስረዳት ይጠቅመናል።*

መልስ፦ አዎን! ማወቁ፡ ይጠቅማችኋል፡ ያስፈልጋችኋልም። ምክንያቱ፡ እንዲህ ነው፦ በዘመነ አስተርእዮ ከሚከበሩት በዓላት መካከል፡ ዋናው፡ እንደምታውቁት፡ "ጥምቀት" ነው። በተዋሕዶ የከበረው፡ የኢየሱስ ክርስቶስ ፍጹም አምላክነትና ፍጹም ሰውነት፡ ለዓለሙ ተገልጦ የተመሰከረበት፡ መታሰቢያውም፡ ጥር ፲፩ ቀን እንዲውል የተደረገው፡ የጥምቀቱ በዓል፡ "ከተራ" ከሚባለው፡ ከዋዜማው ጀምሮ፡ በታላቅ ድምቀት ይከበራል።

ለበዓሉ ሥርዓት ማስፈጸሚያ የሚያስፈልገውን፡ ባሕረ ጥምቀት፡ ውኃውን፡ ከወንዝ፡ በበይ መርተውና ከትረው (ገድበው) የሚያዘጋጁበት፡ ለመንበረ ታቦቱ ማሳረፊያና ለቀዳስያኑ ማገልገያ፡ ለደባትሩም ማሕሌት መቆሚያና ለምእመናኑ መሰባሰቢያ የሚኾኑት ድንኳኖች የሚተከሉበት፡ በዚያ፡ በባሕረ ጥምቀቱ አካባቢ የሚያድረውም ሰው፡ በየወገኑ፡ የየራሱን ዳስ የሚቀልስበት ዕለት ስለኾነ፡ ይህ፡ የጥምቀት በዓል ዋዜማ፡ "ከተራ" ይባላል። "መከተር" (ውኃ መገደብ) ከሚለው ቃል የወጣ ነው።

በዘመነ አሪት፡ እሥራኤል፡ ከግብፅ ከወጡ በኋላ፡ "ምድረ ርስት" ወደተባለችው፡ የከነዓን አገር ከመግባታቸው በፊት፡ አርባ ዓመት ሙሉ፡ በሲና ምድረ በዳ ሲንከራተቱ፡ ማደሪያቸው፡ ድንኳንና ዳስ ስለነበረ፡ የኋላ ትውልድ፡ ያን፡ የመከራና የፈተና ዘመን እንዳይረሳ፡ "የዳስ በዓል" እያሉ፡ በያመቱ እንዲያከብሩት፡ እግዚአብሔር አዝዟቸው ነበረ።

## ኢትዮጵያ እና ኢትዮጵያዊነት፤
### "ፈጣሪዬ" የምለው እግዚአብሔር፡ ማነው?

---

እኛ ኢትዮጵያውያን፡ በኪዳን አሪቱ የብሉዩ ዘመን፡ በዚያው፡ በኦሪቱ ሥርዓት፡ ስናከብረው ከቆየን በኋላ፡ በመጨረሻ፡ በዘመነ ክርስትና፡ በጥምቀት ተክተን፡ በዓሉን፡ እነሆ፡ ዛሬ በሚታሰብበት መልክ ማክበራችንን ቀጠልን። ስለዚህ፡ ካህናቱ፡ በተንቈጠቈጠ መጎናጸፊያ ተሸክመው፡ በዝግታ እየተራመዱ፡ በክብር የሚያጓጉዙት፡ የአዲስ ኪዳኑ ታቦት፡ የተዋበ ልብሰ ተክህኖ በለበሱ፥ መብራትና መስቀል፥ የማዕጠንተ ወርቅ ጽንሐ፥ ዣንጥላና ድባብ በያዙ ልኡካን ተከብቦ፡ በማኅሌታውያኑ ደባትር ሃሌታ፥ በወጣት መዘምራን ደስታ፡ በወንዶች ሆታና በሴቶች እልልታ ታጅቦ፡ በበዓሉ ዋዜማ፡ ከቤተ መቅደሱ ይነሣል። በዚህ መልክ፡ ወደወንዝ፥ ወይም፡ ወደከተራው ቦታ ይወርድና በዚያው አድሮ፡ በማግሥቱ፡ በዋናው የጥምቀት በዓል ዕለት፡ በታላቅ ብሔራዊ ክብር፡ ወደመካነ መንበሩ ይመለሳል። ለዚህ ሥርዓታችን መነሻ የኾነውን ምክንያት፡ እንዲህ በሚል ቃል አጠቃልልላችኋለሁ፡-

እኛ ኢትዮጵያውያን፡ በጥምቀት በዓል የምናካኺደው ሥርዓት፡ እግዚአብሔር፡ ለእሥራኤል ልጆች፡ "አወርሳችኋለሁ!" ብሎ፡ ተስፋ ወደሰጣቸው ምድረ ርስት ይገቡ ዘንድ፡ የኢየሱስ ክርስቶስና የድንግል ማርያም ተቀዳሚት አርአያ የኾነችውን ታቦተ ጽዮንን፡ የኦሪቱ ካህናት ተሸክመው፡ የዮርዳኖስን ወንዝ እንዲያቋርጡ፡ ትእዛዝ ሰጧቸው፡ ወንዙን ሲሻገሩ፡ የወንዙ ውኃ፡ ከኹለት ተከፍሎና በራሱ ኃይል፡ ተከትሮ ቆሞላቸው፡ ሕዝቡ፡ በቀይ ባሕር እንደኾነው፡ በደረቁ መሬት ለመሻገር የቻሉበትን የእግዚአብሔርን ቸርነት ያስታውሰናል።

እንደዚያን ጊዜ ኹሉ፡ ዛሬ፡ በዘመነ ሐዲስ ደግሞ፡ አማናዊቷ፡ ሕያውቷና ዘለዓለማዊቷ ታቦተ ጽዮን ከኾነችው ከድንግል ማርያም የተወለደው፡ አማናዊው፥ ሕያዊውና ዘለዓለማዊው ጽላተ ኪዳን፡ ኢየሱስ ክርስቶስ፡ ወደዮርዳኖስ ወንዝ ወርዶ፡ በዮሐንስ እጅ ከተጠመቀ በኋላ፡ በእርሱ ጥምቀት፡ እኛ፡ ከዲያብሎስ የባርነት አገዛዝ ነጻ ወጥተን፡ የእግዚአብሔር ልጆች የመኾንን ክብር እንድንቀዳጅ ማድረጉን እንዳንዘነጋ፥ ከዚህ የተነሣም፡ ከኃጢአት፡ ወደጽድቅ፥ ከሞት፡ ወደሕይወት ተሻግረን፡ ዘለዓለማዊቷን የእግዚአብሔርን መንግሥት የወረስን መኾናችንን ያረጋግጥልናል።

ከታቦቱ ፊት፡ የቤተ ምልክናው ሠራዊት፡ "ተመልከት ዓላማህን! ተከተል አለቃህን!" የሚለውን፡ የባለመስቀል መፆር ሰንደቅ ዓላማውን አንግቦ ይቀድማል፤ በመካከሉ፡ የቤተ ሕዝቡ ወገን የኾነው፡ ወንዱም፡ ሴቱም፥ ሕፃኑም፡ ሽማግሌውም፡ ፀዓዳ (ነጫጭ) የክት ልብሱን ለብሶ፡ በሆታና በእልልታ ይከተላል፤ ከዚያም፡ የቤተ ክህነቱ ዘርፍ የኾኑት መዘምራኑ ቀጥለው፡ በመቋሚያና በጸናጽል፥ በከበሮና በማኅሌት እያሸበሸቡ ይጓዛሉ። ከታቦቱም በኋላ፡ የቤተ ክህነቱ፥ የቤተ ምልክናውና የቤተ ሕዝቡ ባለሥልጣኖች፡ ታቦቱን ያጅባሉ።

ይህም የሚኾነው፡ ከኪዳነ ልቦናው ዘመን ጀምሮ፡ ሲሠራበት ከቆየው፡ ከጥንታዊው የኢትዮጵያውያን ጥንታዊ ሥርዓት ጋር ተዋሕዶ የቀጠለውን፡ የቅርቡን፡ የኪዳነ ኦሪቱን ዘመን ሥርዓት ለማስታወስ ያህል ነው።

## ምዕራፍ ፮፤ በዓል።
## ዓበይትና ንዑሳን በዓላት።
## በዓለ ጥምቀት።

---

ያም፡ ንጉሡ ዳዊት፡ ታቦተ ጽዮን፡ በእሥራኤል ካህናትና ሕዝብ ተረስታና ተጥላ ከነበረችበት ሥፍራ፡ ወደኢየሩሳሌም ከተማ በአጀብ አምጥቶ፡ ባዘጋጀላት የማረፊያዋ ድንኳን ውስጥ ባስገባት ጊዜ፡ ከደስታው ብዛት የተነሣ፡ ከክብት እረኝነት አንሥቶ፡ ለሕዝብ መሪነት ባበቃው ፈጣሪው ፊት፡ ራሱ፡ በካህናቱና በሕዝቡ ፊት አብሮ እየዘመረ፥ እያጨበጨበና እየዘለለ፡ የምስጋና ስሜቱን ይገልጽ የነበረበትን ምሳሌ የተከተለ መኾኑ ነው።

### ጥምቀት፡ የእኛም፡ የየግላችን በዓል ስለመኾኑ።

የጥምቀት በዓል፡ የኢየሱስ ክርስቶስ በዓል ብቻ አይደለም፡ በእርሱ ጥምቀት ተቀድሰንና ተጠምቀን፡ የእግዚአብሔር ልጆች ለመኾን የበቃነው፡ የእኛም፡ የሰው ልጆች የኾንነው፡ የኢትዮጵያውያን በዓል ጭምር ነው እንጂ።

በዓሉ፡ በመጀመሪያ ነገር፡ በአዲሱ ኪዳን፡ ኢየሱስ ክርስቶስ፡ የራሱን ማንነት፡ ለዓለም የገለጸባትንና ያስመሰከረባትን፡ ጥምቀቱንና ቀኒቱን ያስታውሰናል፡ ቀጥሎ፡ የኹሉ ፈጣሪና አምላክ የኾነው እርሱ፡ ለእኛ አብነት የኾነውን የጥምቀትን ሥርዓት፡ ራሱ ፈጽሞ፡ እኛም፡ ያንኑ ሥርዓት በመፈጸም፡ የመንፈስ ቅዱስን ጸጋ ተቀብለን፡ የእግዚአብሔር ልጆች ለመኾን የበቃንበትን አምላካዊ ፍቅርና ቸርነት፥ ከዚህ የተነሣም፡ የተቀዳጀነውን፡ ይህን፡ ወደር የሌለውን ዘለዓለማዊ የመጨረሻ ክብር፡ አጕልቶ ያሳየናል።

አዎን! ሐዋርያው፡ *"'የእግዚአብሔር ልጆች' ተብለን ልንጠራ፡ አብ፡ እንዴት ያለውን ፍቅር እንደሰጠን እዩ! እንዲሁም ነን።"* ያለውን በማዘከር፡ የጥምቀት በዓል፡ ከእግዚአብሔር፡ በመንፈስ ቅዱስ ተወልደንና ለዘለዓለም ሕይወት ተጠርተን፡ "'የእግዚአብሔር ልጆች' የተባልንበትና የእግዚአብሔር መንግሥት ወራሾች የኾንንበት፡ የየራሳችን የልደት በዓል ነው!" ብለን፡ አምነን፡ በንጹሕ ምስጋናና በፍጹም ደስታ የምናከብረው ታላቅ በዓላችን ነው።

በዓለ ጥምቀትን፡ እኛ ኢትዮጵያውያን ብቻ፡ ከሌላው የክርስቲያኑ ዓለም ተለይተን፡ እጅግ በተመሰጠ፡ መንፈሳዊው ስሜት የምናከብርበትን ምክንያት የሚያመለክተውን፡ እንዲህ የሚለውን አጭር ትንተና አጠቃልዬ አቅርቤላችኋለሁና፡ ተመልከቱት፦

፩ኛ፡ *"በኖኅ ዘመን፡ የእግዚአብሔርን ትዕግሥቱን፡ ደጅ እየጠኑ የነበሩት፡ ጥቂቶቹ፡ ስምንት ሰዎች፡ መርከብን ሠርተው፡ ከጥፋት ውኃ እንደዳኑባት ኹሉ፡ አኹንም፡ እኛን፡ በዚያው አምሳል፡ በጥምቀት ያድነናል፤ ሥጋን፡ በእድፍ በመታጠብ አይደለም፤ በእግዚአብሔርና በጌታችን፡ በኢየሱስ ክርስቶስ ትንሣኤ በማመናችን፡ በበጎ ሕሊና የሚፈጸመውን መልካም ግብርን ያስተምረን ዘንድ ነው እንጂ።"* በሚለው የመጽሐፍ ቃል መሠረት፡ እግዚአብሔር፡ የኪዳኑ ልቦናዋን የኖኅ መርከብ፡ በባሕረ ነጋሽ ላይ ያሻገረበት መለኮታዊና ምሥጢራዊ ሥርዓቱ፡ በኢትዮጵያውያን ዘንድ፡ ከጥንት ጀምሮ፡ ተጠብቆ ሲሠራበት የቆየ በመኾኑ ነው፤

# ኢትዮጵያ እና ኢትዮጵያዊነት፤
## "ፈጣሪዬ" የምለው እግዚአብሔር፡ ማነው?

፪ኛ፡ ኢያሱ፡ የኪዳን አሪቷን የእግዚአብሔር ታቦት በተሸከሙ ካህናት፡ የእሥራኤልን ሕዝብ፡ በዮርዳኖስ ባሕር የማሻገሩ ዜና መዋዕል አብሮ የሚገኝበትን፡ ቀደም ብዬ ያወሳሁላችሁን የታቦተ ጽዮን ዝክረ ነገር የሚያከትተው፡ የኪዳን አሪቱ ሥርዓት፡ በኢትዮጵያ፡ ከቀደመው ጋር ተዋሕዶ፡ እንዲቀጥል በመደረጉ ነው፡

፫ኛ፡ ትንቢቱ ኹሉ ተፈጽሞ፡ ተስፋውም ኹሉ ደርሶ፡ እግዚአብሔር፡ ሰው መኾኑ ከተገለጸ በኋላ፡ በመጥምቁ ዮሐንስ ይሠራበት የነበረው፡ የንስሐ ጥምቀት ሳይቀር፡ ጌታችን፡ ለኒቆዲሞስ በገለጸው የጥምቀት ምሥጢር መሠረት፡ የኪዳን ልቡናውና የኪዳን አሪቱ ሥርዓታት፡ ኹሉም፡ በአዲሱ ኪዳን መንፈስ ቅዱስ ታድሰው፡ ዛሬ፡ በኢየሱስ ክርስቶስ ምሳሌ፡ የአዲስ ኪዳኑን ታቦት የተሸከሙ ካህናት፡ ወደወንዙ፡ ወይም፡ ወደኩተሬው የሚወርዱበት ሥርዓት በመተካቱ ነው።

ኢትዮጵያውያን፡ በዚህ በዓላችን ጊዜ፡ *"ክርስቶስ ተጠምቀ እሰይ! ወለደነ ዳግመ እማይ!"* ማለትም፡ "ክርስቶስ፡ ስለተጠመቀ ደስ ይበለን! እኛም፡ በጥምቀት፡ ከውኃና ከመንፈስ ቅዱስ፡ እንደገና እንድንወለድ አደረገ!" የሚለውን የምሥራች ቃል፡ እንለዋወጣለን። ይህ የደስታ መንፈስና ሥርዓት፡ እንደዘመኑ ትንሣኤ፡ እስከጥር ፳፩ ቀን ድረስ ይቀጥላል።

በበዓሉ ዕለት፡ ከዚህም ቀን ጀምሮ፡ በዚሁ ወራት የሚነገረውና የሚሰማው፡ የሚሰበከውና የሚዘመረው፡ ስለምሥጢረ ጥምቀት ሲኾን፡ ይህ፡ የምሥጢረ ጥምቀት ነገር፡ በዚህ ውይይታችን የአምስቱ አዕማደ ሃይማኖት ርእስ ሥር፡ በሰፊው የተብራራና በዝርዝር የተተቸበት ስለኾነ፡ ያን ሓተታ እንድታስታውሱት ከማሳሰብ በቀር፡ እዚህ ላይ መጨመሩ የሚያስፈልግ አይመስለኝም።

## ቃና ዘገሊላ።

ኢየሱስ ክርስቶስ፡ በዮርዳኖስ ወንዝ፡ በአዋጅ ነጋሪው ዮሐንስ እጅ በተጠመቀ ጊዜ፡ ከድንግል ማርያም ተወልዶ፡ ሰው የኾነው፡ የእግዚአብሔር ወልድ ማንነት በይፋ ተገልጦ ከታወቀ ወዲህ፡ ወዲያው ተከታትሎ፡ በሦስተኛው ቀን፡ ይኸው ማንነቱ፡ በበለጠ ግዙፍ ማስረጃ የተረጋገጠበት የመጀመሪያው ተአምር፡ "ቃና ዘገሊላ" በምትባለው ቦታ፡ ተፈጽሞ ታየ። ከበዓለ ጥምቀት ቀጥሎና ተያይዞ የሚከበረው "የአስተርእዮ" በዓል፡ "ቃና ዘገሊላ" ይባላል።

"ገሊላ"፡ ዋና ከተማው፡ "ናዝሬት" የኾነ፡ ቀድሞ፡ የፍልስጥኤም፡ ዛሬ፡ የእሥራኤል ክፍለ አገር ሲኾን፡ "ቃና"፡ በገሊላ የምትገኝ፡ ወረዳ ናት። በዓሉ፡ "ቃና ዘገሊላ" የተባለው፡ እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያምና ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ተጠርተው በተገኙበት ሠርግ ላይ፡ እርሷ፡ በእናትነት፥ ልጇም፡ በልጅነት ደረጃ ተነጋግረው፡ የመጀመሪያው ታላቅ ተአምር የተፈጸመበት ቦታ፡ "ቃና ዘገሊላ" ወይም፡ "የገሊላዋ ቃና" እየተባለ የሚጠራ ስለኾነ ነው።

# ምዕራፍ ፺፡ በዓል፡፡
## ዓበይትና ንዑሳን በዓላት፡፡
## ቃና ዘገሊላ፡፡

---

### የድንግል ማርያም፡ እመ አምላክነትና አማላጅነት፡ በይፋ የታወቀበት ሠርግ፡፡

*ጥያቄ፡- የቃና ዘገሊላ ዝክረ ነገር፡ በኢትዮጵያውያን ዘንድ፡ ይህን ያህል፡ ከፍተኛ ግምት ተሰጥቶት፡ በዚህ መልክ የሚከበረው ለምንድር ነው?*

መልስ፡- *ይህ የኾነው፡ ያለምክንያት አይደለምና፡ ይህንኑ ልግለጽላችሁ!* በዚያ ሠርግ ላይ የደረሰውን ኹሉ፡ ወንጌላዊው ዮሐንስ፡ እንዲህ ሲል ጽፎታል፡- *"በገሊላ ቃና፡ ሠርግ ነበረ፡ የኢየሱስም እናት፡ በዚያ ነበረች፡ ኢየሱስም ደግሞ፡ ደቀ መዛሙርቱም ወደሠርጉ ታደሙ፡፡*

*"የወይን ጠጅም ባለቀ ጊዜ፡ የኢየሱስ እናት፡ 'የወይን ጠጅ እኮ የላቸውም!' አለችው፡፡ ኢየሱስም፡ 'እናቴ ሆይ! ለምን ታስቸግሪኛለሽ? ጊዜዬ እኮ ገና አልደረሰም!' አላት፡፡ እናቱም፡ ለአገልጋዮቹ፡ 'የሚላችሁን ኹሉ አድርጉ!' አለቻቸው፡፡ አይሁድም እንደሚያደርጉት የማንጻት ልማድ፡ ስድስት የድንጋይ ጋኖች፡ በዚያ ተቀምጠው ነበር፡ እያንዳንዳቸውም፡ ኹለት ወይም ሦስት እንስራ ይይዙ ነበር፡፡*

*"ኢየሱስም፡ 'ጋኖቹን፡ ውኃ ሙሏቸው!' አላቸው፡፡ እስከአፋቸውም ሞሏቸው፡፡ 'አሁን ቀድታችሁ፡ ለአሳዳሪው ስጡት!' አላቸው፡፡ ሰጡትም፡፡ አሳዳሪውም፡ የወይን ጠጅ የኾነውን ውኃ በቀመሰ ጊዜ፡ ከወዴት እንደመጣ አላወቀም፡ ውኃውን የቀዱት አገልጋዮች ግን፡ ያውቁ ነበር፡ አሳዳሪውም ሙሽራውን ጠርቶ፡ 'ሰው ኹሉ አስቀድሞ፡ መልካሙን የወይን ጠጅ፡ ከሰከሩም በኋላ፡ መናኛውን ያቀርባል፡ አንተስ፡ መልካሙን ጠጅ፡ እስካሁን አቆይተሃል፡' አለው፡፡ ኢየሱስ፡ የገሊላ አውራጃ በምትኾን በቃና ያደረጋት፡ የተአምራቱ መጀመሪያ፡ ይህች ናት፡ ክብሩንም ገለጠ፡ ደቀ መዛሙርቱም፡ በእርሱ አመኑ፡፡"*[፻፺]

ይህ፡ የወንጌላዊው ቃል፡ የሰው ልጆች ለኾንነው ኹሉ፡ በተለይም፡ ለእኛ፡ ለኢትዮጵያውያን፡ በቁም ነገር ልናስተውላቸው የሚገቡ መልእክቶችን አስተላልፎልን እናገኘዋለን፡፡ እነዚህም፡ የሚከተሉት ናቸው፡-

፩ኛ፡ የቅድስት ድንግል ማርያምና የልጇ የኢየሱስ ክርስቶስ፡ በዚያ የሠርግ በዓል ላይ፡ መገኘት፡ *"ባልና ሚስት፡ አንድ ሥጋ ናቸው እንጂ፡ ኹለት አይደሉም፡ እግዚአብሔር አንድ ያደረገውን፡ እንግዴህ፡ ሰው አይለየው!"* ተብሎ፡ ፈጣሪ አምላክ፡ በፍጥረት መጀመሪያ፡ በአዳምና ሔዋን የመሠረተውን፡ ኢትዮጵያውያንም፡ በኪዳነ ልቦናና በኪዳነ ኦሪት፡ ጠብቀው ያኖሩት፡ የብሉዩ ኪዳን የጋብቻ ሥርዓት፡ በአዲሱ የምሕረት ኪዳን፡ በኪዳነ[፻፺፩] መንፈስ ቅዱስም፡ መጽናቱንና መጽደቁን፡ መቀደሱንም ያረጋግጥልናል፡፡

፪ኛ፡ የሠርጉ በዓል፡ በእርግጥ፡ የኢየሱስ ክርስቶስ ማንነትና ክብር በይፋ የተገለጠበት መኾኑን፡ ራሱ፡ የወንጌላዊው ቃል፡ በሚበቃ ያስረዳል፡፡